# ሕብረተሰብ ትምህርት
# የመምህራን መምሪያ መጽሐፍ
# ሰባተኛ ክፍል


**አዘጋጆች :**

ጀማል ሙስጠፋ (M.Ed.)

ነጋሽ ሄቦ (M.A.)

ነጌሶ እስሞ (M.Sc.)

**አርታኢዎች:**

በላቸዉ አበራ (M.A)

ግርማ ፀጋየ (M.Ed.)

**ገምጋሚዎች:**

**በቀለ ቀነአ**

**አበራ ከበበዉ**

**ፍቃዱ ከበደ**

**ቤኪ ቶለሣ**

**ተርጓሚዎች:**

1. **በቀለ ቀነአ**
2. **ቤኪ ቶለሣ**
3. **አበራ ከበበዉ**
4. **ከተማ ፀጋ**
5. **ዘዉዴ ረጋሣ**

**ግራፊክስ:**

ታደሰ ድንቁ

© የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ፣ 2014/2021

ይህ መጽሐፍ በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮና በሮቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ትብብር በ2014/2021 ተዘጋጀ፡፡

የዚህ መጽሐፍ የባለቤትነት መብት በህግ የተጠበቀ ነው፡፡ ከኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ፈቃድ ውጪ በሙሉም ሆነ በከፊል ማሳተምም ሆነ አባዝተው ማሰራጨት በህግ ያስጠይቃል፡፡

## መዉጫ

ገፅ


ምዕራፍ 1:የመሬት አፈጣጠር ባህሪያት........................................................................1

1.1. የመሬት አፈጣጠርና ሥርዓተ ፀሓይ ..........................................................1

1.2 በመሬት ገጽ ላይ የሚገኙና የመሬት ውስጣዊ ክፍሎች............................5

1.3 ቅርፊት መሬት የተሠራባቸው ነገሮች .......................................................9

1.4 የዓለቶች ሥርጭትና በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ውስጥ ያላቸው ጠቀሜታ.........12

ምዕራፍ 2፡ የአለም አፈጣጠርና የሰው ልጅ ዝግመታዊ ለውጥ...........................15

2.1 የሰዉ ልጅ ዝግመታዊ ለውጥ ..................................................................15

2.2. የአለም ህዝብ ሁኔታ..............................................................................18

2.3. መንግዣ እድገት ፅንሰ ሀሳብ...................................................................28

ምዕራፍ 3፡ ሰዉና የተፈጥሮ ሀብት......................................................................36

3.1. በሰዉ ልጅና በተፈጥሮአዊ አከባቢ መካከል ያለዉ ግንኙነት ....................36

3.1 የሰዉ ልጅና በተፈጥሮ ሀብት መካካል ያለዉ ግንኙነት ...........................38

3.1. በኢትዮጵያ ውስጥ በተፈጥሮ ሀብት ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ነገሮች .........41

ምዕራፍ 4፡ ቀደምት የአለም ስልጣኔ..................................................................44

4.1.ጥንታዊ የአለም ስልጣኔዎች...................................................................44

4.2. የመካከለኛው ክፍለ ዘመን የአለም ታሪክ ..............................................49

ምዕራፍ 5፡ቀደምት የአፍሪካ ታሪክ....................................................................54

5.1. የጥንታዊ ግብፅ ስልጣኔ.........................................................................54

5.2. የጥንታዊ ኑቢያ /ኩሽ/ስልጣኔ.................................................................60

5.3. ጥንታዊ የሜሮኤ ስልጣኔ.......................................................................63

ምዕራፍ 6፡ጥንታዊውና የመካከለኛ ዘመን የኢትዮጵያ መንግሥታትና የህዝቦች ታሪክ....................69
6.1. ጥንታዊ የኢትዮጵያ መንግሥታት....................70
6.2.የኢትዮጵያ ሙስሊም ሱልጣኔቶች እና የጎንደር ምስረታ....................73
6.3 የህዝቦች ግንኙነት፣ትስስር እና እንቅስቃሴ....................76
6.4. የኢትዮጵያ መሰረታዊ የምጣኔ ሀብት እንቅስቃሴ....................80
ምዕራፍ 7 ፡ልዩ ትኩረት የሚሹ የዓለም ጉዳዮች....................85
7.1 የምንኖርበት አከባቢ....................85
7.2. የህዝብ ቁጥር መጨመር....................88
7.3. ሽብርተኝነት....................90
7.4. በህገ ወጥ መንገድ የሰዎች ዝውውር....................92
የሕብረተሰብ ትምህርት መርሐ ትምህርት 7ኛ ክፍል....................84

# ምዕራፍ 1፡የመሬት አፈጣጠር ባህሪያት

የተሰጠ የክፍለ ጊዜ ብዛት ----------------20

## ከምዕራፉ የሚጠበቁ የመማር ውጤቶች፡

## ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡

- የመሬት አፈጣጠርና የሥርዓተ ፀሓይ ሁኔታን ይገልፃሉ፤
- አራቱን የመሬት ይዘቶችና ግንኙነታቸዉን ይገልፃሉ፤
- የመሬት ንብርብሮችና ባህሪያቸዉን ይገልፃሉ፤
- የመሬት ውስጣዊ ክፍል የመረጃ ምንነት በቀጥተኛና በተዘዋዋሪ  መንገድ ይለያሉ፤
- በኢትዮጵያ የዓለቶች ሥርጭትና በኢኮኖሚ ላይ ያለዉ ጠቀሜታ ይመረምራሉ፡፡

### መግቢያ

በ5ኛና 6ኛ ክፍል በአከባቢ ሣይንስ ትምህርት ላይ ስለ አየር ንብረት፣ የአየር ሁኔታ፣ የህዝቦች አሠፋፈርና መገኛ፣ የኢትዮጵያና የኦሮሚያ ክልል ህዝቦችን በስፋት ተምራቹዋል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ደግሞ ስለሥርዓተ ፀሓይ፣ የመሬት አፈጣጠር፣ የሥርዓተ ፀሓይ አካላት፣ ፕላኔቶች፣ የመሬት ገፅታ መዋቅር፣ የመሬት ውስጣዊ መዋቅር፣ ዓለቶችና ሥርጭታቸዉ እንድሁም ዓለቶች በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ውስጥ ያለዉ ጠቀሜታ የሚሉትን ይማራሉ፡፡

## 1.1. የመሬት አፈጣጠርና ሥርዓተ ፀሓይ

ተማሪዎች ቢያንስ ልደርሱበት የሚገቡ የመማር ብቃት

ከዚህ የምዕራፉ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡

- መሬትና ሥርዓተ ፀሓይ የተፈጠሩበት ሁኔታን ይገልፃሉ፤
- ሥለ ፕላኔቶችና የፕላኔቶች እንቅስቃሴ ይገልፃሉ፡፡

ይህ ርዕስ የበለጠ ተጨባጭ እንዲሆን በፊዝክስ ትምህርት ውስጥ ስለሚገኝ ከፊዝክስ መምህር ጋር በመወያየትና መጽሓፍን፣ በማንበብ ግንዛቤ ማግኘት አስፈላጊ ነው፡፡

## ቅድመ ዝግጅት

የዚህን ርእስ ለማስተማር የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የስርአተ ፀሀይ ምስል፤ ግሎብ፤ ስለፕላኔቶች መረጃ የሚሰጥ ቻርት፤ የመሬት እንስስቃሴ አቅጣጫ የሚያሳይ ምስል ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው፡፡

## የመማር ማስተማር ዘዴ

የዚህን ርእስ ትምህርት የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ማስተማር ይቻላል፡፡ ተማሪዎች ከሚያውቁት በመነሳት የተማሪዎች መማሪያ መጽሀፍ ላይ የሚገኙ የግምገማ ጥያቄዎችን እንደ መነሻ በመጠቀም ለምሳሌ ስርአተ ጸሀይ አፈጣጠር በስርአተ ጸሀይ ውስጥ የሚገኙ ነገሮች ምን ምን አንደሆኑ በመጠየቅ መልሶቻቸው በሰሌዳ ላይ መፃፍ ያስፈልጋል ፡፡ በመቀጠልም የተማሪዎችን ግንዛቤ ለመጨመርና የመማር ማስተማር ሁኔታን ተጨባጭ ለማድረግ የምዕራፉን ገለጻ በውይይት መልክ መጀመር፡፡ የመልመጃ ስራዎችን በተሰጠው ጊዜ ውስጥ እንድሰሩ ማበረታታት የበለጠ ውጤት ሊያመጣ ይችላል፡፡ ይሁን እንጂ ተማሪዎች ቢያንስ ልደርሱበት የሚገባቸዉ የመማር ብቃት ለማሳካት ተማሪዎችን ያማከለ የመማር ማስተማር ዘዴ መምረጥ ያስፈልጋል፡፡ በተማሪዎች መካከል ያለውን ልዩነት ለማጥበብ ቁጥጥርና ክትትል በማድረግ በቂ ድጋፍና ገለጻን በመስጠት ተመሳሳይ ግንዛቤን አንዲያገኙ ማድረግ ይቻላል፡፡

## ልዩ ተሠጥዖና ከፍተኛ የሆነ ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎች

ልዩ ችሎታና ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታቸውን እንዲያሳድጉ ማበረታታት አስፈላጊ ነው፡፡ ውይይቱን ቶሎ መጨረስ ስለሚችሉ ርእሱን የበለጠ ሊያስገነዝባቸው የሚችል ጥያቄዎችን በማዘጋጀት መስጠት ያስፈልጋል ፡፡

ይሁን እንጂ የተለየ ችሎታ ያላቸውን ተማሪዎች ለመደገፍ ጥያቄዎችን ስታዘጋጁ በክፍል ውስጥ ያሉ በዝግታ የሚማሩና ሴት ተማሪዎችን ደግሞ ተጨማሪ ሥራን እንዲሰሩ በመስጠት የመማር ችሎታቸዉን እንደያሻሽሉ ማድረግ መረሳት የለበትም፡፡

## ተከታታይ ምዘና

ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዱ ለማወቅ ተከታታይነት ያለው ክትትል ማድረግ አስፈላጊ ነው፤፡ የተማሪዎችን ችሎታ በመለየት የሚያስፈልጋቸውን እገዛ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ ለምሳሌ ስርአተ ጸሀይ እንዴት ተፈጠረች? የሥርዓተ ጸሀይ እድሜ ስንት ነው? በሥርዓተ ጸሀይ ውስጥ የሚገኙ ነገሮች ምን ምን ናቸው? የሚሉትና የመሳሰሉት ጥያቄዎችን በመጠየቅ ግንዛቤያቸውን ማረጋገጥ ይጠበቅባቹዋል፡፡

ሁሉም ተማሪዎች ቢያንስ ልደርሱበት የሚገባቸው የብቃት ደረጃ ላይ መድረስ አለባቸው፡፡ የሚጠበቅባቸዉ የመማር ደረጃ ላይ ሊደርሱ ያልቻሉ ተማሪዎችን ከሌሎች ተማሪዎች ጋር ተመሳሳይ ብቃት እንዲኖራቸው የተለየ ድጋፍ ሊደረግላቸው ይገባል፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች የተለየ የትምህርት ክፍለጊዜ በማዘጋጀትና በእረፍት ሰዓታቸው የሚሰሩ ስራ በመስጠት እንዲሰሩ በማገዝ የተለየ ድጋፍ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡

የተሻለ ውጤት ያገኙ ተማሪዎች ባገኙት ውጤት በመኩራራት ወደኂላ እንዳይመልሱ ማበረታታትና መከታተል አስፈላጊ ነው፡፡

## የተግባር 1 መልስ

1. ተማሪዎች ስለ ስርአተፀሀይ ሁኔታ የሚያሳይ ምስል በደብተራቸው ላይ በመስራት የፕላኔቶችን ስም እንድፅፉበት ማድረግ እንዲሁም ስለፕላኔቶች የሚገልፁ ሌሎች መረጃዎችን (ከጸሀይ ያላቸው ርቀት፤ የፕላኔቶች ከፍተኛ የሙቀት መጠናቸው፤ ከባቢ አየርና የመሳሰሉትን) እንድፅፉ ማድረግ፡፡
2. የመሬት ቅርፅ በማንሳት አራቱን አቅጣጫዎች የምድር ወገብና ትልቁ ሜሪድያን በአግባቡ መሰየማቸዉን ማረጋጋጥ፡፡ የትልቁ ሜሪዲያንና የምድር ወገብ ርዝማኔ በተከታታይ 12.640 ኪ.ሜ 12.756 ኪ.ሜ መሆኑንና በሁለቱ መካከል ያለው የርዝመት ልዩነት 116 ኪ.ሜ መሆኑን እንዲረዱና የሁለቱ ርዝመት ተመሳሳይ አለመሆናቸው መሬት ሙሉ በሙሉ ክብ አለመሆኗን በደንብ እንድረዱ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡

## የመልመጃ አንድ መልስ

1. ሥርዐተ ጸሀይ ማለት ፀሀይና በፀሀይ ዙሪያ የሚገኙ ዘጠኙን ፕላኔቶች ያጠቃልላል ። ሥርዓተ ጸሀይ በጠፈር ውስጥ ከሚገኙ አካላት አንዱ ሆኖ ሚልክዌ በሚባለው ጋላክሲ ውስጥ ትገኛለች። ሥርዓተ ጸሀይ ከተፈጠረች 4.6 ቢሊዮን አመታትን አስቆጥራለች ። በሥርዓቱ ውስጥ የራሷ ብርሃን ያላት ትልቁና የሥርዓቱ እምብርት ውስጥ የምትገኝ ጸሀይ ናት። በሥርዓቱ ውስጥ ጸሀይ 99.86 የሚሆነውን ትሸፍናለች ።
2. ፕላኔቶች የሥርዓተ ጸሀይ አካል ሆነው ከጸሀይ በተለያየ አይነት ርቀት ላይ የሚገኙና የማይገናኝ ምህዋር በመከተል ፀሐይን ይዞራሉ። ፕላኔቶች ከጸሀይ ባላቸው ርቀት ከሩቅ ወደ ቅርብ በቅደም ተከተል ፕላቶ፣ ኔፕተዮን፣ ኡራኑስ፣ ሣተር፣ ጁፒተር፣ ማርስ፣ መሬት፣ ቬኑስና ሜርኩሪ ናቸዉ።
3. እኛ የሚንኖርበት ፕላኔት መሬት ናት። ከዘጠኙ ፕላኔቶች መሬት በ3ኛ ደረጃ ላይ የምትገኝ ስትሆን ውሃና ህይወት ያላቸው ነገሮች በውስጡ ይኖራሉ።
4. በድሮ ዘመን ሰዎች መሬት ጠፍጣፋ እንደሆነች ያስቡ ነበር ። ነገር ግን መሬት ጠፍጣፋ እንዳልነበረች የሚያረጋግጡ የተለያዩ መረጃዎች አሉ። ከእነዝህም ውስጥ

   ሀ. ፀሓይ የሚትወጣና የምትጠልቅ መምሰሏ፤

   ለ. የመሬት ጥላ በጨረቃ ላይ መታየቱ፤

   ሐ. ከሰማይ ወደታች የተነሳ የመሬት ፎቶ ክብ መሆኗን ማመልከቱ፤

   መ. ሁለት መርከቦች በውቅያኖስ ላይ ስጓዙ እየተራራቁ ሲሄዱ እርስ፤ በራሳቸዉ አለመተያየታቸው፤

   ሠ. አንድ ሰው ከአንድ ቦታ ተነስተዉ በቀጥታ ወደ ፍት የሚጓዝ ከሆነ ተመልሰው የተነሳበት ቦታ መመለሱና የመሳሰሉት ናቸው።
5. መሬት አንድ ጊዜ ፀሀይን ዞራ ለመጨረስ አንድ አመት ወይም 365 ¼ ቀናት ይወስድበታል። መሬት በፀሀይ ዙሪያ የሚታደርገው አንቅስቃሴ የመሬት በፀሃይ ዙሪያ መዞር ተብለው ይጠራል፡፡ መሬት በፀሀይ ዙሪያ በሚታደርገው እንቅስቃሴ የወቅቶች መፈራረቅና የቀንና የሌሊት ርዝማኔ ልዩነት ይፈጠራል ።

## 1.2 በመሬት ገጽ ላይ የሚገኙና የመሬት ውስጣዊ ክፍሎች

የተሠጠ የክፍለ ጊዜ ብዛት -----------------10

### 1.2.1 በመሬት ገጽ ላይ የሚገኙ ይዘቶች / ሊቶስፌር ፣ ባዮስፌር ፣ ሀይድሮስፌር እና አትሞስፌር /

ተማሪዎች ቢያንስ ልደርሱበት የሚገባቸው የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች የዚህን ርዕስ ትምህርት በኋላ ፦

- አራቱን የመሬት ይዘቶች ፣ሊቶስፌር ፣ ባዮስፌር ፣ ሀይድሮስፌርና አትሞስፌርን ይገልጻሉ፤
- በተለያዩ የመሬት ንብርብሮች ውስጥ የሚገኙ ነገሮች ለምን እንደተለያዩ ይተነትናሉ።

## ዋና ዋና ነጥቦች

ተማሪዎች ባለፈው ርእስ ትምህርት እንደ የስርዓተ ፀሓይ አፈጣጠር የሥርዓተ ፀሀይ ይዘቶች፤ ፕላኔቶች፤ የመሬት አፈጣጠር የመሬት እንቅስቃሴ ዓይነትና የመሳሰሉትን በውስጡ ተምረዋል።

በዚህ ርእስ ደግሞ በመሬት ገጽ ላይ የሚገኙትን ሊቶስፌር በዮስፌር ሀድሮስፌርና አትሞስፌር እንዲሁም በመካከላቸው ያለውን ልዩነት ግንኙነት ይማራሉ። ይህን ርእስ ተማሪዎች በደንብ እንዲገነዘቡና እንዳይረሳ አራቱን ስፌሮች የሚገልጽ ቻርት በምስል መልክ ማዘጋጀት አለባቸው። ከተገኘ የዲጂታል መረጃዎችን በመጠቀም ማስተማር በጣም አስፈላጊ ነው።

## ቅድመ ዝግጅት

የዚህን ርእስ ትምህርት ለማስተማር የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን ለምሳሌ የመሬት ንብርብሮችን የሚያሳይ ስዕል፤ ስፌሮችን የሚያሳይ 4ቱን የመሬት ስፌሮች ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው።

## የመማር ማስተማር ዘዴ

የዚህን ርእስ ትምህርት የተለያየ የመማር ማስተማር ዘዴዎችን በመጠቀም ማስተማር ይቻላል፡፡ ይህን የመማር ማስተማር ዘዴ ተማሪዎች ከሚያውቁት እንዲነሱ የመልመጃ ጥያቄዎች እንደ በመሬት ገጽታ ላይ ከሚገኙት ይዘቶች /ስቶስፌር ፤ባዮስፌር ፤ ሀይድሮስፌርና አትሞስፌር ማለት ምን ማለት እንደሆኑ፤ የከባቢ አየር ንብርብሮች ምንነት፤ በማለት መጠየቅ ይቻላል፡፡ ተማሪዎች የመለሱትን መልስ በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ተማሪዎች በቡድን በማደራጀት አራቱን እስፌሮች፤ የከባቢ አየር ንብርብሮች ላይ በሰፊው እንዲወያዩበት እድል ስጡያቸዉ፡፡ ይህ የቡድን ውይይት በሚያካሄድበት ጊዜ ልያተኮሩባቸው የሚገባ ነጥቦችን በማዘጋጀት መስጠት አስፈላጊ ነው፡፡ እያንዳንዱ ቡድን ከተሰጠው ርእስ እንዳይወጣ ክትትል ልደረግባቸው ይገባል፡፡ የተሰጣቸውን ሰርተው ከጨረሱ በኂላ የተገነዘቡትን ተራ በተራ ለክፍል ተማሪዎች እንዲያቀርቡ አድርጉ፡፡ በመጨረሻ ላይ ተማሪዎች በፊት የነበራቸውን ግንዛቤና ከውይይቱ በኂላ የተገነዘቡትን በማመዛዘን ግብረ መልስ ልሰጣቸዉ ይገባል፡፡

## ተከታታይ ምዘና

ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዱ ለማወቅ ተከታታይ ክትትልና ምዘና ልደረግላቸው ይገባል፡፡ የተማሪዎችን ችሎታ ለመለየት የመልመጃ ጥያቄዎችን አሰሩአቸው፡፡ ለተጠየቁት ጥያቄዎች መልስ መመለሳቸውን በመከታተል ተማሪዎች በርእሱ ላይ የተማሩት ትምህርት የሚፈለገውን ችሎታና እውቀት ላይ መድረሳቸዉን ማረጋገጥ፡፡ የተማሪዎችን እንቅስቃሴ በየጊዜው በመከታተል መመዝገብ አስፈላጊ ነው፡፡ ሁሉም ተማሪዎች ቢያንስ ልደርሱበት የሚገባቸውን የመማር ብቃት ደረጃ ላይ መድረስ አለባቸው፡፡፡ የመማር የብቃት ደረጃ በታች ያገኙትን ተማሪዎች ከሌሎች ተማሪዎች ጋር ተመሳሳይ የብቃት ደረጃ ላይ እንዲደርሱ የተለየ እገዛ ልደረግላቸው ይገባል፤፡፡

## 1.2.2 የመሬት መዋቅሮችና ውጣዊ የመረጃ ምንጮች

የተሠጠ የክፍለ ጊዜ ብዛት ----------------------- 6

ተማሪዎች ቢያንስ ልደርሱበት የሚገባቸው የመማር ብቃቶች ፡

- የመሬት መዋቅሮችን ይለያሉ፤
- የመሬት ንብርብሮችና ይዘትን ያደንቃሉ፤
- የመሬት ንብርብሮችን የሚያሳይ ምስል በመሳል የመሬት መዋቅሮችን ያሳያሉ፤
- የመሬት መዋቅሮችን የመረጃ ምንጮች ይረዳሉ።

## ዋና ዋና ነጥቦች

ባለፉት ትምህርት ርእስ ውስጥ በመሬት ገጽ ላይ የሚገኙ አራቱን ሊቶስፌር፤ባዮስፌር ሀይድሮስፌር ፤አትሞስፌር እንዲሁም በመካከላቸው የሚገኘው ግንኙነት ተምረው ነበር። ተማሪዎች በዚህ ውስጥ ደግሞ ስለመሬት መዋቅሮችና የመረጃ ምንጮቻቸውን በደንብ እንዲረዱና ትምህርቱ ሳይረሳ ለረዥም ጊዜ እንዲቆይ በመፅሐፍ ላይ ያሉ ምስሎችን በትምህርት መርጃ መሳሪያዎች መበልፀግያ ክፍል የሚገኙት ወይም በሞባይል ምስሎችን በማሳየት ማገዝ ነው። በሌላ በኩል ይህ ርእስ በፊዝክስ ትህርት ውስጥም ስለሚገኝ ከፊዚክስ መምህርን ጋር በመወያየት አስፈላጊው ልምድ መውሰድ ተገቢ ነው።

## ቅድመ ዝግጅት

ይህን ርእስ ለማስተማር የመማሪያ መርጃ መሳሪያዎች፤ የመማር ማስተማር ዘዴ፤ ምዘና፤ ሶስቱ የመማር ብቃቶች መግለጫ /ችሎታ፤ እውቀትና አመለካከት / ለማሳካት ይህንን የመምህሩን መምሪያ በመጠቀም ተማሪዎችን ማገዝ ይጠበቅብዎታል።

የዚህን ርእስ ትምህርት ለማስተማር ከመጀመራችዉ በፊት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን፤ ምስሎችና ከተቻለ ትምህርቱን ተጨባጭ ለማድረግ የተቀቀለ እንቁላል ወደ ክፍል በማምጣት የመሬት ንብርብሮችን ለማሳየት መዘጋጀት፤ ተጨማሪ ተመሳሳይ መፅሐፍን በማንበብ ግንዛቤንና የመማር ማስተማር ሁኔታ ማጠናከር ይጠበቅብዎታል።

## የመማር ማስተማር ዘዴ

የዚህን ርእሰ ትምህርት ለማስተማር ከመጀመርዎ በፊት የተማሪዎችን የመመሪያ መፅሐፍ ማንበብና ከሌሎች ምንጮች መረጃዎች ማጠራቀም አስፈላጊ ነው፡፡ ተማሪዎች ከዚህ በፊት ከሚያውቅ ላይ በመነሳት በጥያቄና መልስ አማካይነት የመሬት ውስጣዊ መዋቅሮች ምን እንደሆኑ እንዲመልሱ አድርጉ፡፡ ለምሳሌ የመሬት መዋቅሮችና የመሬት ውስጣዊ መረጃዎች ምን ምን እንደሆነ ተማሪዎችን መጠየቅ ይቻላል፡፡ ለዚህ ርእስ የሚያስፈልጉትን የመማር ማስተማር ዘዴዎችን ይምረጡ ፡፡ በተለይ ሴት ተማሪዎች በንቃት እንዲከታተሉ አበረታቱዋቸው፡፡ የዚህ ትምህርት ይዘት ሁሉን አቀፍ እንዲሆን የተለየ ችሎታ ያላቸው ተማሪዎች፤ ሴት ተማሪዎችና በዝግታ የሚማሩ ተማሪዎችን ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

## የተለየ ስጦታ እና ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎች

የተለየ ችሎታና ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎችን በማገዝ የፈጠራ ችሎታቸውን እንዲያሳድጉ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ውይይቱን በፍጥነት መጨረስ ስለሚችሉ ርእሱን የበለጠ ለማስረዳት የሚያስችል ተጨማሪ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት መስጠት ያስፈልግዎታል፡፡ ነገር ግን እነዚህን የተለየ ችሎታ ያላቸውን ተማሪዎች ለማገዝ ሲዘጋጁ በዝግታ ለሚመሩ ተማሪዎች ተጨማሪ ሥራ በመስጠትና የሚፈለገው ደረጃ ላይ እንዲደርሱ መርዳት ልረሣ የማይገባ ጉዳይ ነው፡፡

## ተከታታይ ምዘና

ተማሪዎች የተማሩትን ተምህርት ምን ያክል እንደተረዱ ለመወቅ ተከታታይነት ያለዉ ክትትል ሊደረግላቸው ይገባል፡፡ የተማሪዎች የትምህርት ችሎታ ለመለየት  የመልመጃ ጥያቄዎች እንደ የመሬት ውስጣዊ መዋቅሮች ምንነት፤ ውስጣዊ የመሬት አፈጣጠር ልዩነትና የመሬት ውስጣዊ ባህሪያት፤ የመሬት ውስጣዊ መዋቅር መረጃ ምንጭና የመሳሰሉትን መለየታቸውን ያረጋግጡ፡፡ ለተጠየቁት ጥያቄዎች መልስ መመለሳቸውን ክትትል በማድረግ በተማሩት ትምህርት ርእስ ላይ የሚፈለገው እውቀትና ችሎታ ማግኘታቸውን ያረጋግጡ፡፡  የተማሪዎችን እንቅስቃሴ በየጊዜው በመከታተል መዝገብ ላይ ያስፍሩ፡፡ ሁሉም ተማሪዎች ቢያንስ ልደርሱበት የሚገባቸውን የብቃት ደረጃ ማግኘት አለባቸው፡፡  የመማር የብቃት ደረጃ በታች ያገኙ ተማሪዎችን በክፍል ውስጥ ከሚገኙ ተማሪዎች ጋር ተመሳሳይ ደረጃ ላይ እንዲደርሱ ተከታታይነት ያለው የተለየ እገዛ ሊደረግላቸው ይገባል፡፡

## የመልመጃ 1:2 መልስ

1. በመሬት ገጽታ ላይ የሚገኙ አራቱ ዋና ዋና ይዘቶች ፦
ሊቶስፌር ሀይድሮስፌር አትሞስፌርና ባዮስፌር
2. ሀይድሮስፌር ውሃማ የመሬት አካል እንደ ባህር፤ ውቅያኖስ፤ ሐይቆች፤ ወንዞችና የመሳሰሉት በውስጡ የያዘ ነው።
3. አራቱ ዋና ዋና የአትሞስፌር ንብርብሮች
ትሮፖስፌር፤ ኢስትራቶስፌር፤ ሜዞስፌርና ቴርሞስፌር ናቸው።
4. ስለ ውስጣዊ የመሬት ሁኔታ መረጃ የሚገኘው በእሣተ ጎመራ ፍንዳታ ምክንያት የሚፈጠረዉ ጉድጋድ ላይ በተደረገው ጥናትና የተለያዩ ማእድናትን ለመፈለግ በማሽኖች በተቆፈሩ ጉድጓዶች ላይ በሚደረገው ጥናት ነው።
5. የመሬት ውስጣዊ መዋቅሮችን ቀለል ባለ መንገድ ለመረዳት የተቀቀለ እንቁላልን በመቁረጥ የእንቁላሉን ቅርፊት ከቅርፍተ መሬት፤ ነጬን የእንቁላሉ ክፍል ከመካከለኛዉ የመሬት ክፍል የእንቁላሉን አስኳል ከእምብረተ መሬት ጋር በመነጻጸር እንዲረዱ ያድርጉ ።

## 1.3 ቅርፊት መሬት የተሠራባቸው ነገሮች

የተሠጠ የክፍለ ጊዜ ብዛት ---------------- 4

**ተማሪዎች ቢያንስ ልደርሱበት የሚገባቸው የመማር ብቃት**

ተማሪዎች ከዚህ ርእስ ትምህርት በኋላ፤

- ቅርፊተ መሬት የተሰራባቸውን ዋና ዋና ኤለመንቶችና ማዕድናት ይለያሉ፤
- የአለቶችን ዓይነትና ምድባቸውን ይለያሉ፤
- የአለቶችን አፈጣጠርና የተፈጠረባቸውን ነገሮች ያደንቃሉ።

## ዋና ዋና ነጥቦች

ባለፉት ትምህርት ውስጥ የመሬት ንብርብሮችና ውስጣዊ የመሬት መረጃዎችን መማራችሁ የሚታወስ ነው። በዚህ ርእስ ስር ቅርፊተ መሬት የተሠራባቸውን ነገሮችና የአለቶችን ምድቦች ይማራሉ። ትምህርቱን በደንብ እንዲገነዘቡና ለረዥም ጊዜ እንዳይረሳ ለማድረግ በመማሪያ መፅሐፍ ላይ ያሉ ስዕሎች፤ በትምህርት መርጃ መሥሪያ መበልፀግያ ማዕከል ያሉ ስዕሎችና

ፎቶዎችን ከኢንተርኔት በማውረድ ማሳየት አስፈላጊ ነው። በሌላ በኩል ይህ ርእስ በኬሚስትሪ ትምህርት ውስጥም ስለሚገኝ ከመምህራን ጋር በመወያየት ልምድ መለዋወጥ አስፈላጊ ነው።

## ቅድመ ዝግጅት

ይህንን ርእስ በማስተማር የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች፣ የመማር ማስተማር ዘዴን፣ ምዘና፣ ሶስቱ የመማር ብቃት ገላጮች /ችሎታ እውቀትና አመለካከትን የመሳሰሉትን በማጠቃለል ማስተማር ያስፈልጋል።

**ማሳሰቢያ፤** ስለ ኤለመንቶችና ማዕድናት ተማሪዎች በኬሚስትሪ ትምህርት ውስጥ በጥልቀት ስለሚማሩ ቅርፊተ መሬት የተሠራባቸዉን 8ቱን ኤለመንቶች ላይ ብቻ ማተኮር አለባችው።

**የመማር ማስተማር ዘዴ**

ተማሪዎች ከሚያውቁት  ላይ እንዲነሱ ትምህርቱን በጥያቄና መልስ መልክ መጀመር ነው። ለምሣሌ ኤለመንቶች፣ማዕድናትና አለቶች ምን እንደሆኑ በኤለመንቶችና ማዕድናት መካከል ያለው ልዩነት ምን እንደሆነ በማለት መጠየቅ ነው። ከዚህ ጥያቄ ተማሪዎች የሚያውቁትን እንዲመልሱ ማበረታታት በተቻለ መጠን ሁሉም ተማሪዎች የመሳተፍ እድል አግኝተው እንዲናገሩ ማድረግ ነው። መልሱን ከተቀበልኳችዉ በኋላ ተማሪዎችን እንደክፍሉ ተጨባጭ ሁኔታ በቡድን በመክፈል ስለ ማዕድናት ኤለመንቶችና አለቶች እንዲወያዩ አድርጉ። ተማሪዎች ውይይት በሚያካሄዱበት ጊዜ የቡድኑ አባላት በሙሉ እኩል መሳተፋቸውን ማረጋገጥ የተሰጣቸውን ከሰሩ በኃለ የተገነዘቡትን ተራ በተራ ለክፍል ተማሪዎች እንዲያቀርቡ አግዙአቸው። በመጨረሻ የማጠቃለያ ሀሳብ በመስጠት በተማሪዎች መከከል ያለዉን ልዩነት በመረዳት በትምህርታቸዉ ተመሳሳይ ግንዛቤ ማግኘት እንድችሉ ማድረግ ያሰፈልጋል። በተጨማርም ትምህርቱን ተጨባጭ ለማድረግ የተለያዩ ፕሮጀክቶችን ማሰራት ይችላሉ።

## የተለያየ የፈጠራ ችሎታና ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎች

እነዚህን ተማሪዎች በማገዝ የፈጠራ ችሎታቸውን  እንዲያዳብሩ ማበረታታት አስፈላጊ ነው። ውይይቱን ቀድመው መጨረስ ስለሚችሉ ርእሱን በይበልጥ ለማስገንዘብ የሚረዱ ተጨማሪ ጥያቄዎችን አዘጋጅተው መስጠት ያስፈልጋል።

ነገር ግን እነዚህን የተለየ ችሎታ ያላቸውን ተማሪዎች ለማገዝ ሲዘጋጁ በዝግታ የሚማሩ በክፍል ውስጥ ያሉ ተማሪዎችን ደግሞ ተጨማሪ ሥራ በመስጠት የሚፈለገው የመማር ብቃት ላይ እንዲደርሱ ማድረግ መረሳት የሌለበት ጉዳይ ነው።

## ተከታታይ ምዘና

ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ትምህርቱን እየተከታተሉ መሆናቸውን ለተጠየቁት ጥያቄዎች መልስ መመለሳቸውን በመከታተል በተማሩት ትምህርት ርእስ ላይ የሚፈለገው ግንዛቤ ማግኘታቸውን ማረጋገጥ ነው፡፡ የትምህርት ውጤታቸውን በየጊዜው በመከታተል መዝገብ ላይ መመዝገብ ነው፡፡

ተመሪዎች ልደርሱበት ከሚገባቸው የትምህርት ደረጃ በታች ያገኑ ተማሪዎችን በክፍል ውስጥ ከሚገኙ ተማሪዎች ጋር ተመሳሳይ ደረጃ ላይ እንዲደርሱ የተለየ እገዛ ያስፈልጋቸዋል ፡፡

ከተማሪዎች ወላጆችና ያንን ክፍል ከሚያስተምሩ ከሌሎች መምህራን ጋር በየጊዜው በመገናኘት በዝግታ የሚማሩ ተማሪዎችን ብቃት ላይ ውይት ማድረግ አለብዎት ፡፡ የተሻለ ውጤት ያገኙ ተማሪዎች ባገኙት ተኩራርተው ወደ ኂላ እንዳይመለሱ ማበረታታትና ክትትል ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡

## የመልመጃ 1፡3 መልስ

1. ኦክስጅንና ሲልከን
2. ማእድናት ማለት ከብዙ ኤለመንቶች ጥርቅም የተሠራ ማለት ነው፡፡
3. ማእድናት እንደ ኳርቲዝ ፤ ወርቅና መደብ የመሳሰሉት ናቸው፡፡
4. ሶስቱ አለቶች ቅልጠት አለት፣ ዝቅጠተ አለትና ለውጥ አለት ናቸው፡፡

| ተ.ቁ | አለቶች | የተፈጠሩበት ሁኔታ | የሚገኙበት ቦታ |
|---|---|---|---|
| 1 | ቅልጠተ አለት | ከእሳተ ጎመራ ፍንዳታ | ከፍተኛ እና መካከለኛ ስምጥ ሸለቆ የመሬት ክፍል |
| 2 | ዝቅጠተ አለት | አንድ ላይ ተጠራቅመው ከጠነከሩት ማሶች | ደቡብ ምስራቅ ዝቅተኛ አዋሽ ወንዝ ሸለቆ መጨረሻ አካባቢ |
| 3 | ለውጥ አለት | በመጠነ ሙቀትና በሙቀት | ምእራብ ወለጋ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ሐረር ከተማ አካበቢ |

## 1.4 የዓለቶች ሥርጭትና በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ውስጥ ያላቸው ጠቀሜታ

የተሰጠ የክፍለ ጊዜ ብዛት----------- 2

**ተማሪዎች ቢያንስ ልደርሱበት የሚገባቸው የመማር ብቃቶች**

ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- የኢትዮጵያ ዓለቶች ሥርጭት ምን እንደሚመስሉ ይገልጻሉ፤
- ካርታን በማየት የዓለቶች ዓይነትና የሚገኙበት ቦታ ያሳያሉ፤
- ዓለቶች በኢኮኖሚ ውስጥ ያላቸውን ጥቅም ምን እንደሆነ ይገልጻሉ፤
- በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ እድገት ውስጥ ዓለቶች ያላቸው ድርሻ ይገልጻሉ።

## ዋና ዋና ነጥቦች

ባለፉት ትምህርት ውስጥ ቅርፊተ መሬት የተሠራባቸውን ነገሮችና የዓለቶችን አይነት መማራቸው ይታወቃል። በዚህ ትምህርት ውስጥ ደግሞ የአለቶች ስርጭትና በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ እድገት ውስጥ ያላቸውን ጠቀሜታ ይማራሉ። ይህንን ትምህርት በደንብ ለማስገንዘብ የዓለቶችን ሥርጭትና ጠቀሜታን የሚያሳይ ካርታና ስዕል ጋር የተያያዙትን ከትምህርት ማበልፀግያ ማእከል በመውሰድ እንዲሁም ስዕሎችን ከኢንተርኔት በማውረድ ሊያሳዩአቸው ይገባል።

## ቅድመ ዝግጅት

ይህንን ርእስ ለማስተማር የትምህርት መርጃ መሣሪያ፤ የመማር ማስተማር ዘዴዎች መገምገም የመማር ብቃት መግለጫዎች ችሎታ፣ እውቀትና አመለካከት የመምህራን መምሪያ በመጠቀም ተማሪዎችን ማገዝ ይጠበቅብዎታል ። የዚህን ትምህርት ርእስ ለማስተማር ከመጀመርዎ በፊት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችና ስዕሎችን በማዘጋጀት ተጨማሪ ተመሳሳይ መፅሐፍትን በማንበብ ግንዛቤንና የተማሪዎችን የመማር ሁኔታን ማጠናከር ይጠበቅብዎታል።

**የመማር ማስተማር ዘዴ**

የባለፈውን ትምህርት ርእስ ስለ ዓለቶች አፈጣጠር ካስታወሱአቸው በኋላ የዓለቶች ስርጭት ምን እንደሚመስልና ጠቀሜታዉ ምን እንደሆነ እንዲሁም ለዚህ ርእስ የሚሆን የመልመጃ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት ጠይቁአቸው ፡፡ ተማሪዎች የሚያውቁትን እንዲናገሩ አግዙአቸው መልስ ከተቀበሉ በኋላ ተማሪዎችን በተለያየ ምድብ/ እንደ የክፍሉ ተጨባጭ ሁኔታ በመክፈል እንዲወያዩ አድርጉአቸው፡፡ የተገነዘቡትን ተራ በተራ ለክፍል ተማሪዎች እንዲያቀርቡ በማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡

## ልዩ ስጦታና ከፍተኛ የሆነ ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎች

የተለየ ችሎታና ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎችን በማገዝ የፈጠራ ችሎታቸውን እንዲያሳድጉ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ውይይቱን በፍጥነት መጨረስ ስለሚችሉ ርእሱን የበለጠ ለመረዳት የሚያስችል ተጨማሪ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት መስጠት ያስፈልጋል፡፡ ነገር ግን እነዚህን ተማሪዎች ለማገዝ ሲዘጋጁ በዝግታ የሚመሩ ተማሪዎች ተጨማሪ ሥራ መስጠትና የሚፈለገው የመማር ብቃት ላይ እንዲደርሱ ማድረግ ልረሳ የማይገባ ጉዳይ ነው፡፡

## ተከታታይ ምዘና

ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዱ ለመወቅ ተከታታይነት ያለዉ ክትትል ሊደረግላቸው ይገባል፡፡ የተማሪዎች የትምህርት ችሎታ ለመለየት  የመልመጃ ጥያቄዎች እንደ የመሬት ውስጣዊ መዋቅሮች ምንነት፤ የመሬት ውስጣዊ መዋቅር መረጃ ምንጭና የመሳሰሉትን መለየታቸውን ያረጋግጡ፡፡ ለተጠየቁት ጥያቄዎች መልስ መመለሳቸውን ክትትል በማድረግ በተማሩት ትምህርት ላይ የሚፈለገው እውቀትና ችሎታ ማግኘታቸውን ያረጋግጡ፡፡ የተማሪዎችን እንቅስቃሴ በየጊዜው በመከታተል በመዝገብ ላይ ያስፍሩ፡፡ ሁሉም ተማሪዎች ቢያንስ ልደርሱበት የሚገባቸውን የመማር ብቃት ማግኘት አለባቸው፡፡  የመማር የብቃት ደረጃ በታች ያገኙ ተማሪዎችን በክፍል ውስጥ ከሚገኙ ተማሪዎች ጋር ተመሳሳይ ደረጃ ላይ እንዲደርሱ የተለየና ተከታታይነት ያለው እገዛ ሊደረግላቸው ይገባል፡፡

### የመልመጃ 1-4 መልስ

1. ሀ. ቅልጠተ አለት ከፍተኛና መካከለኛ የመሬት አቀማመጥ

ለ. ዝቅጠተ አለት ደቡብ ምስራቅና ደቡብ ኢትዮጵያ

ሐ. ለውጥ አለት ቤኒሻንጉል ጉሙዝ አካበቢ ሐረርና መቀሌ ከተማ አካባቢ የመሳሰሉት ናቸው፡፡

2. ቅልጠት አለት

## የምእራፍ 1 የማጠቃለያ መልሶች

ክፍል 1 እውነት /ሀሰት

1. እውነት 2.ሀሰት 3. እውነት 4. እውነት 5.ሀሰት

**ክፍል 2 አዛምድ**

5. ረ 7. ለ 8. ሐ 9. ሀ 10. ሠ 11. መ

**ክፍል 3 ምርጫ**

13. ለ 14. ሀ 15. ሐ 16. ሀ

**ክፍል 4 ባዶ ቦታ**

17. ጁፒተር

18. አንድ /1/ ፕሉቶ

19.በሁለት ይከፈላል፡፡ እነርሱም የየብስ እና የውሃ አካላት ናቸው

20. የአለቶች ኡደት የሚያሳይ ዲያግራም ከተማሪዎች መማሪያ መፅሐፍ እንዲስሉ አድርጉአቸው ፡፡

# ምዕራፍ 2፡ የአለም አፈጣጠርና የሰው ልጅ ዝግመታዊ ለውጥ

**የተሠጠ የክፍለ ጊዜ ብዛት ----------------27**

**የትምህርቱ የመማር ውጤቶች**

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኂላ ተማሪዎች

- የሰው ዘር አመጣጥን ይገልጻሉ፤
- ሰው ልጅ መገኛ ምንጭ የሆነ የአርኪኦሎጂ ጥናት ቦታዎችን ይዘረዝራሉ፤
- አሁን ባለውና በነበረው ሁኔታ ላይ ተንተርሰው የዓለም ህዝብ ቁጥር መጨመርን በተመለከተ የወደፊቱን ሁኔታ ይተነብያሉ፤
- የህዝቦችን አሰፋፈርና ምክንያቶቹን ይለያሉ፤
- የዓለም ህዝብ ቁጥር መጨመር ላይ ተንተርሰው የኢትዮጵያን ህዝብ ቁጥር ይገመግማሉ፤
- የመጓጓዣ የዕድገት ደረጃን ይገልጸሉ፤
- የተለያዩ የመጓጓዣ ዓይነቶችን በመጠቀም ጥቅማቸውንና ድርሻቸውን ይገመግማሉ፤
- በመንገድ ላይ ያሉ የትራፊክ መንገድ ምልክቶች ጠቀሜታ ይለያሉ፡፡

## ዋና ዋና ነጥብ

ተማሪዎች ባለፈው ምዕራፍ ውስጥ ስለሥርዓተ ፀሐይ፣ የመሬት አፈጣጠርና የመሬት ገፅታ ባህርያት ተምረው ነበር፡፡ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ስለ የዓለምና ኢትዮጵያ ህዝብ ይማራሉ፡፡ በዚህ ውስጥ የህዝብ ቁጥር መጨመር፣ የህዝቦች ሥርጭትና የከተሞች መስፋፋትን ይማራሉ፡ ፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ስለመጓጓዣና ዓይነቶቹ፤ የትራፊክ ህግ፤ የመንገድ ደህንነት፤ የትራፊክ አደጋና መንገድን ለማቋረጥ መደረግ የሚገቡ ጥንቃቄዎች ይማራሉ፡፡

## 2.1 የሰዉ ልጅ ዝግመታዊ ለውጥ

የተሠጠ የክፍለ ጊዜ ብዛት -------------------- 5

**ተማሪዎች ልደርሱበት የሚገባቸው የመማር ብቃቶች፤**

- የሰው ልጅ ዝግመታዊ አመጠጥና ታሪካቸውን ይመረምራሉ፤

- በአፍሪካ ቀንድ የቅሪተ አካልየሚገኝባቸዉና የአርኪኦሎጂ ጥናት የሚካሄድባቸውን ቦታዎች ይለያሉ፤
- የሰው ልጅ እስከ ዛሬ ያለፈባቸዉን ውጣ ውረዶችን ይገልጻሉ፡፡

## ዋና ዋና ነጥቦች

በዚህ ውስጥ ተማሪዎች ስለሰው ልጅ ዝግመታዊ ለውጥ፣ የቅሪተ አካል /አርኪኦሎጂ ጥናት፣ የሰው ልጅ መገኛና ያለፈባቸውን ውጣ ውረዶችን ይማራሉ፡፡

## ቅድመ ዝግጅት

የዚህን ትምህርት ርእስ ለማስተማር የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች እንደ ስዕል፤ የሰው ልጅ አመጣጥ ደረጃን የሚያሳይ ቻርትና የመሳሰሉትን ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው፡፡ ክፍል ከመግባትዎ በፊት ይህንን ርእስ በደንብ አንብበው መረዳት አለብዎት ፡፡ በአፍሪካ ቀንድም ሆነ በኢትዮጵያ ደረጃ ብዙ የአርኪኦሎጂ ቦታዎች እንደሉ በደንብ አስተውሉ፡፡ ስለሰው ልጅ አመጣጥ የተለያዩ የማጣቀሻ መፅሐፍን በማንበብ ግንዛቤዎትን ያዳብሩ፡፡ የአፍሪካ ቀንድ የሰው ልጅ መገኛ መሆኑዋን በዚህ አካባቢ የሚገኙ ህዝቦችን የሚያኮራ መሆኑን እንዲያደንቁ ተማሪዎችን ማስገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

## የመማር ማስተማር ዘዴ

ተማሪዎች ከዚህ በፊት ሰምተው የሚያውቁትን ጥንታዊ ቅርሶች እንዲናገሩ በመጠየቅ ትምህርት መጀመር አስፈላጊ ነው፡፡ ተማሪዎች ከተናገሩት ቅርሶች ውስጥ የሰው ልጅ መገኛ ቦታ የሆነው እንዲለዩ አግዙአቸው፡፡ ተማሪዎች የተነገሩትን ስሞች በጥቁር ሠሌዳ ላይ መፃፍ፡፡ እነሱም እንደ አውስትራሎፒትክስ፣ አፋረንስስ፣ /ሉሲና ሆሞሳፒያንስ (ሳላም)፡፡ በተማሪዎች መካከል ያለው ልዩነት እንዲጠብ በቂ መብራሪያ በመስጠት አስተምሩአቸው፡፡ በመቀጠልም የቆይታቸው ሁኔታ ላይ በመወያየት በቅደም ተከተል የቅርጸቻቸዉን እድሜ ተማሪዎች ስማቸውን እንዲጠሩ በማድረግ በጥቁር ሠሌዳ ላይ ጻፉ፡፡ ተማሪዎች ደግሞ በደብተሮቻቸው ላይ ይጻፉ፡፡

## ተከታታይ ምዘና

ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዱ ለመወቅ ተከታታይነት ያለዉ ክትትል ሊደረግላቸው ይገባል፡፡ የተማሪዎች የትምህርት ችሎታ ለመለየት የመልመጃ ጥያቄዎችን በመስጠት ለተጠየቁት ጥያቄዎች መልስ መመለሳቸውን ክትትል በማድረግ፡፡ በተማሩት ትምህርት ርእስ ላይ የሚፈለገው የመማር ችሎታ ላይ መድረሳቸዉን ያረጋግጡ፡፡ የተማሪዎችን እንቅስቃሴ በየጊዜው በመከታተል በመዝገብ ላይ ያስፍሩ፡፡ ሁሉም ተማሪዎች ቢያንስ ልደርሱበት የሚገባቸውን የብቃት ደረጃ ላይ መድረስ አለባቸው፡፡ ልደርሱበት ከሚገባቸው የመማር ብቃት ደረጃ በታች የሆኑ ተማሪዎችን በክፍል ውስጥ ከሚገኙ ተማሪዎች ጋር ተመሳሳይ ደረጃ ላይ እንድደርሱ ተከታታይነት ያለው እገዛ ሊደረግላቸው ይገባል፡፡

**መልመጃ 2.1**

1. የሰው ልጅ አመጣጥ ምንጭ ሁለት መላምቶች አሉ

- በእምነት በኩል
- በሣይንስ በኩል የተገለጸ መላምቶች ናቸው

በእምነት በኩል ሰውን የፈጠረው እግዚአብሄር ነው ይላሉ፡፡ በዚህ ሀሳብ ላይ በሁሉም የእምነት ድርጅቶች ልዩነት የለም፡፡ በሣይንስ በኩል የሰው ልጅ የተገኘው ሚሊዮን አመታትን በፈጀው ዝግመታዊ ለውጥ ነው ብለው ያምናሉ፡፡

2. ሆሚኢድ ⟶ አውስቲራሎፒትክስ. ⟶ ሆሞ ሐቢልስ ⟶ ሆሞ ኤሬክተስ ⟶ ሆሞሳፒያንስ
3. አርክኦሎጂ ይባላል
4. ሆሞ ኤሬክተስ

- ከድንጋይ ነዉ
- መሣሪያውን ለእርድ (ቆዳን ለመግፈፍ) የእንጨት ሥራ ሥሮችን ቆፍረው ለማዉጣት፤ እንጨት ለመቁረጥ ይጠቀሙበት ነበር፡፡

## 2.2. የአለም ህዝብ ሁኔታ

የተሰጠ የክፍለ ጊዜ ብዛት -------------------12

**ተማሪዎች ቢያንስ ልደርሱበት የሚገባቸው የመማር ብቃቶች**

ተማሪዎች የዚህን ርዕስ ትምህርት ከተማሩ በኋላ

- የህዝብ ብዛትን በድሮና የአሁኑ ጊዜን በማነጻጸር ይናገራሉ፤
- የዓለም ህዝብ ቁጥር መጨመር ሁኔታን ይገልጻሉ፤
- በአለም ህዝብ መለወጥ ምክንያት የሚሆኑትን ይዘረዝራሉ፤
- የኢትዮጵያን ህዝብ ስርጭት እና መዋቅራቸውን በማወዳደር ያደንቃሉ፡፡

### ዋና ነጥብ

ባለፈው ትምህርት ውስጥ የሰው ልጅ ዝግመተዊ አመጣጥ ተምራችኋል በዚህ ትህርት ውስጥ ደግሞ ስነህዝብ ይማራሉ፡፡

### ቅድመ ዝግጅት

ይህንን ርዕስ ለማስተማር ከመጀመራችዉ በፊት በደንብ አንብበው መረዳት ያስፈልጋል፡፡ ህዝብ ማለት ተመሳሳይ በህሪ ያላቸዉና በአንድ በተወሰነ ቦታ በጋራ የሚኖሩ መሆናቸዉን እንድገነዘቡ ማድረግ የሰዎች ስብስብ በአንድ ተወሰነ ቦታ ለረጅም ጊዜ የኖሩ መሆኑን ተማሪዎች እንድረዱ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

### የመማር ማስተማር ዘዴ

ስለህዝቦች ተማሪዎች በቀላሉ እንዲረዱ የተለያየ የመማር ማስተማር ዘዴን እንደ ገለጻ፤ ጥያቄና መልስ፤ የውይይት ዘዴ በመጠቀም ስለቤተሰቦቻቸው ጎረቤታቸው ማህበረሰብ እንዲሁም በአካባቢያቸው የሚኖሩ ሰዎች እራሳቸው የህዝቦች አባል እንደሆኑ እንዲያው አግዙአቸው፡፡ እንደዝሁም ስለህዝብ ብዛት ለማስተማር የቤተሰቦቻቸው የጎረቤቶቻቸዉን ብዛት መነሻ በማድረግ የኢትዮጵያንና የዓለምን ህዝብ እንዲገምቱ ሁኔታዎችን አመቻቹላቸው፡፡

## ልዩ ስጦታና ከፍተኛ የሆነ ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎች

የተለየ ችሎታና ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎችን በማገዝ የፈጠራ ችሎታቸውን እንዲያሳድጉ ማድረግ ያስፈልጋል ውይይቱን በፍጥነት መጨረስ ስለሚችሉ ርዕሱን የበለጠ ለመረዳት የሚያስችል ተጨማሪ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት መስጠት ያስፈልጋል፡፡ ነገር ግን እነዚህን የተለየ ችሎታ ያላቸውን ተማሪዎች ለማገዝ ሲዘጋጁ በዝግታ የሚመሩ ተማሪዎች ተጨማሪ ሥራን በመስጠትና የሚፈለገውን የመማር ብቃት ላይ እንዲደርሱ መርዳት ልረሳ የማይገባ ጉዳይ ነው፡፡

## ተከታታይ ምዘና

ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት ምን ያክል እንደተረዱ ለመወቅ ተከታታይነት ያለዉ ክትትል ሊደረግላቸው ይገባል፡፡ የተማሪዎች የትምህርት ችሎታ ለመለየት የመልመጃ ጥያቄዎች እንድሰሩ በማድረግ ምን ያህል እንደተረዱ ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ ለተጠየቁት ጥያቄዎች መልስ መመለሳቸውን ክትትል በማድረግ በተማሩት ትምህርት ርእስ ላይ የሚፈለገው እውቀትና ችሎታ ማግኘታቸውን ያረጋግጡ፡፡ የተማሪዎችን እንቅስቃሴ በየጊዜው በመከታተል በመዝገብ ላይ ያስፍሩ፡፡ ሁሉም ተማሪዎች ቢያንስ ልደርሱበት የሚገባቸዉን የብቃት ደረጃ ላይ መድረስ አለባቸው፡፡ ልደርሱበት ከሚገባቸው የመማር የብቃት ደረጃ በታች ያገኙ ተማሪዎችን በክፍል ውስጥ ከሚገኙ ተማሪዎች ጋር ተመሳሳይ ደረጃ ላይ እንዲደርሱ ተከታታይነት ያለው እገዛ ሊደረግላቸው ይገባል፡፡

### 2.2.1 የህዝብ ቁጥር መጨመር ሁኔታ

የተሠጠ የክፍለ ጊዜ ብዛት----------------4

**ተማሪዎች ቢያንስ ልደርሱበት የሚገባቸው የመማር ብቃቶች**

ተማሪዎች ከዚህ ርዕስ ትምህርት በኋላ

- ለህዝብ ቁጥር መጨመር ምክንያት የሆኑ ነገሮችን ይገልጻሉ፤
- የልደት፣ ሙትና የስደት ሒሳባዊ ሽሌጾችን ይሰራሉ፡፡

## ዋና ዋና ነጥቦች

ባለፉት ትምህርት ውስጥ የህዝቦች ምንነት የዓለም ህዝቦች ብዛት በድሮና በአሁኑ ጊዜ የህዝብ ብዛት መካከል ያለውን ልዩነት ተምረዋል። ተማሪዎች በዚህ የትህርት ርዕስ ውስጥ እንደ የህዝብ ቁጥር መለወጥ፣ ውልደት፣ የውልደት ልኬት ሞት፣ የሞት ልኬት፣ የሀገር ውስጥና የውጭ ስደት እነደዚሁም የልደት ልኬትና የመሳሰሉትን ይማራሉ። ይህን ርእስ ተማሪዎች በደንብ እንድገነዘቡና ለረጅም ጊዜ እንዳይረሱ የተለያየ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ማለትም የህዝብ ብዛት የሚያሳይ ሠንጠረዥ ማዘጋጀት አለብዎት። ትምህርቱ ተጨባጭ እንደሆን ኢንተርኔት፣ የተለያዩ መፅሐፍና ሌሎች ከርዕሱ ጋር ተያያዥነት ያላቸዉን በማንበብ ለማስተማር መዘጋጀት ያስፈልጋል።

## ቅድመ ዝግጅት

ህዝብ ተጠጋግተዉና ህዝብ ተበታትነው የሚኖሩበትን አከባቢ የህዝብ መጨመር፣ ውልደት፣ ሞትና ስደት የሚያሳይ ሠንጠረዥና ካርታን ያዘጋጁ። ለማስተማር ክፍል ከመግባትዎ በፊት በህዝብ ብዛት ላይ የሚያተኩሩ የተለያዩ መፅሐፍን በማንበብ ይዘጋጁ። ጥያቄዎችን በመማሪያ መፅሐፍ ላይ ያለዉን መልመጃ ቀድመው በመስራት ይዘጋጁ።

## የመማር ማስተማር ዘዴ

ስለ ህዝቦች ቁጥር መጨመር ተማሪዎች ከሚያዉቁት ላይ ተነስተው እንዲናገሩ ይጠይቁ። ከመለሱ በኋላ በመለማመጃ ጥያቄ ላይ ውይይት እንዲያደርጉ ሁኔታውን አመቻቹላቸው ። ለምሳሌ ተማሪዎች በሀ እና ለ ምድብ በመክፈል የሀ ምድብ በተፈጥሮ የሰው ቁጥርን የማይቀየሩ ነገሮች እና ለ ምድብ ደግሞ የህዝብ ቁጥርን የሚጨምሩ ነገሮች በሚል ርእስ ስር ውይይት ካደረጉ በኋላ ለክፍል ተማሪዎች እንዲያቀርቡ ማድረግ የተማሪዎች ግንዛቤ እንዲጨምር ያደርጋል።

ከውይይቱ አዲስ ነገር ማግኘታቸውን አስተያየት እንድሰጡ ማድረግ በመጨረሻ ላይ ተማሪዎች ግንዛቤ እንዲያገኙ የህዝቦች ቁጥር መጨመር ህሳባዊ ስሌት እንዴት እንደሆነና እንደሚሰላ ለምን ያህል እንደሚጨምር ወይም እንደሚቀንስ እንዲያጠኑ ለማድረግ ምክሩ። ይህ በሚከናወንበት ጊዜ ተማሪዎ ምን እንደተጠየቁና እንዴት እንደምሰላ ትክክለኛውን የሂሣብ

ስሌት እንዲለዩ አግዙአቸው። በመከተልም አራቱን መሠረታዊ የህሳብ ስሌቶችን በመጠቀም እንዲሰሩ አግዙአቸው። በመጨረሻም ተማሪዎች በራሳቸው የተሰጣቸውን ጥያቄዎች የሚፈለገውና ትክክለኛውን ፎርሙላ ተጠቅሞ መስራታቸውን ያረጋግጡ። የክፍልና የቤት ሥራን ሰጥተው መስላት እንዲችሉ አበረታቱአቸው።

## ልዩ ስጦታ እና ከፍተኛ የሆነ ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎች

የተለየ ችሎታና ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎችን በማገዝ የፈጠራ ችሎታቸውን እንዲያሳድጉ ማድረግ ያስፈልጋል። ውይይቱን ቀድመዉ መጨረስ ስለሚችሉ ርእሱን የበለጠ ለመረዳት የሚያስችል ተጨማሪ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት መስጠት ያስፈልጋል። ነገር ግን እነዚህን ተማሪዎች ለማገዝ ሲዘጋጁ በዝግታ የሚመሩ ተማሪዎች ተጨማሪ ሥራ በመስጠትና የሚፈለገው የመማር ብቃት ላይ እንዲደርሱ መርዳት ልረሳ የማይገባ ጉዳይ ነው።

## ተከታታይ ምዘና

መምህራን የተማሪዎችን ተሣትፎ ለመለየት መስታወሻ እየያዙ መሄድ ያስፈልጋል፡፡ በየቀኑ ተሣትፎአቸውን እየመዘገቡ በመሄድ እያንዳንዱን ተማሪ መገምገም ይችላሉ። ተማሪዎች በክፍል ውስጥ እየተሳተፉ መሆናቸውን ለተጠየቁት ጥያቄዎች መልስ መመለሳቸውን፤ የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠቀም መለካት መቻላቸውን በመከታተል የሚፈለገውን ግንዛቤና ችሎታ ማግኘታቸውን ያረጋግጡ።

## 2.2.1. የህዝብ ቁጥር መጨመር

የተሠጠ ክፍለ ጊዜ ብዛት -------------- 4

**ተማሪዎች ቢያንስ ልደርሱበት የሚገባቸው የመማር ብቃቶች**

**ተማሪዎች የዚህ ምእራፍ ትህርት ተምረው ከጨረሱ በኋላ**

- የህዝቦች መዋቅር ምንነት ይገልፃሉ።
- የህዝብ መዋቅር ከሀገሪቷ ኢኮኖሚ ጋር ያለውን ግንኙነት ምን እንደሆነ ይገልጻሉ።
- የጥገኝነት ምንነትን ይገልፃሉ።

## ዋና ዋና ነጥብ

በዚህ ትምህርት ዋና ዋና ነጥቦች እንደ የህዝብ ቁጥር መለወጥ ባህርይ፣ የህዝብ መዋቅር፣ ህዝብ በማህበረሰብ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ያለው ድርሻ፣ ጥገኝነትና የጾታ ወደር/Ratio ምን እንደሆነ ይማሩታል፡፡

## ቅድመ ዝግጅት

መምህራን ለማስተማር ክፍል ከመግባትዎ በፊት በህዝብ ብዛት ላይ የተጻፉ የተለያዩ የማጣቀሻ መፅሀፍን በማንበብ፣ በቂ ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ተማሪዎች የተሰጡ መልመጃዎችን እንድሰሩ ማድረግ አለብዎት፡፡ ተጨማሪ የማመዛዘኛ ጥያቄዎች ለተማሪዎች መስጠት አስፈላጊ በመሆኑ አዘግጅተው ክፍል መግባት ይጠበቅቦታል፡፡ የተለያዩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችና የህዝብ የዕድሜ ስርጭት የሚያሳይ ፒራምድ መጠቀም ይጠበቅብዎታል፡፡

## የመማር ማስተማር ዘዴ

ተማሪዎች ከሚያውቁት እንድነሱ ለማድረግ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት  በክፍል ውስጥ ይጠይቁ፡፡ ተማሪዎች የነገሩአችሁን መልስ በጥቁር ሰላዳ ላይ መፃፍ፡፡ ለውይይት እንድያመች ተማሪዎቹን በተለያየ ምድብ በመመደብ የተለያዩ የህዝብ ፒራሚድ ይስጡአቸው፡፡ ለምሳሌ በማደግ ላይ ያሉና ያደጉ ሀገሮች የሚያሳይ የህዝብ መዋቅር የሚያሳይ ሰንጠረዥ ተማሪዎች ሰርተዉ ለክፍል  እንዲያቀርቡ ማድረግ ግንዛቤአቸውን መገምገም ያስችላል፡፡ በመቀጠልም የህዝብ መዋቅርና ምርታማነትም ከሰዎች እድሜ ጋር ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት እንዳለው  እንዲያውቁ አጭር መግለጫ ስጡአቸው፡፡

ግንዛቤአቸውን ይበልጥ ለማሳደግ የሚያስፈልገውን መለኪያ እንዲገነዘቡ ምሳሌ በመውሰድ በመስራት አሳዩአቸው፡፡ ተማሪዎችም እንዲሰሩ የክፍልና የቤት ሥራን መለኪያ ባለው ሁኔታ መስጠት ያስፈልጋል፡፡

## የተለየ ስጦታና ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎች

የተለየ ችሎታና ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎችን በማገዝ የፈጠራ ችሎታቸውን እንዲያሳድጉ ማድረግ ያስፈልጋል ውይይቱን በፍጥነት መጨረስ ስለሚችሉ ርእሱን የበለጠ ለመረዳት የሚያስችል ተጨማሪ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት መስጠት ያስፈልግዎታል፡፡ ነገር ግን እነዚህን ተማሪዎች ለማገዝ ሲዘጋጁ በክፍል ውስጥ ያሉ በዝግታ የሚመሩ ተማሪዎች ተጨማሪ ሥራ መስጠትና የሚፈለገው የመማር ብቃት ላይ እንዲደርሱ መርዳት ልረሳ የማይገባ ጉዳይ ነው፡፡

## ተከታታይ ምዘና

ተማሪዎች የተማሩትን ተምህርት ምን ያክል እንደተረዱ ለመወቅ ተከታታይነት ያለዉ ክትትል ሊደረግላቸው ይገባል፡፡ የተማሪዎች የትምህርት ችሎታ ለመለየት  የመልመጃ ጥያቄዎች እንደ የመሬት ውስጣዊ መዋቅሮች ምንነት ውስጣዊ የመሬት አፈጣጠር ልዩነትና የውስጣዊ ክፍፍል ባህሪይ ፤የመሬት ውስጣዊ መዋቅር መረጃ ምንጭና የመሳሰሉትን መለየታቸው ያረጋግጡ፡፡ ለተጠየቁት ጥያቄዎች መልስ መመለሳቸውን ክትትል በማድረግ በተማሩት ትምህርት ርእስ ላይ የሚፈለገው እውቀትና ችሎታ ማግኘታቸውን ያረጋግጡ፡፡  የተማሪዎችን እንቅስቃሴ በየጊዜው በመከታተል በማስታወሽ መዝገብ ላይ ያስፍሩ፡፡ ሁሉም ተማሪዎች ብያንስ ልደርሱበት የሚገባቸውን የብቃት ደረጃ ማግኘት አለባቸው፡፡ ልደርሱበት ከሚገባቸው የመማር ብቃት በታች ያገኙ ተማሪዎችን በክፍል ውስጥ ከሚገኙ ተማሪዎች ጋር ተመሳሳይ ደረጃ ላይ እንዲደርሱ የተለየና ተከታታይነት ያለው እገዛ ሊደረግላቸው ይገባል፡፡

### 2.2.2 የህዝብ ሥርጭት

**የተሠጠ የክፍለ ጊዜ ብዛት ---------2**

**ተማሪዎች ቢያስ ልደርሱበት የሚገባቸው የመማር ብቃቶች፣**

ተማሪዎች የዚህን ርዕስ ትምህርት ተምረው ከጨረሱ በኂላ

- የህዝብ ሥርጭትን የሚወስኑ ነገሮችን ለይተው ይገልጻሉ
- የአለም ህዝብ ብዛት ተጠጋግተዉ የሚገኙባቸዉን  ቦታዎች ይገልፃሉ
- የህዝብ ሥርጭትን የሚቆጣጠሩ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ነገሮችን ያደንቃሉ፡፡

## ዋና ዋና ነጥቦች

ባለፉት ትምህርት ውስጥ የህዝብ ቁጥር መለወጥ ባህር፣ የህዝብ መዋቅር፣ ህዝቦች በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ውስጥ ያላቸውን ድርሻ፣ ጥገኝነትና የጾታ ወደር/Ratio ተምሩዋል። በዚህ ርእስ ስር የህዝብ ሥርጭት፣ ጥገኝነትና የህዝብን ስርጭት የሚወሰኑ ነገሮችና የመሳሰሉትን ይማሩታል። ይህንን ርእሰ ተማሪዎች በደንብ እንድገነዘቡና ለረጅም ጊዜ ሳይረሳ እንዲቆይ የህዝብን ሥርጭት የሚያሳይ ካርታ ማዘጋጀት ያስፈልግዎታ። ይህንን ርእስ ይበልጥ ተጨባጭ ለማድረግ ከእንተርኔትና ከተለያዩ መፃህፍት በማንበብ በአግባቡ ለማስተማር መዘጋጀት ይጠበቅብዎታል።

## ቅድመ ዝግጅት

ተማሪዎችን ለማስተማር ክፍል ከመግባትዎ በፊት በህዝብ ብዛት ላይ የተጻፉ የተለያዩ መጻህፍተን በማንበብ የተለያየ በቂ መረጃን መሰብሰብ። በተማሪዎች መማሪያመፅሐፍ ላይ ያለዉን ጥያቄዎችና መልመጃ ውስጥ የሚገኙትን ለተማሪዎች በመስጠትና በማዘጋጀት ክፍል መግባት ይጠበቅብዎታል። የአለም ህዝብ ብዛትና የመሬት አቀማመጥን የሚያሳይ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ማዘጋጀት ያስፈልጋል።

## የመማር ማስተማርዘዴ

ይህንን ርእስ የተለያዩ የመማር ማስተማር ዘዴዎን በመጠቀም ማስተማር ይቻላል፡፡ ከእነዝህም ውስጥ ጥያቄና መልስ፣ በውይይት፣ በማሳየት፣ ፕሮጅክት በማሰራትና የመሳሰሉትን የማስተማሪያ ዘዴዎችን መጠቀም ናቸው። በዚህ ርስ ውስጥ ዋናው ነጥብ የህዝቦች ስርጭት ህዝቦች በብዛት የሚኖሩበት ቦታ ወይም ተበታትነው የሚኖሩበት ቦታዎች፤ የህዝብን ስርጭት የሚወስኑ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ነገሮች ናቸው። ተማሪዎችም በራሳቸው እንድሰሩ የቤትና የክፍል ሥራ ስጡአቸው ። በተጨማሪም የህዝብ ቁጥር ከሚያሳይ ፐራሚድ ተመልክተዉ የህዝብ መዋቅርና የህዝብ ግንኙነት ቀለል ባለ መንገድ እንድረዱ ማድረግ ይሞክሩ።

## ልዩ ስጦታና ከፍተኛ የሆነ ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎች

የተለየ ችሎታና ከፍ ያለ ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎችን በማገዝ የፈጠራ ችሎታቸውን እንዲያሳድጉ ማድረግ ያስፈልጋል ውይይቱን በፍጥነት መጨረስ ስለሚችሉ ርእሱን የበለጠ ለመረዳት የሚያስችል ተጨማሪ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት መስጠት ያስፈልግዎታል። ነገር ግን እነዚህን የተለየ ችሎታ ያላቸውን ተማሪዎች ለማገዝ ሲዘጋጁ በዝግታ የሚመሩ ተማሪዎች ተጨማሪ ሥራ በመስጠትና የሚፈለገው የመማር ብቃት ላይ እንዲደርሱ መርዳት ልረሳ የማይገባ ጉዳይ ነው።

## ተከታታይ ምዘና

ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዱ ለመወቅ ተከታታይነት ያለዉ ክትትል ሊደረግላቸው ይገባል። የተማሪዎች የትምህርት ችሎታ ለመለየት  የመልመጃ ጥያቄዎች እንደ የመሬት ውስጣዊ መዋቅሮች ምንነት ውስጣዊ የመሬት አፈጣጠር ልዩነትና የውስጣዊ ክፍፍል ፀባይ ፤የመሬት ውስጣዊ መዋቅር መረጃ ምንጭና የመሳሰሉትን መለየታቸው ያረጋግጡ። ለተጠየቁት ጥያቄዎች መልስ መመለሳቸውን ክትትል በማድረግ በተማሩት ትምህርት ርእስ ላይ የሚፈለገው እውቀትና ችሎታ ማግኘታቸዉን  ያረጋግጡ።  የተማሪዎችን እንቅስቃሴ በየጊዜው በመከታተል በመዝገብ ላይ ያስፍሩ። ሁሉም ተማሪዎች ብያንስ ልደርሱበት የሚገባቸውን የብቃት ደረጃ ማግኘት አለባቸው። ልደርሱበት የሚገባቸው የመማር ደረጃ በታች ያገኙ ተማሪዎችን በክፍል ውስጥ ከሚገኙ ተማሪዎች ጋር ተመሳሳይ ደረጃ ላይ እንዲደርሱ የተለየና ተከታታይነት ያለው እገዛ ሊደረግላቸው ይገባል።

## 2.2.4 ስደትና የህዝብ አሰፋፈር /በሀገር ውስጥና ከሀገር ውጪ

የተሠጠ የክፍለ ጊዜ ብዛት ------------2

### ተማሪዎች ብያንስ ልደርሱበት የሚገባቸው የመማር ብቃት

ተማሪዎች የዚህን ምእራፍ ትምህርት ተምረው ከጨረሱ በኋላ ፡-

- የስደት ዓይነቶችን ይለያሉ።
- ስደት በከተማና በገጠር ያለዉ ልዩነት ምን እንደሆነ ይገልጻሉ

## ዋና ዋና ነጥቦች

ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ሰለህዝብ ሥርጭት የህዝቦች ጥግጋትና የህዝብ ስርጭትን የሚቆጣጠሩ ነገሮችን ተምረዋል። በዚህ ርእስ ስር የስደት ምንነትና ስደት በከተማና በገጠር ምን እንደሚመስል፤ የከተሞች መስፋፋትንና የኢትዮጵያ ህዝቦች ይማራሉ። ተማሪዎች ይህንን ርእስ በደንብ እንዲገነዘቡና ለረጅም ግዜ እንዳይረሳ ለማድረግ የህዝብን ስርጭት የሚያሳይ ካርታ ማዘጋጀት ይጠበቅብዎታል። ርእሱን የበለጠ ተጨባጭ ለማድረግ ኢንተርኔት፣ ሌሎች የተለያዩ መፅሓፍትና ሌሎቾ መረጃዎችን በማንበብ በአግባቡ ለማስተማር መዘጋጀት ይጠበቅብዎታል።

## ቅድመ ዝግጅት

ለማስተማር ክፍል ከመግባተዎ በፊት ስለስደትና የህዝብ አሰፋፈር የተጻፉ መፃህፍትን በማንበብ ይዘጋጁ። የህዝቦች አሰፋፈርን የሚያሳይ የኢትዮጵያ ካ ርታ ቻርት ወይም ጋራፍ ያዘጋጁ ።

## የመማር ማስተማር ዘዴ

የባለፈውን ትምህርት ሰለህዝብ ሥርጭት ተማሪዎች ካስተወሱአቸው በኂላ ስደትና የህዝቦች አሰፋፈርን በተመለከተ ተማሪዎች ምን ያህል እንደሚያውቁ ለመረዳት የተለያዩ የመልመጃ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት ይጠይቁ። ተማሪዎች የሚያውቁትን እንዲናገሩ አግዙአቸው። መልሱን ከተቀበሉአቸው በኂላ ተማሪዎችን በተለያየ ምድብ እንደ እየክፍሉ ተጨባጭ ሁኔታ በመክፈል እንዲወያዩበት አድርጉአቸው ለተወሰነ ቡድን የህዝቦችን ስርጭት፣ የህዝቦች አሰፋፈር በከተማና በገጠር ላይ እንዲወያዩ አድርጉአቸው። ለምሳሌ አንድ ቡድን ስለገጠር ህዝቦች ሌላው ደግሞ በከተማ ህዝቦች ላይ በመወያት ልዩነታቸው ለክፍል እንዲያቀርቡ በማድረግ ግንዛቤአቸውን ይገምግሙ። የተገነዘቡትን ታራ በተራ ለክፍል ተማሪዎች እንዲያቀርቡ አድርጉአቸው።

## ልዩ ስጦታና ከፍተኛ የሆነ ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎች

የተለየ ችሎታና ከፍ ያለ ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎችን በማገዝ የፈጠራ ችሎታቸውን እንዲያሳድጉ ማድረግ ያስፈልጋል ውይይቱን በፍጥነት መጨረስ ስለሚችሉ ርእሱን የበለጠ ለመረዳት የሚያስችል ተጨማሪ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት መስጠት ያስፈልጋል። ነገር ግን

እነዚህን የተለየ ችሎታ ያላቸውን ተማሪዎች ለማገዝ ሲዘጋጁ በዝግታ የሚመሩ ተማሪዎች ተጨማሪ ሥራ መስጠትና የሚፈለገው የመማር ብቃት ላይ እንዲደርሱ መርዳት ልረሳ የማይገባ ጉዳይ ነው፡፡

## ተከታታይ ምዘና

ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዱ ለማወቅ ተከታታይነት ያለዉ ክትትል ሊደረግላቸው ይገባል፡፡ የተማሪዎችን የትምህርት ችሎታ ለመለየት  የመልመጃ ጥያቄዎች እንደ የስደት ምንነት፣ የህዝቦች አሰፋፈር በከተማና በገጠር ያለዉ ልዩነትና የመሳሰሉትን መለየታቸው ያረጋግጡ፡፡ ለተጠየቁት ጥያቄዎች መልስ መመለሳቸውን ክትትል በማድረግ በተማሩት ትምህርት ርእስ ላይ የሚፈለገው እውቀትና ችሎታ ማግኘታቸዉን ያረጋግጡ፡፡ የተማሪዎችን እንቅስቃሴ በየጊዜው በመከታተል በመዝገብ ላይ ያስፍሩ፡፡ ሁሉም ተማሪዎች ብያንስ ልደርሱበት የሚገባቸውን የብቃት ደረጃ ማግኘት አለባቸው፡፡ ልደርሱበት ከሚገባቸው የመማር የብቃት በታች ያገኙ ተማሪዎችን በክፍል ውስጥ ከሚገኙ ተማሪዎች ጋር ተመሳሳይ ደረጃ ላይ እንዲደርሱ የተለየና ተከታታይነት ያለው እገዛ ሊደረግላቸው ይገባል፡፡

## የመልመጃ 2.2 መልስ

1. የአለም ህዝብ የእርሻ ስራን ስጀምሩና በቋሚነት አንድ ቦታ መኖር በጀመሩበት ጊዜ በብዛት የሰው ልጅ መሰረታዊ ፍላጎቶች እንድ ምግብ፤ ልብስና በመጠለያ በበቂ ሁኔታ ከማግኘታቸው የተነሳ የሰው ልጆች ቁጥር መጨመር ምክንያት ሆኑዋል፡፡
2. ኢስያ አውሮፓና አፍሪካ
3. የእድሜ ፒራሚድን በቀላል መንገድ የሰዎችን የእድሜ ክልል ለመሳየት ያግዛል፡፡ የእድሜ ፒራሚድ ሁለት ግራፍ ያለውና በጀርባ የተገናኘ ሆኖ ወንዶችን በግራ ሴቶችን ደግሞ በቀኝ በኩል የሚያሳይ ነው፡፡ በተጨማሪም እድሜን የሚያሳይ ሆኖ በዘርፍ ላይ የህዝብ ብዛትን ያሳያል፡፡
4. የህዝቦች ስደት ሰዎች ለአጭር ጊዜ ወይም ለረጅም ጊዜ በፊት ከነበሩት ቦታ ለቀዉ ወደሌላ ቦታ መሄድ ሲሆን በተፈጥሮ የሚከሰት ስደት / በድርቅ፣ በጎርፍ፣ በእሳት / ወይም በሰዎች /በመጣላት፣ በሰፈራ /በሀገር ውስጥ፣ ከሀገር ውጪ መሰደድ ነው፡፡
5. /67, 4 4 0

6. 122
7. 75
8. 200 ኪ.ሜ

## 2.3. መጓጓዣ እድገት ፅንሰ ሀሳብ

**የተሠጠ የክፍለ ጊዜ ብዛት -----------10**

2.3.1 የመጓጓዣ እድገት ጽንሰ ሀሳብ -----------------1 ክፍለ ጊዜ

2.3.2 መጓጓዣ በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት ውስጥ ያለው ሚና---- 2 ክፍለ ጊዜ

### ተማሪዎች ቢያንስ ልደርሱበት የሚገባቸው የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች የዚህን ርዕስ ትምህርት ተምረው ከጨረሱ በኂላ

- የመጓጓዣ ምንነትና ዓይነትን ይገልጻሉ
- የመጓጓዣ የእድገት ደረጃን ይገልጻሉ
- መጓጓዣ በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት ውስጥ ያለውን ሚና ይናገራሉ፡፡

### ዋና ዋና ነጥብ

ባለፈው ትህርት ውስጥ የሰዎች ስደት የከተሞች መስፋፋትና የህዝብ አሰፋፈር ተምረው ነበር፡፡ በዚህ ርእስ ስር ስለመጓጓዣ፣ የመጓጓዣ ዓይነቶች የመጓጓዝ እድገትና ጠቀሜታው፣ በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ውስጥ ያለው ሚናና የመሳሰሉትን ይማራሉ፡፡ ይህንን ርእስ ለተማሪዎች ተጨባጭ ለማድረግ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን እንደ የመጓጓዣ ዓይነቶች(ባህላዊና ዘመናዊ የመጓጓዣ ዓይነቶችን የሚያሳይ ስዕል አሳዩአቸው፡፡

### ቅድመ ዝግጅት

መምህራን ክፍል ከመግባታቸው በፊት ይህንን ርእስ አስመልክተው የተለያዩ መፅሐፍትን በማንበብ ራሳቸውን ማዘጋጀት አለባቸው፡፡ የተለያዩ የመጓጓዣ ዓይነቶችን የሚያሳዩ ስዕሎችን በማዘጋጀት ክፍል ሲገቡ ተማሪዎች ማየት በሚችበት ቦታ ላይ ማስቀመጥ አስፈላጊ ነዉ፡፡

## የመማር ማስተማር ዘዴ

የዚህን ትምህርት ርእስ የተለያየ ዘዴዎችን በመጠቀም ማስተማር ይቻላል፡፡ በዚህ ትህርት ውስጥ ተማሪዎች ከሚያውቁት በመነሳት የተለያዩ ጥያቄዎችን እንደ መጓጓዣ ምንድን ነው፧ በአካባቢያችሁ ሰዎች በመጓጓዣ ምን ምን ይጠቀማል፧ የመጓጓዣ እድገት ማለት ምን ማለት ነው፧ መጓጓዣ በኢኮኖሚ እድገት ውስጥ ያለው ድርሻ ግለጽ፧ በማለት ጠይቁአቸው፧፧ ተማሪዎች የሰጡትን መልስ በጥቁር ሰሌዳ ላይ ይጻፉ፡፡ መልሱን ከተቀበላችው በኂላ ተማሪዎቸን በቡድን በመክፈል የመጓጓዣ ምንነት፣ የመጓጓዣ ዓይነት፣ መጓጓዣ በኢኮኖሚ እድገት ውስጥ ያለው ሚናና በመሳሰሉት ላይ በስፋት እንዲወያዩ እድል ስጡአቸው፡፡

ተማሪዎች ውይይት በሚያደርጉበት ወቅት ሊያተኩሩበት የሚገባቸው ነጥቦች በጽሁፍ ይስጡአቸው፡፡ እያንዳንዱ ምድብ በተሰጠው ርእስ ላይ እንድያተክሩ ተከታተሉአቸው፡፡ የተሰጣቸውን ሰርተው ከጨረሱ በኂላ ከተገነዘቡት ውስጥ ተራ በተራ ለክፍል ተማሪዎች እንድያቀርቡ ዕድል ስጡአቸው፡፡ በመጨረሻ የማጠቃለያ ሀሳብና ግብረ መልስ ይሰጣቸው፡፡

## ልዩ ስጦታና ከፍተኛ የሆነ ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎች

የተለየ ችሎታና ከፍ ያለ ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎችን በማገዝ የፈጠራ ችሎታቸውን እንዲያሳድጉ ማድረግ ያስፈልጋል ውይይቱን በፍጥነት መጨረስ ስለሚችሉ ርእሱን የበለጠ ለመረዳት የሚያስችል ተጨማሪ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት መስጠት ያስፈልጋል፡፡ ነገር ግን እነዚህን የተለየ ችሎታ ያላቸውን ተማሪዎች ለማገዝ ሲዘጋጁ በዝግታ የሚመሩ ተማሪዎች ተጨማሪ ሥራ መስጠትና የሚፈለገው የመማር ብቃት ላይ እንዲደርሱ መርዳት ልረሳ የማይገባ ጉዳይ ነው፡፡

## ተከታታይ ምዘና

ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዱ ለመወቅ ተከታታይነት ያለዉ ክትትል ሊደረግላቸው ይገባል፡፡ የተማሪዎች የትምህርት ችሎታ ለመለየት  የመልመጃ ጥያቄዎች እንደ መጓጓዣ ምንድን ነው፧ በአካባቢያችሁ ሰዎች በመጓጓዣ ምን ምን ይጠቀማል፧ የመጓጓዣ እድገት ማለት ምን ማለት ነው፧ መጓጓዣ በኢኮኖሚ እድገት ውስጥ ያለው ድርሻ ግለጽና የመሳሰሉትን በመጠየቅ መለየታቸውን ያረጋግጡ፡፡ ለተጠየቁት ጥያቄዎች መልስ

መመለሳቸውን ክትትል በማድረግ በተማሩት ትምህርት ርእስ ላይ የሚፈለገው እውቀትና ችሎታ ላ መድረሳቸዉን ያረጋግጡ፡፡ የተማሪዎችን እንቅስቃሴ በየጊዜው በመከታተል በማጠቃለያ መዝገብ ላይ ያስፍሩ፡፡ ሁሉም ተማሪዎች ብያንስ ልደርሱበት የሚገባቸውን የብቃት ደረጃ ማግኘት አለባቸው፡፡ ልደርሱበት ከሚገባቸው የመማር የብቃት ደረጃ በታች ያገኙ ተማሪዎችን በክፍል ውስጥ ከሚገኙ ተማሪዎች ጋር ተመሳሳይ ደረጃ ላይ እንዲደርሱ የተለየና ተከታታይነት ያለው እገዛ ሊደረግላቸው ይገባል፡፡

## 2.3.3 የመጓጓዣ አይነቶች

**የተሠጠ የክፍለ ጊዜ ብዛት ----------3**

## 2.2.5 የመንገድ ደህንነት የትራፊክ አደጋና በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ላይ የሚያደርሰው ጉዳት

**የክፍለ ጊዜ ብዛት--------------4**

### ተማሪዎች ብያንስ ልደርሱበት የሚገባቸው የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች የዚህን ትህርት ርዕስ ተምረው ከጨረሱ በኂላ ፡-

- የተለያዩ የመጓጓዣ አይነትና ጥቅማቸው ይዘረዝራሉ፡፡
- የተለያዩ የመጓጓዣ ዓይነቶችና ጥቅማቸን በማመዛዘን ይገልጻሉ
- በመንገድ ላይ ያሉ የትራፊክ ምልክቶች ጥቅም ይለያሉ
- መሠረታዊ የሆነ የትራፊክ ደንቦችን ይገልጻሉ፡፡

## ዋና ዋና ነጥቦች

ተማሪዎችባለፈው ትምህርት ውስጥ ስለስደትና የህዝቦች አሰፋፈር ተምረው ነበር፡፡ በዚህ ርእስ ስር ስለመንገድ ደህንነት፣ የትራፊክ አደጋ፣ የትራፊክ አደጋ በኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ላይ ያለውን ሰፊ ችግር፣ ስለመጓጓዣ፣ የመጓጓዣ ጥቅሞችና በኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ውስጥ ያለውን ድርሻና የመሳሰሉትን ይማራሉ፡፡ የዚህን ርዕስ ትምህርት ተጨባጭ ለማድረግ የተለያዩ

የትምህርት መረጃ መሣሪያዎችን፣ የትራፊክ መብት ምልክቶች ስዕልና የመሳሰሉትን ማዘጋጀት ይጠበቅብዎታ፡፡

## ቅድመ ዝግጅት

የዚህን ርእስ ትምህርት ለማስተማር ክፍል ከመግባታችሁ በፊት ከዚህ ርእስ ጋር የሚመሳሰል የተለያዩ መፅሀፍትን በማንበብ ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው፡፡ የትራፊክ ምልክቶችን የሚገለጽ ስዕል የትራፊክ መብራትን ወዘተ በማዘጋጀት ክፍል ሲገቡ ተማሪዎች ማየት በሚችሉበት ቦታ ላይ በመስቀል ለተማሪዎች ማሳየት አስፈላጊ ነው፡፡

## የመማር ማስተማር ዘዴ

የዚህን ትምህርት ርእስ የተለያዩ የማስተማር ዘዴዎችን በመጠቀም ማስተማር ይቻላል፡፡ በዚህ የመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ተማሪዎች ከሚያውቁት ነገር ተነስተው እንድማሩ የተለያዩ የመልመጃ ጥያቄዎች እንደ በአካባቢያችሁ ከሚገኙ የመጓጓዣ አይነቶች የበለጠ አገልግሎት እየሰጠ ያው የቱ ነው፤ የመንገድ ደህንነት ማለት ምን ማለት ነው፤ የመንገድ ደህንነት ለመጠበቅ ተጠያቂነቱ የማን ነው፤ በማለት ጠይቋቸው፡፡ ተማሪዎች የሰጡትን መልስ በጥቁር ሠሌዳ ላይ ከፃፋችሁ በኋላ ተማሪዎችን በቡድን በመመደብ የመጓጓዣ ዓይነቶች፣ የትራፍክ ደህንነት፣ የትራፊክ አደጋ፣ የትራፊክ ምልክቶችና በትራፊክ ደንቦች ላይ በሰፊው እንድወያዩ እድል ስጡአቸው፡፡ ተማሪዎች በቡድን ውይይት በሚያካህዱበት ወቅት ሊያተኩርባቸዉ የሚገባውን ነጥብ በማዘጋጀት ይስጡአቸው፡፡ እያንዳንዱ ምድብ ከተሰጠው ርእስ አለመውጣቱን ያረጋግጡ፡፡ የተሰጣቸውን ሰርተው ከጨረሱ በኋላ ከተገነዘቡት ውስጥ ተራ በተራ ለክፍል ተማሪዎች እንዲያቀርቡት አድርጉአቸው፡፡ በመጨረሻም ላይ ተማሪዎች በፊት ከነበራቸው ግንዛቤና ከተወያዩ በኋላ ያገኙትን በማነጻጸር እንድናገሩ እድል በመስጠት የማጠቃለያ ሀሳብና ግብረ መልስ ስጡአቸው፡፡

## ልዩ ስጦታና ከፍተኛ የሆነ ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎች




የተለየ ችሎታና ከፍ ያለ ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎችን በማገዝ የፈጠራ ችሎታቸውን እንዲያሳድጉ ማድረግ ያስፈልጋል ውይይቱን በፍጥነት መጨረስ ስለሚችሉ ርእሱን የበለጠ ለመረዳት የሚያስችል ተጨማሪ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት መስጠት ያስፈልጋል፡፡ ነገር ግን እነዚህን የተለየ ችሎታ ያላቸውን ተማሪዎች ለማገዝ ሲዘጋጁ በዝግታ የሚመሩና ሴት ተማሪዎችን ተጨማሪ ሥራ በመስጠት የሚፈለገው የመማር ብቃት ላይ እንዲደርሱ መርዳት ልረሳ የማይገባ ጉዳይ ነው፡፡

## ተከታታይ ምዘና

ተማሪዎች የተማሩትን ተምህርት ምን ያህል እንደተረዱ ለመወቅ ተከታታይነት ያለዉ ክትትል ሊደረግላቸው ይገባል፡፡ የተማሪዎች የትምህርት ችሎታ ለመለየት የመልመጃ ጥያቄዎች እንደ የመሬት የመጓጓዣ ዓይነቶችና ጥቅሞች፣የትራፍክ ደህንነት፣ የትራፊክ አደጋ፣ የትራፊክ ምልክቶችና በትራፊክ ደንቦችና የመሳሰሉትን ጥያቄዎችን በመጠየቅ መለየታቸውን ያረጋግጡ፡፡ ለተጠየቁት ጥያቄዎች መልስ መመለሳቸውን ክትትል በማድረግ በተማሩት ትምህርት ርእስ ላይ የሚፈለገው እውቀትና ችሎታ ማግኘታቸውን ያረጋግጡ፡፡ የተማሪዎችን እንቅስቃሴ በየጊዜው በመከታተል በመዝገብ ላይ ያስፍሩ፡፡ ሁሉም ተማሪዎች ብያንስ ልደርሱበት የሚገባቸውን የብቃት ደረጃ ማግኘት አለባቸው፡፡ ብያንስ ልደርሱበት ከሚገባቸው የመማር ብቃት በታች ያገኙ ተማሪዎችን በክፍል ውስጥ ከሚገኙ ተማሪዎች ጋር ተመሳሳይ ደረጃ ላይ እንዲደርሱ የተለየና ተከታታይነት ያለው እገዛ ሊደረግላቸው ይገባል፡፡

**ማሳሰቢያ ፡-**

በተማሪ መፅሀፍ ላይ የተሰጠውን የተግባር ሥራ ከሰሩ በኋላ በተማሪ መጽሀፍ ላይ ለሚገኘው ምልክቶች የዚህን ሠንጠረዡ መግለጨ በማየት ይስጡአቸው፡፡

| ተ.ቁ | ምልክቶቹ የሚያስተላልፉት መመሪያ | የምልክቶች |
|---|---|---|
| 1 | የሚያስጠነቅቁ |  |
| 2 | የሚከለክሉ |  |
| 3 | የሚያስገድዱ |  |
| 4 | ቅድሚያ የሚያሰጡ |  |
| 5 | መረጃ የሚሰጡ |  |
| 6 | አቅጣጫ የሚያሳዩ |  |

**የመልመጃ 2.3 መልስ**

1. መጓጓዣ ሰዎችን ወይም እቃን ከአንድ ቦታ ወደሌላ ቦታ ለመጓጓዝ የሚያገለግል ነው፡፡ መጓጓዣ ሰዎች በቀላሉ በአለም ላይ እነዲንቀሳቀሱ ያደርጋል፡፡
2. ዘመናዊ መጓጓዣ በሶስት ዋና ዋና ክፍሎች ይመደባል፡፡ እነሱም ፡
   - የየብስ መጓጓዣ
   - የውሃ መጓጓዣ
   - የአየር መጓጓዣ ናቸው
3. የትራፊክ ህግን መጠበቅ ብዙ ጥቅሞች አሉት እነሱም
   - የሰው ህይወት እንዳይጠፋና ንብረት እንዳይባክን ይረዳል
   - የኢኮኖሚ እድገትን ያፋጥናል፡፡
4. እንደአለም የትራፍክ ምልክት አይነቶች በስድሰት ይከፈላሉ፡፡ እነርሱም

ማስጠንቀቂያ የሚሰጡ
የሚከለክሉ
የሚያስገድዱ
ቅድሚያ የምያሰጥ
መረጃ ሰጪ
አቅጣጫ አመልካች

5. መንገድን በጥንቃቄ ስናቋርጥ የምናከናውናቸው ነገሮች ብዙ ናቸው፡፡ እነርሱም፡-
    - በማያስፈራ ቦታ በኩል ማቋረጥ
    - በደንብ ማየትና ማዳመጥ
    - ለትራፊክ/ለመኪና ቅድሚያ መስጠት
    - በትክክለኛ መንገድ አቋርጥ
    - አለመሮጥ

**የምእራፍ 2 መጨረሻ ጥያቄዎች መልስ**

ክፍል 1. ለሚከተሉት ጥያቄዎች እውነት ወይም ሀሰት በማለት መልስ/ሽ/

1. እውነት
2. ሐሰት
3. ሐሰት
4. ሐሰት
5. ሐሰት

**ክፍል 2 ባዶውን ቦታ ሙላ/ሙይ**

6. መ 7. ሐ 8. ሠ 9. ለ 10.

**ክፍል 3 ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጥ**

11. ሀ 12. ለ 13. መ 14. ለ ሠ. ሐ

**ክፍል 4 ባዶው ቦታ ሙላ/ዪ**

16. ሆሞ ሐቢሊስ 17. መኀንኘ

**አጭር መልስ**

18. መቆም የሚገቡ ዋና ዋና ነገሮች

- ጠጥቶ ማሽከርከር
- ለረጅም ጊዜ በድካም ማሽከርከር
- በሞባይል እያወሩ ማሽከርከር
- ከመጠን በላይ በሆነ ፍጥነት ማሽከርከር

- ከተፈቀደው መንገድ ውጭ ማሽከርከር
- ባልተፈቀደ በኩል መዞር
- ምልክት ሳያሳዩ ማሽከርከር

19. መንገድን ስናቋርጥ ማድረግ የሚገቡን ነገሮች

- በማያስፈራ /ሰላም / በሆነ በኩል ማቋረጥ
- በመንገድ ዳር ሳይደርስ መቆም
- በሁሉም በኩል ትራፊክን ማየትና ማዳመጥ
- ለትራፊክ  ቅድሚያ መስጠት
- በቀጥተኛ መስመር ቀስ ብለው መቋረጥ
- አለመሮጥ

20. ሀ. 32.5 ሚሊዮን ለ.54

ሐ. 5 ኪ.ሜ ሐ. 100.50

# ምዕራፍ 3፡ ሰዉና የተፈጥሮ ሀብት

**የተሠጠ የክፍለ ጊዜ ብዛት ------------11**

## ከምዕራፉ የሚጠበቁ የመማር ውጤቶች፤

- በሰዉ ልጅና ተፈጥሮ ሀብት መካከል ያለዉን ግንኙነት ይገልፃሉ፤
- የተፈጥሮ ሀብትን በመገኛቸዉና በጥቅማቸዉ መክፈል ይችላሉ፤
- በተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም ላይ ጉዳት ልያደርሱ የሚችሉ ነገሮችን ይዘረዝራሉ።
- በተፈጥሮ ሀብትና በሰዉ ልጅ መካከል ያለዉን ግንኙነት(ከአቅም በላይ የሆነ አሠፋፈር፣ ተመጣጣኝ የሆነ አሠፋፈርና ዝቅተኛ የሆነ አሠፋፈር) ምን እንደሆነ ይገልፃሉ፤
- የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤና በቀጣይነት የመጠቀም ፅንሠ ሀሳብ ይገልፃሉ፤
- የተፈጥሮ ሀብትን ከጥፋት ለመጠበቅ ለህብረተሰብ ግንዛቤ መፍጠር ይችላሉ።

## መግቢያ

ባለፉት ትምህርት ውስጥ የሰዉ ልጅ ዘገምተናዊ ለውጥና የዓለም ህዝብ፣ የዓለም ህዝብ ቁጥር መለዋወጥና የህዝብ ሥርጭት፣ የህዝብ እንቅስቃሴ በአንድ ሀገር ውስጥና ከሀገር ውጪ፣ የሰዉ ልጅና የመጓጓዣ እድገት፤ የትራፍክ ደንቦች፤ የመንገድ ላይ ደህንነትና የመኪና መንገድን ያለጥንቃቄ ማቋረጥ ልያደርስ የሚችለዉ የመኪና አደጋዎችን መማራቸዉ ይታወቃል።

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ስለሰዉ ልጅ የተፈጥሮ ሀብትና ማህበራዊ እኮኖሚያዊ እድገት፤ የሰዉ ልጅና የተፈጥሮ ሀብት ግንኙነት፤ የተፈጥሮ ሀብት ዓይነቶችና በኢትዮጵያ ውስጥ በተፈጥሮ ሀብት ላይ ልደርሱ የሚችሉ ጉዳቶችን ይማራሉ።

### 3.1. በሰዉ ልጅና በተፈጥሮአዊ አከባቢ መካከል ያለዉ ግንኙነት

**ተማሪዉች ቢያንስ ልደርሱበት የሚገቡ የመማር ብቃቶች**

- በሰዉ ልጅና በተፈጥሮ ሀብት መካከል ያለዉ ግንኙነትን ይገልፃሉ፤
- የተፈጥሮ ሀብትን በመገኛቸዉና በሚሠጡት ጥቅም መሠረት ይመድባሉ፤
- በተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም ላይ ጉዳት ልያደርሱ የሚችሉ ነገሮችን ይዘረዝራሉ።

## ዋና ዋና ነጥቦች

በዚህ ምዕራፍ ትምህርት ውስጥ ሰዉና የተፈጥሮ ሀብት የሚለዉን ይማራሉ። ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት በትክክል እንድረዱና ለረጅም ጊዜ ሳይረሳ እንድቆይ ለማድረግ ከዚህ ርዕስ ጋር ልሄዱ የሚችሉ በትምህርት ማበልፀግያ ማዕከል ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ ስዕሎችን ከተቻለ ስለተፈጥሮ ሀብት ብክነትና እንክብካቤ የሚያሳዩ ቪድዮዎችን መጠቀም ይቻላል። በተጨማርም የግብርና በለሙያን በመጋበዝ የተማሪዎችን ግንዛቤ እንድጨምር ማድረግ ይቻላል።

## የመማር ማስተማር ዘዴዎች

የዚህን ትምህርት ርዕስ ማስተማር ከመጀመራችዉ በፍት የተማሪዎች መፅሓፍና ሌሎች ተጨማሪ መፅሓፍን በማንበብ ለትምህርት የሚረዱ መረጃዎችን መሰብሰብ ያስፈልጋል። ተማሪዎች የሚያዉቁትን እንድናገሩ ትምህርቱን በጥያቄና መልስ መልክ መጀመር ነዉ። ለምሳሌ በሰዉ ልጅና በአከባቢዉ የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብት መካከል ያለዉን ግንኙነት መጠየቅ ያስፈልጋል። ለዝህ ርዕስ የሚያስፈልጉ የመማር ማስተማር ዘዴን መምረጥ ያስፈልጋል። ተማሪዎች ትምህርታቸዉን በንቃት እንድከታተሉ ማበረታታት አስፈላግ ነዉ።

### ልዩ ስጦታና ከፍተኛ የሆነ ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎች

የተለየ ችሎታና ከፍ ያለ ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎችን በማገዝ የፈጠራ ችሎታቸውን እንዲያሳድጉ ማድረግ ያስፈልጋል ውይይቱን በፍጥነት መጨረስ ስለሚችሉ ርእሱን የበለጠ ለመረዳት የሚያስችል ተጨማሪ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት መስጠት ያስፈልግዎታል። ነገር ግን እነዚህን የተለየ ችሎታ ያላቸውን ተማሪዎች ለማገዝ ሲዘጋጁ በዝግታ የሚመሩ ተማሪዎች ተጨማሪ ሥራ በመስጠትና የሚፈለገው የመማር ብቃት ላይ እንዲደርሱ መርዳት ልረሳ የማይገባ ጉዳይ ነው።

## ተከታታይ ምዘና

ተማሪዎች ትምህርቱን ምን ያህል እንደተማሩና እንደተገነዘቡ ለማወቅ የማያቋርጥ ክትትል ያስፈልጋል። የተማሪዎቻችሁን ችሎታ ለመለየት የተለያዩ የምዘና ጥያቄዎችን ማዘጋጀት

ያስፈልጋል፡፡ ተማሪዎች የሚያቀረቡትን መልሶችን በመሰብሰብ በትምህርቱ ላይ ምን ያህል እዉቀት እና ግንዛቤ እንዳገኙና የሚጠበቀዉ የመማር ብቃት ማግኘታቸዉን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ የተማሪዎችን ተሳትፎ በየቀኑ በማስታወሻ ደብተር ላይ መመዝገብ፡፡ ሁሉም ተማሪዎች ልደርሱበት የሚገባቸዉ እዉቀትና ግንዛቤ ማግኘት አለባቸዉ፡፡ የሚጠበቀዉ የመማር ብቃት ላይ መድረስ ያለቻሉ ተማሪዎች ልዩ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ የመማር ችሎታቸዉን ማሻሻል ያስፈልጋል፡፡

## 3.1 የሰዉ ልጅና በተፈጥሮ ሀብት መካካል ያለዉ ግንኙነት

**የተሰጠ የክፈለ ጊዜ ብዛት -----------3**

**ተማሪዎች ብያንስ ልደርሱበት የሚገቡ የመማር ብቃት**

- የሰዉ ልጅና በተፈጥሮ ሀብት መካካል ያለዉ ግንኙነት ምን እንደሆነ ያመዛዝናሉ፤
- በተፈጥሮ ሀብትና በሰዉ ልጅ መካከል ያለዉን ግንኙነት(ከአቅም በላይ የሆነ አሠፋፈር፣ ተመጣጣኝ የሆነ አሠፋፈርና ዝቅተኛ የሆነ አሠፋፈር) ምን እንደሆነ ይገልፃሉ፤
- በአከባቢያቸዉ የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብቶች እንክብካቤ ያድጋሉ፡፡

### ዋና ዋና ነጥቦች

በተፈጥሮ ሀብት በህገ ወጥ መንገድ መጠቀም ብክነት የሚያስከትል መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይህ የተፈጠሮ ሀብት ብክነት እየተከሰተ ያለዉ በሰዉ ልጅ ተግባር ምክንያት መሆኑ መግለፅ ያስፈልጋል፡፡ በማደግ ላይ ያሉ ሀገሮች ድህነትና ዝቅተኛ የእኮኖሚ እድገት ላይ የሚገኙ መሆናቸዉ ይታወቃል፡፡ ለምሳሌ ከሰሀራ በታች የሚገኙ የአፍርካ ሀገሮች ላይ የተፈጥሮ ሀብት ብክነት ውስብስብ  አድርገዉታል፡፡ ስለዚህ በከፍተኛ ፍጥነት እያደገ ያለዉን የሰዎች ቁጥር ለመቀነስ ማህበረሰቡን ማስተማርና የህዝብ ቁጥር ተመጣጣኝ እንድሆን በማድረግ የተፈጥሮ ሀብት ብክነትን መቀነስ ወሳኝ ጉዳይ ነዉ፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች የሰዉ ልጅና የተፈጥሮ ሀብት ግንኙነት ምን መሆን እንዳለበት በደንብ እንድገነዘቡ ማድረግ ይጠበቅበቹዋል፡፡ ከአቅም በላይ የሆነ የህዝብ አሠፋፈር ማለት በአንድ በተወሰነ ቦታ ላይ የህዝብ ቁጥር ከተፈጥሮ ሀብት በላይ ሆኖ ስገኝ ነዉ፡፡ እንደዝህ ዓይነት ግንኙነት የሚታየዉ በእኮኖሚ በጣም ዝቅተኛ የሆኑና የቤተሰብ ምጣኔ የማይጠቀሙ ሀገሮች ላይ ነዉ፡፡ ለዝህ ጥሩ ምሣሌ ልሆኑ የሚችለዉ የአፍርካ፣ ደቡብ አሜርካና ኢሲያ አህጉራት ናቸዉ፡፡

ተመጣጣኝ የሆነ የህዝብ አሠፋፈር ማለት የአንድ ሀገር የህዝብ ቁጥርና በሀገሪቱ ያለዉ የተፈጥሮ ሀብት ተመጣጣኝ ሆኖ ስገኝ ነዉ። በእንደዝህ ያሉ ሀገራት ውስጥ ዝቅተኛ የሆነ የሀብት ብክነትና ጤናማ የሆነ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ግንኙነት ይኖራቹዋል።

ከአቅም በታች የሆነ ህዝብ ማለት የአንድ ሀገር የህዝብ ቁጥር በሀገሪቱ የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብት በታች ሆኖ ስገኝ ማለት ነዉ። የሚወለደዉ የህፃናት ቁጥር በጣም ዝቅተኛ ነዉ። በእንደዝህ ዓይነት ሀገሮች ለተፈጥሮ ሀብት የሚደረገዉ ጥንቃቄ ስላሌለ ከፍተኛ የሆነ የሀብት ብክለት ይታያል።

## ቅድመ ዝግጅት

ይህንን ርዕስ ለማስተማር የኢትዮጵያ ካርታና የተፈጥሮ ሀብት ብክነት የሚያሳይ ካሬታ ወይም ግራፍ ቀድሞ ማዘጋጀት ያስፈልጋል።

### የመማር ማስተማር ዘዴዎች

የዝህ ርዕስ ትምህርት ተማሪዎችን ማዕከል ባደረገ መልኩ በተለያየ ዘዴዎች ልቀርብ ይችላል። ለምሣሌ በመስክ ጉብኝት፣ በፕሮጀክት ወይም በገለፃ መልክ የግብርና ባለሙያዎችን በመጋበዝ ልሆን ይችላል። በእንደዝህ ዘዴዎች ለመጠቀም በቅድሚያ ከዚህ ርዕስ ጋር የተያያዜ ሌሎች ፅሁፎችን በማንበብ መዘጋጀት ያስፈልጋል። ተማሪዎች ትምህርታቸዉን በትክክል እንድከታተሉ የሚቀርበዉ ትምህርት በሚስብ መልኩ መሆን አለበት።

### ተከታታይ ምዘና

ተማሪዎች ትምህርቱን ምን ያህል እንደተማሩና እንደተገነዘቡ ለማወቅ የማያቋርጥ ክትትል ያስፈልጋል። የተማሪዎቻችሁን ችሎታ ለመለየት የተለያዩ የምዘና ጥያቄዎችን ማዘጋጀት ያስፈልጋል። ለምሣሌ ስለተፈጥሮ ሀብት ምንነት፤ የተፈጥሮ ሀብት ጥቅም ላይ የመሣሰሉት ተማሪዎች የሚያቀረቡትን መልሶችን በመሰብሰብ በትምህርቱ ላይ ምን ያህል እዉቀትና ግንዛቤ እንዳገኙና የሚጠበቀዉ የመማር ብቃት ማግኘታቸዉን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። የተማሪዎችን ተሳትፎ በየቀኑ በማስታወሻ ደብተር ላይ መመዝገብ። ሁሉም ተማሪዎች ልደርሱበት የሚገባቸዉ እዉቀትና ግንዛቤ ማግኘት አለባቸዉ። የሚጠበቀዉ የመማር ብቃት ላይ መድረስ

ያልቻሉ ተማሪዎች ልዩ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ የመማር ችሎታቸዉን ማሻሻል ያስፈልጋል።

1. የተፈጥሮ ሀብት ዓይነቶች
2. ታዳሽ የሆኑ የተፈጥሮ ሀብት
3. ታዳሽ ያልሆኑ የተፈጥሮ ሀብት

**ከዚህ ርዕስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፤**

- ታዳሽና ታዳሽ ያልሆኑ የተፈጥሮ ሀብት መካከል ያልሆነዉን ልዩነት ይገልፃሉ።

## ዋና ዋና ነጥቦች

በለፈዉ ትምህርት ውስጥ በሰዉ ልጅ እና በተፈጥሮ ሀብት መካከል ያለዉን ግንኙነት ተምሯል። በዚህ ርዕስ ሥር ታዳሽና ታዳሽ ያልሆኑ የተፈጥሮ ሀብት ምንነት ይማራሉ። ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት በደንብ እንድገነዘቡና ለረዥም ጊዜ እንዳይረሱ ለማድረግ የተለያዩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን መጠቀምና በተጨማርም ከዚህ ርዕስ ጋር የሚያያዙ የተለያዩ መፅሓፍትን በማንበብ በደንብ መዘጋጀት ያስፈልጋል።

## ቅድመ ዝግጅት

የዚህን ርዕስ ትምህርት ለማስተማር የተለያዩ የትምህርት መርጃ መሣሪያ፤ የኢትዮጵያ ካርታና ታዳሽና ታዳሽ ያልሆኑ የተፈጥሮ ሀብቶች ሥዕል ማዘጋጀት አስፈላግ ነዉ። በተጨማሪም ለዝህ ርዕስ የሚመች የመማር ማስተማር ዘዴን መምረጥ ያስፈልጋል።

## የመማር ማስተማር ዘዴ

በዚህ ትምህርት ርዕስ ላይ በተማሪዎች መማሪያ መፅሓፍ ውስጥ የተፃፈዉን ሀሳብ ቀድመዉ በማንበብ ተጨማሪ ጭብጦችን ተማሪዎች እንድያገኙ ማድረግ ያስፈልጋል። ተማሪዎችን በቡድን ሆነዉ እንድወያዩና እዉቀታቸዉንና ልምዳቸዉን እንድለዋወጡ ማድረግ። ታዳሽና ታዳሽ ያልሆኑ የተፈጥሮ ሀብቶች ማካከል ያለዉን ልዩነት ላይ የተለያዩ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት የሚያዉቁትን እንድናገሩ ማድረግ ያስፈልጋል።

## ልዩ ተሠጥዖና ከፍተኛ የሆነ ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎች

የተለየ ችሎታና ከፍ ያለ ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎችን በማገዝ የፈጠራ ችሎታቸውን እንዲያሳድጉ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ውይይትን በፍጥነት መጨረስ ስለሚችሉ ርእሱን የበለጠ ለመረዳት የሚያስችል ተጨማሪ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት መስጠት ያስፈልጋል፡፡ ነገር ግን እነዚህን የተለየ ችሎታ ያላቸውን ተማሪዎች ለማገዝ ሲዘጋጁ በዝግታ የሚመሩና ሴት ተማሪዎች ተጨማሪ ሥራ በመስጠትና የሚፈለገው የመማር ብቃት ላይ እንዲደርሱ መርዳት ልረሳ የማይገባ ጉዳይ ነው፡፡

## ተከታታይ ምዘና

ተማሪዎች ትምህርቱን ምን ያህል እንደተማሩና እንደተገነዘቡ ለማወቅ የማያቋርጥ ክትትል ያስፈልጋል፡፡ የተማሪዎቻችሁን ችሎታ ለመለየት የተለያዩ የምዘና ጥያቄዎችን ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ ተማሪዎች የሚያቀረቡትን መልሶች በመሰብሰብ በትምህርቱ ላይ ምን ያህል እዉቀትና ግንዛቤ እንዳገኙና የሚጠበቀዉ የመማር ብቃት ማግኘታቸዉን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ የተማሪዎችን ተሳትፎ በየቀኑ በማስታወሻ ደብተር ላይ መመዝገብ፡፡ ሁሉም ተማሪዎች ልደርሱበት የሚገባቸዉ እዉቀትና ግንዛቤ ማግኘት አለባቸዉ፡፡ የሚጠበቀዉ የመማር ብቃት ላይ መድረስ ያለቻሉ ተማሪዎች ልዩ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ የመማር ችሎታቸዉን ማሻሻል ያስፈልጋል፡፡

## 3.1. በኢትዮጵያ ውስጥ በተፈጥሮ ሀብት ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ነገሮች

የተሠጠ የክፍለ ጊዜ ብዛት -----------2

### ዋና ዋና ነጥቦች

በለፉት ትምህርት ውስጥ ታዳሽና ታዳሽ ያልሆኑ የተፈጥሮ ሀብትን ተምሩዋል፡፡ በዚህ ርዕስ ትምህርት በኢትዮጵያ ውስጥ በተፈጥሮ ሀብት ላይ ጉዳት የሚያደርሱ የሰዉ ተግባራት ለምሳሌ የእርሻ መሬትን ለማስፋፋት፤የከተሞች መስፋፋት፤ የህዝብ አሠፋፈርና የመሣሠሉትን ይማራሉ፡፡

## ቅድመ ዝግጅት

በህዝብ አሠፋፈርና የተፈጥሮ ሀብት ላይ ተፅዕኖ የሚያደርሱ ነገሮችን የሚያሳይ የኢትዮጵያ ካርታና ሰዉ ሰራሽ የሆነ የህዝብ ጥግግትን የሚወስኑ ነገሮችን የሚያሳይ ቻርት ማዘጋጀት ነዉ፡፡ በትምህርት ቤታችዉ አከባቢ የተፈጥሮ ሀብት ብክነት የደረሰበትን ቦታ ተማሪዎች እንድጎበኙ ለማድረግ ቅድመ ዝግጅት ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ በዚህ ርዕስ ላይ ትኩረት ልሰጠዉ የሚገባዉ በህዝብ ተፅዕኖ፣ የእርሻ መሬት መስፋፋት፣ የከተሞች መስፋፋትና የህዝብ ጥግግት ላይ በቂ የሆነ ግንዛቤ እንድያገኙ የተለያዩ አገዥ መፅሓፍትን በማንበብ ተማሪዎችን በደንብ እንድገነዘቡ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ተማርዎች የተማሩትን ትምህርት እንዳይረሱና ለረጅም ጊዜ እንድቆይ ለማድረግ ከዚህ ትምህርት ጋር የሚሄዱ የተለያዩ ሥዕሎችን፣ መጠቀም ያስፈልጋል፡፡

## የመማር ማስተማር ዘዴ

በዚህ ርዕስ ትምህርት ላይ በተማሪዎች መማሪያ መፅሓፍ ላይ የተፃፈዉንና ሌሎች ተጨማሪ መፅሓፎችን ማንበብና ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ተማሪዎች የእርሻ መሬትን ለማስፋፋት፤ በከተሞች መስፋፋት የህዝብ ጥግግት በተፈጥሮ ሀብት ላይ የሚያደርሱትን ጉዳቶች በቂ እዉቀት እንድያገኙ ለማድረግ የተለያዩ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት ተማሪዎች እንድወያዩ ማድረግ አስፈላጊ ነዉ፡፡

## የፕሮጀክት ሥራ

ተማሪዎች በቡድን ሆነዉ በአከባቢያቸዉ የሚገኙትን ደኖችና አፈርን እንድመለከቱ በማድረግና የተረዱትን ነገር ላይ ለክፍል ተማሪዎች ርፖርት እንድያቀርቡ አድርጉ፡፡ በመስክ ጉብኝት የተማላካቱትን ርፖርት ለማቅረብ ሴት ተማሪዎች ከወንድ ተማሪዎች ጋር እንድወዳደሩ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

## ተከታታይ ምዘና

ተማሪዎች ትምህርቱን ምን ያህል እንደተማሩና እንደተገነዘቡ ለማወቅ የማያቋርጥ ክትትል ያስፈልጋል፡፡ የተማሪዎቻችሁን ችሎታ ለመለየት የተለያዩ የምዘና ጥያቄዎችን ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ ተማሪዎች የሚያቀረቡትን መልሶችን በመሰብሰብ በትምህርቱ ላይ ምን ያህል እዉቀት እና ግንዛቤ እንዳገኙና የሚጠበቀዉ የመማር ብቃት ማግኘታቸዉን ማረጋገጥ

ያስፈልጋል። የተማሪዎችን ተሳትፎ በየቀኑ በማስታወሻ ደብተር ላይ መመዝገብ። ሁሉም ተማሪዎች ልደርሱበት የሚገባቸዉ እዉቀትና ግንዛቤ ማግኘት አለባቸዉ። የሚጠበቀዉ የመማር ብቃት ላይ መድረስ ያልቻሉ ተማሪዎች ልዩ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ የመማር ችሎታቸዉን ማሻሻል ያስፈልጋል።

## የመልመጃ 3 የጥያቄ መልሶች

ሀ. ምርጫ

1. ሀ 2. መ 3. ሀ

**ለ. አጭር መልስ**

ሀ. የሚታደሱ የተፈጥሮ ሀብት

ለ. የማይታደሱ የተፈጥሮ ሀብት

2. የሰዉ ልጅ ለኑሮዉ የሚያስፈልገዉን እንደ ምግብ፣ ልብስ መጠለያ ከአከባቢዉ ስለሚያገኙ ከተፈጥሮ ሀብት ጋር የማይቋረጥ ግንኙነት አሉዋቸዉ።

3.

- የህዝብ ተፅዕኖ
- የእርሻ መሬት መስፋፋት
- የከተሞች መስፋፋት
- የህዝብ ስርጭት

4. ከአቅም በላይ ህዝብ ማለት የህዝብ ቁጥር ከተፈጥሮ ሀብት በላይ ሲሆን ማለት ነዉ
5. ዝቅተኛ የሆነ ህዝብ ባህሪያት የሆነዉ፤
   - የተመቻቸ ኑሮ ይኖራሉ
   - ልጆች እና ቤተሰብ በሙሉ የህይወት ዋስትና ከመንግስት ያገኛሉ
   - የሥራ ዕድል ሰፊ መሆን

ሐ. ባዶ ቦታ ሙሉ

1. የህዝብ ሥርጭት፣ የእርሻ መሬት መስፋፋት፣ የከተሞች መስፋፋት
2. የማይታደሱ የተፈጥሮ ሀብት ናቸዉ

## ምዕራፍ 4፡ ቀደምት የአለም ስልጣኔ

**የክፍለ ጊዜ ብዛት------------ 24**

**ከዚህ ምዕራፍ የሚጠበቁው ጤቶች፣**

- በወንዞች ዳርቻ የተመሰረቱትን ቀደመትስልጣኔዎችበካርታ ላይያሳያሉ
- ቀደምት የአለም ስልጣኔን እና የመካከለኛው ክፍለ ዘመን ስልጣኔን በማነፃፀር ያገናዝባሉ፡፡
- የክርስትና ሀይማኖት አመጣጥ እና መስፋፋትን ይገነዘባሉ
- የእስልምና ሀይማኖት አመጣጥ እና መስፋፋትን ይገነዘባሉ
- የባዛንታየን ኢምፓየር ገፀ ባህሪያትን ትዘረዝራላችሁ፡፡

**መግቢያ**

በአከባቢ ሳይንስ ትምህርት ውስጥ ስለ ማህበራዊ ኑሮ፣የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤ፣ግብርና እና ንግድ በክልል እና በኢትዮጵያ ያለበትን ደረጃ ተምረዋል፡፡ በተጨማሪም በምስራቅ አፍሪካ ውስጥ የሚገኙ የታሪካዊ ቅርሶች ማዕከላትን ለይተዋል፡፡በዚህ ምዕራፍ ደግሞ ስለ ቀደምት የአለም ወንዞች ሸለቆዎች ስልጣኔዎች ማለትም እንደ ሜሶፖታሚያ፣ህንድ፣ ቻይና እና የግሪኮ-ሮማ ስልጣኔዎችን በስፋት ይማራሉ፡፡ እንዲሁም ስለ ክርስትና ሀይማኖትና የእስልምና ሀይማኖት አመጣጥ እና መስፋፋትን ይማራሉ፡፡ በጨረሻም ስለ ባዛንታየን ኢምፓየር ባህሪያትን ይገነዘባሉ፡፡

### 4.1.ጥንታዊ የአለም ስልጣኔዎች

**(ሜሶፖታሚያ፣ህንድ፣ቻይና እና የግሪኮ-ሮማን)**

**የክፍለ ጊዜ ብዛት----------- 17**

**ተማሪዎች ቢያንስ ሊኖራቸው የሚገባ የትምህርት ብቃት፤**

- በወንዞች ዳርቻ የተመሰረቱትን ስልጣኔዎች ይዘረዝራሉ
- ቀደምት የአለም ስልጣኔና የመካከለኛው ክፍለ ዘመን ስልጣኔ ውጤቶችን ያብራራሉ
- የክርስትናና የእስልምና ሀይማኖት አመጣጥና መስፋፋትን ይዘረዝራሉ
- የባዛንታየን ኢምፓየር ታሪክና ባህሪያትን ያገናዝባሉ፡፡
- ደምት የአለም ስልጣኔዎችና የመካከለኛውን ክፍለ ዘመን የአለም ስልጣኔዎችን ይለያሉ፡፡

## ዋና ዋና ነጥቦች

በጥንት ዘመን የነበሩ የአለምስልጣኔዎችንና በዘመናዊ አለም ያለውን ስልጣኔ መረዳት ያስፈልጋል። እንዲሁም በጥንት ዘመንና በመካከለኛው ክፍለ ዘመን የነበሩትን ስልጣኔዎችን አንድነትና ልዩነታቸውን ማመዛዘን እንዲያመዛዝኑ ማድረግ አስፈላጊ ነው። ቀደምት የአለም ስልጣኔዎች የተጀመሩበትን ቦታ በካርታ ላይ መለየት የመጀመሪያውና ዋናው ነጥብ ነው።

በቀደምት የአለም ስልጣኔ ውስጥ የተለያዩ ፈጠራዎችና ስልጣኔዎች ተስፋፍተዋል። ከእነዚህ ስልጣኔዎች ውስጥ በሰው ልጅ የኑሮ ዘይቤ ላይ ከፍተኛ ለውጥ ያመጡት በተለያየ ዘርፍ ነው፡ ፡. እነሱምግብርና፣ ንግድ፣ የሰዎች በአንድ አካባቢ በቋሚነት መኖር፣ የከተሞች መቆርቆር እና የመንግስታት መመስረት ናቸው፡፡ በተጨማሪም ስነ-ፅሁፍ፣የብረታ ብረት ስራ፣ ስነ-ህንፃ፣የሸማ፣ የሸክላ፣ የእንጨት ስራዎች፣ ቀለማትን መቀባት፣ጀልባን ለመጓጓዣነት መጠቀም ከፍረኛ ደረጃ ላይ የደረሱት  በቀደምት የአለም ስልጣኔ ነው፡፡በተመሳሳይ መልኩ የዴሞክራሲ ሐሳብ፣የተለያዩ ሀይማኖቶች አመለካከት፣ህጎች፣የሪፐብሊክ ጽንሰ ሀሳብ፣ እናቲያትር የቀደምት አለም ስልጣኔዎች ውጤት ናቸው፡፡እንዲሁም የሂሳብ ሳይንስ ትምህርትንማስፋፋት፣ የህክምናና የህዋ ሳይንስ ጥናቶችን ለአለም አበርክተዋል።

ጥንታዊ የአለምስልጣኔዎች በወንዞች ዳርቻ የተመሰረቱበትን ምክንያት በአግባቡ መረዳት አስፈላጊ ነው። በሜድትራኒያን ባህር አካባቢ የተመሰረቱን ስልጣኔዎች በጥልቀት ተለይተው መታወቅ አለባቸው። እንዲሁም በሜድትራኒያን ባህር አካባቢ የተመሰረቱን ስልጣኔዎች በማነፃፀር ማስተዋል ይጠበቅባችኋል።




ካርታ. 4.1. የሜድትራኒያን ባህር አካባቢ ስልጣኔን የሚያሳይ

የክርስትና ሀይማኖት የተጀመረው በ1ኛውዓ.ም በመካከለኛው ምስራቅ አሁን ፍሊስጤምና እስራኤል በሚባሉት አከባቢዎች ውስጥ ነው፡፡ የክርስትና ሀይማኖት ከ1ኛው እስከ 4ኛዉዓ.ም የተለያዩ ችግሮችን ማሳለፉን ለይቶ ማወቅ አስፈላጊ ነው፡፡በተጨማሪም የክርስትና ሀይማኖት በተለያዩ የአለም ክፍሎች የተሰፋፋበት ክፍለ ዘመን በቅደም ተከተል ማደራጀት አስፈላጊ ነው፡፡

የክርስትና ሀይማኖት ከእስልምና ሀይማኖት ጋር ያለውን ግንኙነት አመቺ በሆነ መልኩ ማደራጀት አስፈላጊ ነው፡፡ እንዲሁም የእነዚህ ሀይማኖቶች ትምህርት የሰውልጅ መልካም ስብእናን፣ ሰላምን እና ፍቅርን እንዲላበስ እደሚያስተምሩ ማወቅ ዋና ነጥብ ነው፡፡ በአጠቃላይ በአለም ላይ ያሉት ሀይማኖቶች ለሰው ልጅ ሰላም እና አብሮነትን የሚያስተምሩ መሆናቸውን በአግባቡ መረዳት አሰፈላጊ ነው፡፡ ለምሳሌ የተለያዩ ሀይማኖቶች ያሉበት ሀገሮች እንደ ኢትዮጵያና ሌሎች ሀገሮችን ልምድ በአግባቡ በመረዳት በቂ ዝግጅት ማድረግና ተማሪዎች እንዲረዱ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡

## ቅድመ ዝግጅት

ስለ ቀደምት የአለም ስልጣኔዎች ከማስተማር በፊት የስልጣኔን ምንነት፣ የቀደምት አለም ስልጣኔዎችን አይነት እና ሁኔታ የተለያዩ ዋቢ መጽሐፎችን በማንበብ በቂ ግንዛቤ ማጎልበት አስፈላጊ ነው፡፡ የቀደምት አለም ስልጣኔዎችን አካባቢ የሚያሳይ ካርታ አዘጋጁ፡፡ የቀደምት

አለም ስልጣኔዎችን የሚያሳዩ ፎቶዎችንና ፖስተሮችን በማሰባሰብ ማዘጋጀት፡፡ በተለይ የጥንት ሜሶፖተሚያ፣ ግሪክ፣ ህንድ እና የመሳሰሉትን ስልጣኔዎችን የሚያሳዩ ፎቶግራዎችን ማሰባሰብና መጠቀም፡፡ ከተቻለ ፖስተሮችን፣ በጥንት ዘመን የነበሩ ምሁራን ፎቶዎች እና የተለያዩ የታሪካዊ ቅረሶች ፎቶ አዘጋጅ/ጂ፡፡

በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ ማውጣት ዋናው ተግባር ነው፡፡ እለታዊ የትምህርት ዕቅድ በምታወጡበት ጊዜ የትምህርት መርጃ መሳሪያ ማዘጋጀትና የተለያዩ የማስተማር ዘዴዎችን ማካተት አስፈላጊ ነው፡፡ በተጨማሪም ሲለበሶችን፣ የተማሪ መጽሐፍ እና የመምህር መምሪያ መጽሐፍትን በማሰተያየት የትምህርት ዕቅድ አዘጋጁ፡፡ በዚህ ሁኔታ የቀደምት ሜሶፖተሚያ ስልጣኔ ለማስተማር 3 **ክፍለ ጊዜ**፣የህንድና ቻይና ስልጣኔዎችለማስተማር ደግሞ**6ክፍለ ጊዜ** ተጠቀሙ፡፡ እንዲሁም የግሪኮ-ሮማን ስልጣኔን ለማስተማር 6 **ክፍለ ጊዜ**ተጠቀሙ፡፡ የክርስትናህይማኖት አጀማመርና መሰፋፋት ለማስተማር 2 **ክፍለ ጊዜ**በቂ ነው፡፡በአጠቃላይ 17 **ክፍለ ጊዜያት**ይሆናሉ፡፡ተማሪዎችን ማነቃቃት የሚችሉ **ከሶስት** ያልበለጡ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት በገለጻ ወቅት መጠየቅ አስፈላጊ ነው፡፡

## የመማር ማስተማር ዘዴ

በመጀመሪያ ከተለያዩ መረጃዎች ላይ የቀደምት አለምስልጣኔ ትርጉምና የተጀመሩበትን አካባቢዎች መረዳት አስፈላጊ ነው፡፡ጥንታዊ የአለም ስልጣኔዎች በወንዞች ዳርቻ የተመሰረቱበትን ምክንያት መረዳት አስፈላጊ ነው፡፡ በመቀጠልም ምቹ የሆነ የመማር ማስተማር ዘዴ ትመርጣላችሁ፡፡ የተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎችያሉ ሲሆን በተማሪው የቅበላ ሁኔታ ላይ በመመስረት በውይይት፣ ሰርቶ በማሳየት፣ የተላያዩ ነገሮችን በማነጻጸርና ማገናዘብ ዘዴዎችውስጥ የተሻለውን መጠቀም ይቻላል፡፡

ተማሪዎች የቀደምት የአለም ስልጣኔዎችን(የሜሶፖታሚያ፣ህንድ፣የቻይናእናየግሪኮ-ሮማ)መገኛ ቦታዎች የአለምን ካርታ በመጠቀም እንዲያሰዩ ታደርጋላችሁ፡፡ ፖስተሮችን፣ በጥንት ዘመን የነበሩ የምሁራን ፎቶዎች እና የተለያዩ የታሪካዊ ቅርሶች ፎቶ ላይ ተማሪዎች በነፃነት ሀሳባቸውን እንዲሰጡ ማድረግ፡፡ በተማሪዎች መጽሐፈፍ ላይ የተሰጡትን ፕሮጀክቶችን በማሰራት ተጨባጭ የሆነ ትምህርት ለተማሪዎች መስጠት ይጠበቅባችኋል፡፡በተጨማሪም የክርስትናህይማኖት አጀማመርና መሰፋፋት ከማስተማር በፊትበቂ መረጃ ማግኘት አስፈላጊ

ነው። በተማሪዎች መካከል አላስፈላጊ ክርክሮችና አለመግባባቶች እንዳይፈጠሩ ጥንቃቄ ማድረግ አስፈላጊ ነው።

የሀይማኖቶች ትምህርት የሰውልጅ መልካም ስብእናን፣ መቻቻልን፣ አብሮነትን፣ ሰላምን እና ፍቅርን የሚያስተምር መሆኑን ተማሪዎች በቀላል መንገድ እንዲረዱ ማድረግ አሰፈላጊ ነው። ተማሪዎች የሀይማኖት መቻቻልን መረዳታቸው አስፈላጊ ነው። በአለምአቀፍ ህጎች ውስጥ የፈለጉትን እምነት የመከተል መብት፣ ሰብአዊ መብት እና የሀይማኖት እኩልነት መብት የተደነገገ መሆኑን በመግለጸ ተማሪዎችን ማስተማር አስፈላጊ ነው።

በአጠቃላይ የመማር ማስተማር ሂደታችሁ ሁሉን አቀፈና አሳታፊ የሆነ መሆን አለበት። የጾታ እኩልነትን ለማረጋገጥ ተማሪዎች እኩል የመሳተፍ መብት እንዳለቸው ማስረዳት አስፈላጊ ነው። እንዲሁም የልዩ ፍላጎት ተማሪዎች መደገፍ እና ማበረታታት አስፈላጊ ነው።

## ልዩ ተሰጥዖ ያላቸዉን ተማሪዎች መደገፍ

ልዩ ተሰጥዖና ከፍተኛ ግንዛቤ ያላቸዉን ተማሪዎች በመደገፍ የፈጠራ ችሎታቸዉን እንዲያዳብሩ ማበረታታት አስፈላጊ ነዉ።ለምሳሌ የጀልባ ስዕል ማንሳት፣ ካርታ ማንሳትና ስዕል የመሳል ሞያ መለማመድ የሚፈልጉ ተማሪዎች ካሉ አበረታታቸዉ/ቿያዉ። በቡድናቸዉ ዉስጥ የተሰጣቸዉን ስራ ቀድመዉ የጨረሱ ተማሪዎችም ካሉ በተጨማሪ ሊሰሩ የሚችሉትን ጥያቄ መስጠት ተገቢ ነዉ። ጥያቄዎቹ እየተማሩት ካለዉ ርዕስ ዉስጥ ሳይወጣ በተቀራራቢ ይዜት በማዘጋጀት ሊሰጣቸዉ ይገባል።

## ተከታታይ ምዘና

በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዱ ለማወቅ ተከታታይነት ያለው ክትትልና ምዘና ሊደረግ ይገባል፡፡ በዚህ ሁኔታ የተማሪዎችን የትምህርት ችሎታ ለመለየት የመልመጃ ጥያቄዎችን በመስጠት መለየት እንችላለን፡፡ ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት መረዳታቸውን ለማወቅ በመሃል የማረጋገጫ ጥያቄዎችን መጠየቅ አስፈላጊ ነው፡፡በዚህ መሰረት ተማሪዎች ቀደምት የአለም ስልጣኔ የተጀመረበትን ቦታ በካርታ ላይ ማሳየት እንዳለበቸው መዘንጋት የለበትም፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች ከጥንት የአለም ስልጣኔዎች መካከል ከውጭ ሀይል ወረራዎች ነፃ በመሆን ያስቀጠሉ ሀገራትን እንዲያብራሩ መጠየቅ አለባችሁ፡፡ከጥንታዊ ቅርሶች ተማሪዎች የተወሰኑትን እንዲዘረዝሩ

መጠየቅም ይቻላል፡፡

ተማሪዎችን በቡድን በማሳተፍ ምን ያህል እንደተረዱ መለየት አስፈላጊ ነው፡፡በቀደምት የአለም ስልጣኔ የተገኙትን ግኝቶችና ስልጣኔዎችን የሚገልጽ በአካባቢያቸው ከሚገኙት ነገሮች የሰሩትን መገምገም አስፈላጊ ነው፡፡ በተመሳሳይ በነዚህ ንዑስ ርዕሶች መጨረሻ ስር ያሉትን የመልመጃ ጥያዎች ተማሪዎችን በመጠየቅ የግንዛቤ ደረጃቸውን መገምገም አስፈላጊ ነው፡፡ እያንዳንዱ ተማሪ የመልመጃዎችን ጥያቄዎች መልስ እንዲመልሱ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡በዚህ መሰረትእያንዳንዱ ተማሪ መልመጃዎችን በግሉ/ሏ እንዲሰሩ ማድረግ ግዴታ ነው፡፡በአጠቃላይ ተማሪዎች ቢያንስ ሊኖራቸው የሚገባቸው የትምህርት ብቃት ለማወቅ ተከታታይ ምዘና መስጠትና ግብረ መልስ መስጠት አስፈላጊ ነው፡፡

## 4.2. የመካከለኛው ክፍለ ዘመን የአለም ታሪክ

**(የባይዛንታይን ኢምፓየርና የእስልምና አመጣጥ እና መስፋፋት)**

**የክፍለ ጊዜ ብዛት-------------7**

**ተማሪዎች ቢያንስሊኖራቸው የሚገባ የትምህርትብቃት:**

- በመካከለኛው ክፍለ ዘመን በአለም ላይ የተመዘገቡ ዕድገቶችን ያመዛዝናሉ
- የባዛንታይን ኢምፓየር ባህሪያትንና ቀደምት የመካከለኛውን ክፍለዘመንና ዘመናዊ የአለም ስልጣኔዎችን ያነፃጽራሉ
- የእስልምና ሀይማኖት የት እንደተጀመረና እንዴት እንደተሰፋፋ በመረዳት በአፍሪካ ቀንድ ሰላማዊ በሆነ መንገድ መስፋፋቱን ይረዳሉ፡፡

## ዋናዋነ ነጥቦች

ተማሪዎች ስለ ጥንት ዘመን መንግስታትና ባህርያት መማራቸውን ለይቶ ማወቅ አስፈላጊ ነው፡ ፡ በታችኛው ክፍል ተምረው ያለፉትን እንዲገልጹ ዕድል መስጠት አለባችሁ፡፡ በመቀጠልም ከመካከለኛ ክፍለ ዘመን የአለም ስልጣኔ ውስጥ አንዱ የባይዛንታይን ኢምፓየር እንደሆነ መረዳት አስረላጊ ነው፡፡ የምዕራብ ሮማ እና የባይዛንታይን ኢምፓየሮች አስተዳደር ተመሳሳይነትና ልዩነት በጥልቀት መረዳት ይገባል፡፡ በዚህ ሁኔታ ምዕራብ ሮማ በ476 ዓ.ም መውደቅ ለባይዛንታይን ኢምፓየር መመስረት የፈጠረውን ዕድል በማወቅ ዝግጅት ማድረግ፡፡

የባዛንታየን ኢምፓየር ባህሪያትን፣የመካከለኛውን ክፍለ ዘመን እና ዘመናዊ የአለም ስልጣኔዎችን በማነፃፀር መገምገም አስፈላጊ ነው፡፡ ለባዛንታየን ኢምፓየር መመስረት፣ መስፋፋትና መውደቅ ምክንያት የሆኑትን አብይ ነጥቦችን ለይቶ ማወቅ አስፈላጊ ነው፡፡

በመቀጠልም ስለ እስልምና ሀይማኖት የትና መቼ እንደተመሰረተ እና እንዴት እንደ ተስፋፋ በአግባቡ ማወቅ አስፈላጊ ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ የእስልምና ሀይማኖት በመጀመሪያው 7ኛ ክፍለ ዘመን በሳውዲ አረቢያ (መካና መዲና) አከባቢ በነቢዩ ሙሀመድ ትምህርት ተጀመረ፡፡በአፍሪካ ቀንድ የእስልምና ሀይማኖት ሰላማዊ በሆነ መንገድ መስፋፋቱን መረዳት ዋና ነጥብ ነው፡፡ በተቃራኒው ወደ መካከለኛው ምስራቅ፣ ሰሜንና መካከለኛው አፍሪካ፣ ወደ ደቡብና ደቡብ ምስረቅ ኤሽያ የእስልምና ሀይማኖት የተስፋፋው በጦርነት መሆኑን እንደ ዋና ነጥብ አደራጁ፡፡ የእስልምና ሀይማኖት ትምህርት የሰው ልጅ ከመጥፎ ስራና ከክፉ ድርጊት እንዲቆጠብ የሚያስተምር መሆኑን መረዳት አስፈላጊ ነው፡፡ የእስልምና ሀይማኖት ከሌሎች ሀይማኖቶች ጋር ያለው ግንኙነት ምን እንደሚመስል በማስተያየት ማደራጀት ያስፈልጋል፡፡

## ቅድመ ዝግጅት

ስለ መካከለኛውን ክፍለ ዘመን ከማስተማራችሁ በፊት በቂ ዝግጅት ማድረግ ይኖርባችኋል፡፡ በዚህ መሰረትስለ ባይዛንታይን ኢምፓየር ትርጉም፣ ባህሪና የመካከለኛውን ክፍለ ዘመን ባህሪና የእስልምና ሀይማኖት በተመለከተ የተለያዩ ምንጮችን በማንበብ መዘጋጀት አስፈላጊ ነው፡፡ የእስልምና ሀይማኖት የት እንደተመሰረት፣ እንዴት እንደ ተስፋፋ እና የእስልምና ሀይማኖት ትምህርት ስለ ሰው ልጅ ሰላም እና መብት የሚያስተምር መሆኑን መረዳት አስፈላጊ ነው፡፡ በዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ ውስጥ የመምህሩንና የተማሪውን ተግባር በጥራት መካተት አለበት፡፡ በተጨማሪም የትምህርት መርጃ መሳሪያ መጠቀም አስፈላጊ ነው፡፡ የአለም ካርታን በመጠቀም የባይዛንታይን ኢምፓየርና የእስልምና ሀይማኖት የተስፋፋበትን አካባቢ እንዲያሳዩ ማድረግ፡፡ ከተቻለ የባይዛንታይን ኢምፓየር አስተዳደር ግዛት በሚታይ መልኩ ማዘጋጀት፡፡

በካርታ ላይ የእስልምና ሀይማኖት ወደ አውሮፓ፣ ደቡብ እና ደቡብ ምስራቅ ኤሺያ እና በአፍሪካ አህጉር እንዴት እንደተስፋፋ የሚያሳይ ካርታ ማዘጋጀት፡፡ በተለይ በሰላማዊ መንገድ ወዴትና እንዴት እንደተስፋፋ ካርታ ወይም ፖስተር በማዘጋጀት ለተማሪዎች ማሳየት ይጠበቅባችኋል፡፡በተጨማሪም በአካባቢያችሁ የሚገኙ ቁሳቁሶችን በመጠቀም የትምህርት መርጃ

መሳሪያ በማዘጋጀት ለመማር ማስተማር ሂደት መጠቀም ይኖረባችቸዋል፡፡ በመጨረሻም የባይዛንታይ ኢምፓየር ለሚለውን ንዑስ ርእስ **አራት ክፍለ ጊዜና** የእስልምና ሀይማኖት የት እንደተመሰረተና እንዴት እንደተስፋፋ ለሚለውን **ሶስት ክፍለጊዜ** መጠቀም፡፡በአጠቃላይ **ሰባት ክፍለ ጊዜያትይሆናሉ፡፡** ይህንን ክፍለ ጊዜ ከትምህርት ዕቅዳችሁ ይዜት ጋር አብሮ መሄዱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

## የመማር ማስተመማር ዘዴ

ይህን ርእስ ለማስተማር የተለያዩ የመማር ማስተማር ዘዴዎችን መጠቀም አለባችሁ፡፡ከእነዚህ የመማር ማስተማር ዘዴዎች ለትምህርቱ ምቹ የሆነውን መምረጥ፡፡ እንዲሁም የባይዛንታየን ኢምፓየር ታሪክ በማስመልከት አሳይመንትና ምንባብ ለተማሪዎች መስጠት፡፡የአለም ካርታን በመጠቀም የባይዛንታይን ኢምፓየር የተስፋፋበትን አካባቢ እንዲለዩ ማድረግ፡፡ የመካከለኛ ክፍለ ዘመን የአለም ስልጣኔና የባይዛንታየንኢምፓየርን በማስተያየት እንዲያመዛዝኑ ማድረግ፡፡

የክፍሉ ተማሪዎችን በአራት/አምስት ቡድን በመክፈል የባይዛንታይንኢምፓየር ባህሪ ላይ እንዲወያዩ በማድረግ የተወያዩበትን ደግሞ በክፍል ውስጥ እንዲገልጹ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ በተለይ በፊውዳሊዝም ስርዓት ላይ በጥልቀት እንዲወያዩ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በባይዛንታይን ኢምፓየር የታዩትን ዕድገትና ለውጦች እንዲገልጹ ማድረግ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ በተጨማሪም የባይዛንታይን ኢምፓየር ከሌላ ሀገሮች ጋር የነበረውን ግንኙነት ምን እንደሚመስል እንዲወያዩበትና እንዲያቀርቡ ማድረግ ከመማር ማስተማር ዘዴዎች ውስጥ ዋናው ነው፡፡

የእስልምና ሀይማኖት መመስረትና መስፋፋት ላይ ተማሪዎች እንዲወያዩ ማድረግ የተመረጠ የማስተማር ዘዴ ነው፡፡ ነገር ግን ተማሪዎች ተገቢ ያልሆነ ውይይት ዉስጥ እንዳይገቡ መከታተል በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ምክንያቱም የሀይማኖት ጉዳይ ስሜት የሚያነሳሳ ከመሆኑ የተነሳ አላስፈላጊ ግጭት ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡ ከዚህ በላይ ስለ ክርስትና ሀይማኖት አጀማመርና መስፋፋት የተገለጹትን በማንበብ የማስተማር ዘዴዎች በመጠቀም ተጠቀሙበት፡፡ በመጀመሪያው ሄጂራ የአክሱም መንግስትና የአረብያ ሙስሊሞች ያላቸውን ግንኙነት ማስረዳት አስፈላጊ ነው፡፡

የእስልምና ሀይማኖት እሴቶችን ተማሪዎች በነፃነት እንዲገልጹ በማድረግየእስልምና ሀይማኖት መመስረትና መስፋፋት ላይ በቂ እውቀት እንዲያገኙ ማዲረግ ማግኘት ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም በገለፃ፣ ውይይት፣ማነፃፀር፣ ማመዘን፣ ጥያቄና መልስ፣ በቅደም ተከተል ማስቀመጥ እና ከመሳሰሉትዘዴዎች ዉስጥ የሚመቹትንስራ ላይ ማዋል ተገቢ ነው፡፡ትልቁ ትኩረትና ግንዛቤያችሁ ደግሞ ሁሉን አቀፍና አሳታፊ የሆነ የመማር ማስተማር ዘዴ መጠቀም መዘንጋት የለበም፡፡ በተጨማሪም የፆታ እኩልነትን ማረጋገጥ እና የልዩ ፍላጎት ተማሪዎችን መደገፍ ተገቢ ነው፡፡

## ልዩ ተሰጥዖ ያላቸዉን ተማሪዎች መርዳት

የተለያዩ ቅርፃ ቅርፆን ለመስራት ፍላጎት ያሳዩትን እና ችሎታ ያላቸዉንና ካርታን ማንሳት፣ ግጥም መፃፍና ክፍሉን የሚጥኑ አዳዲስ አስተሳሰቦችን የሚያመነጩትን ማበረታታት አስፈላጊ ነዉ። በተጨማሪም በቡድናቸዉ ዉስጥ የተሰጣቸዉን ስራ ቀድመዉ የጨረሱትን ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ይበልጥሊያስገነዝቧቸዉ የሚችሉትን ጥያቄዎች በተጨማሪ መስጠት ያስፈልጋል።

## ተከታታይ ምዘና

በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ተከታታይ ምዘናማካሄድ አስፈላጊ ነው፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎችቢያንስሊኖራቸውየሚገባየትምህርትብቃት መምህራን ለማወቅ እንዲችሉ ስለሚረዳቸው ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የመማር ማስተማር ሂደታችሁን ጠንካራና ደካማ ጎን ለይቶ ለማወቅይጠቅማል፡፡ ደካማ ጎንን ለይቶ ማወቅ ደግሞለወደፊቱ ለማስተካከልና ለማቀድ ይጠቅማል፡፡ በዚህ ሁኔታ ተማሪዎች በቡድን የሚያደርጉት ተሳትፎ በመገምገም ለታዩት ደካማ ጎኖች ግብረ መልስ መስጠት፡፡

የአለም ካርታን በመጠቀም የባይዛንታይን ኢምፓየር የሚገኝበትና የተስፋፋበትን አካባቢ በመጠየቅ ምዘና አድርጉ፡፡ በተጨማሪምበካርታ ላይ የእስልምና ሀይማኖት የተስፋፋበትን መንገድ እንዲያሳዩ በመጠየቅ ምዘናና ግምገማ ማድረግ፡፡ በተማሪዎች መጽሐፍ ላይ ያለውን የሙከራ ጥያቄዎችንና በምዕራፉ ማጠናቀቂያ ያሉትን የመልመጃ ጥያቄዎችን በመጠየቅና በግላቸውም በማሰራትየተማሪዎችን ግንዛቤ መገምገም አስፈላጊ ነው፡፡

**የመልመጃ ጥያቄዎች መልስ**

**የመልመጃ.4.1. ጥያቄዎች መልስ**

1. ኩኒፎርም ይባላል
2. የሜሶፖታሚያን ወንጀልና መጥፎ ተግባራትን ለመቀነስ እንዲሁም ሰላምና መረጋጋትን ለማስፈን
3. በወንዞች ዳርቻ ላይ በመመሰረት የግብርናና የእደጥበብ ስራን ማሳደግ
4. ለህጎች መሰረት፣ ለዘመናዊ ፖሊቲካ፣ ለአስተዳደር ስረዓት እና የመሳሰሉት
5. ለም አፈር፣ በቂ ውሃ እና ምቹ አየር መኖራቸው

**የመልመጃ.4.2. ጥያቄዎች መልስ**

1. በሮማ ስልጣኔ ዘመን የወጡትን ህጎች ስራ ላይ እንዲውል ማድረግናጠንካራ የመንግስት አስተዳደርን በማዋቀር ይታወቃል
2. የስኑ-ህንፃ ሞያን በማሻሽል፣ የክርስትና ሀይማኖትን በማጠናከር፣ ስነ ፅሁፍን ማሳደግ እና የመሳሰሉት ናቸው
3. ሀይማኖትን ከአስተዳደር ጋር በማያያዝ ድንበር ማስፋፋት፣ የባለአባት ስርአትን መመስረት እና የመሳሰሉት ናቸው።
4. በ7ኛው ክፍለ ዘመን የአክሱም መንግስት ከአረብ ሀገሮች ጋር ጠንካራ ግንኙነት ስለነበረው ነው።

## የምዕራፍ 4 ማጠቃለያ ጥያቄዎች መልስ

**I. የእውነት/ሐሰትጥያቄዎች መልስ**

1.እውነት 2.ሐሰት 3. እውነት 4. እውነት 5. እውነት

**II. የአዛምድ ጥያቄዎች መልስ**

1. ሰ 2.ረ 3. መ 4. ሀ 5. ለ 6. ሐ

**III. የምርጫጥያቄዎች መልስ**

1. ለ 2.ለ 3. መ 4. ሀ 5. ለ 6.ሀ

# ምዕራፍ 5፡ቀደምት የአፍሪካ ታሪክ

**የክፍለ ጊዜ ብዛት------------9**

- ጥንታዊ የአፍሪካ ስልጣኔዎችን ይዘረዝራሉ
- የጥንታዊ የአለም ስልጣኔ አመስራረትን ያመዛዝናሉ
- የጥንታዊ ግብፅ ስልጣኔአመስራረትንያገናዝባሉ
- የጥንት ኑቢያ ስልጣኔ ልዩ የሚያደርገውን በመገንዘብ ያደንቃሉ
- የጥንት ኑቢያና ሜሮኤ ስልጣኔዎች ባህርያትን ያገነዘባሉ
- የአፍሪካ ሀገራትን ከቅኝ ግዛት በፊትና በኋላ ያሉትን ሁኔታዎችን በማስተያየት ይገመግማሉ፡፡

## መግቢያ

በምዕራፍ አራት ትምህርት ውስጥ በዓለም ላይ የተለያዩ ሀገሮች ስላጣኔ አመሰራረትና የተመሰረቱት ስልጣኔዎችም ለዓለም ማህበረሰብ ያበረከቱትን አስተዋጽኦ ግንዛቤ አግኝተዋል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ደግሞ ከቀደምት የአፍሪካ ስልጣኔዎችውስጥ የጥንታዊ ግብፅ ፣ኑቢያእናሜሮኤ አመሰራረትና ውድቀት ይማራሉ፡፡ ሦስቱ ስልጣኔዎች ከሁሉም አፍሪካ ሀገሮች ቀደምትና በጣም ታዋቂ የሆኑ ናቸው፡፡የጥንታዊ ግብፅ ስልጣኔ በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ አከባቢ የተመሰረተ ነው፡፡ የኑቢያናሜሮኤ ስልጣኔዎች ደግሞ በአሁኑ ሱዳን አካባቢየተመሰረቱ ቀደምት የአፍሪካ ስልጣኔዎች ናቸው፡፡

## 5.1. የጥንታዊ ግብፅ ስልጣኔ

**የክፍለ ጊዜ ብዛት-----------3**

**ማሪዎች ቢያንስሊኖራቸው የሚገባ የትምህርትብቃት:**

- የጥንታዊ ግብፅ ስልጣኔ ለዓለም ያበረከተዉን አስተዋጽኦ ይዘረዝራሉ
- ስለ ግብፅ ስልጣኔ አጀማመርና አወዳደቅ ይዘረዝራሉ
- የአፍሪካ መንግስታት በቀደምትና በመካከለኛው ክፍለ ዘመን የነበራቸውን ስልጣኔዎች ያመዛዝናሉ

## ዋና ዋና ነጥቦች

ጥንታዊ የግብፅ ስልጣኔ በሰሜን አፍሪካ አከባቢ የተመሰረተና ከአፍሪካስልጣኔዎች ውስጥ ቀደምትየሆነ ነው፡፡የአፍሪካስልጣኔ የሆነው የጥንታዊ ግብፅ ስልጣኔ ለዓለም ያበረከተው አስተዋጽኦ መረዳት አስፈላጊ ነው፡፡ የጥንታዊ ግብፅ ስልጣኔ የተጀመረው በ3000 ዓ.ዓ አከባቢ ሲሆን ለዓለም ማህበረሰብ በተለያዩ ዘርፎች ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡

ግብፃዊያን ለዓለም ማህበረሰብ ካበረከቱት የስልጣኔ ዘርፎች ውስጥ የሃይማኖት አመለካከት፣ ስነ-ሕዋ፣ሒሳብ እና የስነ-ህክምና ምርምሮችን ያካትታል፡፡ በተጨማሪም ሙያዊ ስራ በሆኑት በፒራሚድ ግንባታዎች፣የመቃብር ቦታ ግንባታዎች፣ስነ-ጹሁፎች፣የቀለምቅብ ስራ እና የሞተን ሰው ሬሳ ለረጅም ጊዜ የማቆየት ዘዴናቸው፡፡ በጥንታዊ ግብፅ ስልጣኔ የሞተን ሰው ሬሳ ለረጅም ጊዜ የማቆየት ዘዴ ሙሚፊኬሽን ሲባል ስነ-ፅሁፋቸው ደግሞ ሀይሮግሎፊክስ በመባል ይታወቃል፡፡

በተማሪዎች መጽሐፍ ላይ የተቀመጠውን ማብራሪያ መሰረት በማድረግ የጥንታዊ ግብፅ ስልጣኔ በጥልቀት መተንተን አስፈላጊ ይሆናል፡፡የጥንታዊ ግብፅ ስነ-ፅሁፍከዋና ዋና ነጥቦች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ እንዲሁምየጥንታዊ ግብፅ ምጣኔ ሀብት መሠረት ግብርናና የንግድ እንቅስቃሴ መሆኑን መረዳት በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ በተጨማሪም የጥንታዊ ግብፅ ነገስታት የነበሩ ፈርኦን ተብለው ይጠራሉ፡፡ የጥንታዊ ግብፅ ነገስታት ወይም ፈርኦን ባህሪያት እና ጠንካራ ጎኖቻቸውን ማደራጀት አስፈላጊ ነው፡፡

በ3100 ዓ.ዓ አከባቢ በላይኛውና በታቸኛው የናይል ወንዝ ሸለቆ የተቋቋሙ ሁለቱ የጥንታዊ ግብጾች መንግስታት አንድ የጋራመንግስት አቋቋመዋል፡፡ሌላው ዋናው ነጥብ ደግሞ የላኛውና የታችኛው ናይል ተፋሰስ የጥንታዊ ግብጾች ነገስታት በጋራ ሲጠቀሙ የነበሩትን አርማና በጋራ ያቋቋሙት መንግስት ላይ ገለጻ ማድረግያስፈልገል፡፡

የጥንታዊ ግብጾች ስልጣኔ ከጊዜ በኋላ ቀስ በቀስ ሊወድቅ ችሏል፡፡ለጥንታዊ ግብጾች ስልጣኔ መውደቅ ምክንያት የሆኑት ውስጣዊና ውጫዊ ምክንያቶ ናቸው፡፡ የውስጣዊና ውጫዊ

ምክንያቶችን በጥልቀት ለመረዳት በመጻሐፉ መጨረሻ ገጽ ላይ የተዘረዘሩትንዋቢ መጽሐፍት ፈልገው በማግኘት ሐሳቡን ማደራጀትአስፈላጊ ነው።







ስዕል 5.1.*ሀይሮግሊፍክስ የጥንታዊ ግብፅ ስነ-ጹሁፍ*

ጥንታዊ ግብጾች የኑቢያ ወይም ኩሽ መንግስትን ከወረሩት በኋላ ለረዥም ጊዚያት ማስተዳደር ችለዋል። ነገር ግን የኑቢያ(የኩሽ)መንግስትም በተራው ጥንታዊ ግብፅን በመውረር አስተድሯል፡ ፡ተማሪዎችን ይህንን ሐሳብ ማስጨበጥ በጣም አስፈላጊ ይሆናል፡




ካርታ 5.1 የጥንታዊ ግብጾች፣ኑቢያናሜሮኤ ስልጣኔዎችን የሚያሳይ

## ቅደመ ዝግጅት

መምህራንየጥንታዊ አፍሪካስልጣኔዎች(የግብፅ፣ኑቢያ እና ሜሮኤ) የሚያውቁትን ዋቢ መጽሐፍትን ፈልገው በማግኘት ግንዛቤያችሁን ማዳበር አስፈላጊ ነው፡፡እንዲሁም ተማሪዎች ስለ ጥንታዊ ግብፅ ስላጣኔዎች መስፋፋት በማስመልከት ዋቢ መጽሐፍትን በማንበብ ግንዛቤያቸውን እንዲያዳብሩ ማበረታ አስፈላጊ ነው፡፡

መምህራን! ስለ ጥንታዊ አፍሪካ ስልጣኔዎች ማስተማር ከመጀመራችሁ በፊት የአለምና የአፍካ ካርታ በማዘጋጀት የተለያዩ የጥንታዊ ስልጣኔዎች መገኛ ካርታማዘጋጀት ላይ መጠቆም አስፈላጊ ነው፡፡ መምህራን ይህንን የትምህርት መርጃ መሣሪያ ከትምህርት ቤቱ ማግኘት የማትችሉ ከሆነ በአከባቢያችሁ ከሚገኙ ቁሳቁሶችስርታችሁ መጠቀም ይችላል፡፡ እንዲሁም ፖስተሮችን፣ፎቶግራፎችን፣የፕራሚድ ስዕል፣ቅርጻቅርጾችን እና የቀደምት ስልጣኔዎች ቅሪተ አካላትን መጠቀም ትችላላችሁ፡፡በተመሳሳይፖስተሮችን እና ቅርጻቅርጾችን በአከባቢው ከሚገኙ ነገሮች በማዘጋጀት ለማስተማሪያነት መጠቀም ይቻላል፡፡

የዕለቱ ትምህርት ዕቅድ በጥራትናተማሪዎችን ባማከለ መልኩ ማዘጋጀት ተገቢ ነው፡፡ በዚህ የዕለት ትምህርት ዕቅድ ውስጥ የመምህራና የተማሪዎች ተግባራትን በመለየት በተሰጠው **ሶስት ክፍለ ጊዜ** ውስጥ ማጠናቀቅ ይገባል፡፡ ተማሪዎች ቢያንስሊኖራቸው የሚገባ

የትምህርትብቃት ማስረዳትና ማበረታታት አስፈላጊ ነው። መምህራን የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን ሲያዘጋጁየዕለት የትምህርት ዕቅድ ጋር ማጣጣም አስፈላጊ ነው።

## የመማር ማስተማር ዘዴ

ይህንን የትምህርት ይዜት ማስተማር ከመጀመራችሁ በፊት ተማሪዎች በምዕራፍ አራት ውስጥ የተማሩትን የዓለም ስልጣኔዎችን እንዲያብራሩ ዕደል ይሰጡአቸው።ተማሪዎችን የማሳተፍ ዘዴም ትምህርቱን ወደ ላይና ወደ ጎን ለማያያዝ ይረዳል። ምክንቱም የተማሪዎች ግንዛቤ በምን ደረጃ ላይ እንደምገኝ ለመለየት የሚረዳ ዘዴ ነው።

በመቀጠልም የአፍሪካ አህጉር ካርታን በማዘጋጀት ለትምህርት መርጃነት መጠቀም ይቻላል። ተማሪዎች የአፍካ አህጉር ከሌሎች አህጉራት ጋር የነበረውንግንኙነትና ትስስር እንዲያብራሩ ዕደል ይሰጣችው። አንዳንድየአውሮፓ አገራት አህጉራት ለአፍሪካ አህጉር ስልጣኔዎች ያላቸው አስተሳሰብ ዝቅተኛ መሆኑንተማሪዎችን ማስረዳት ያስፈልጋል። ይሁን እንጂ የአፍሪካ አህጉር ከጥንት ዘመን ጀምሮ እስከ መካከለኛ ክፍለ ዘመን የተለያዩ ስልጣኔዎች የተስፋፋበት አህጉር መሆኑን በግልፅ ተማሪዎችን ማስረዳት አስፈላጊ ነው።

ከተለያዩ የመማር ማስተማር ዘዴዎች ውስጥ ምቹ የሆነሁንና የትምህርት ይዘቱ በቀላሉ ለማስጨበጥ የሚረዳ የመማር ማስተማር ዘዴ መምረጥ ተገቢ ነው።ለምሳሌተማሪዎች የአፍሪካ አህጉር ካርታን በማዘጋጀት የጥንታዊ ግብፅ ስልጣኔ መገኛ እንዲያሳዩና የተለያዩ የፕሮጀክት ስራ እንዲሰሩ ማድረግ ያስፈልጋል። በተጨማሪም ተማሪዎች የተለያዩ የጥንታዊ ግብፅ ስልጣኔ መገለጫ የሆኑትን ቅርጻቅርጾችንና ፒራሚዶችን በስዕል መልክ በግልና በቡድን ሰረተው እንዲያቀርቡ ማድረግ ያስፈልጋል። በአከባቢያቸው ከሚገኙ ቁሳቁሶች ነገሮች ለምሳሌ ጭቃ፣ እንጨት እና ከካርቶንተጠቅመው የጥንታዊ ግብፅስላጣኔዎችመገለጫ የሆኑትንአስመስሎ እንዲሰሩ ተማሪዎችን ማገዝ ወይም ማሰራት ተገቢ ነው ።

ከተለያዩ የመማር ማስተማር ዘዴዎች ለምሳሌ ተማሪዎችን ከሰርቶ ማሳያ፣ ሪፖርት ዘዴ፣ እርስ በርስ ውይይት እና ከማመዛዘን ዘዴዎች ውስጥ ምቹ የሆነውን መርጠው መጠቀም አስፈላጊ ነው።የክፍሉን ተማሪዎች በሶስት ወይም በአራት ቡድን በማደራጀትቀደምት የዓለም ስልጣኔዎችን እንዲያመዛዝኑ ማድረግ።ተማሪዎች ከውይይታቸው በኃላ የተገነዘቡትን

እንዲያብራሩ ዕድል መስጠት፡፡ በመጨረሻም ሁሉም ተማሪዎች ያቀረቡትን በማጠቃለል የጋራ ግንዛቤ ላይ እንዲደረሱ ማድረግ አስፈላጊ ነው

በአጠቃላይ መምህራን ሁሉንም የተማሪዎች ግንዛቤ ደረጃ ማዕከል ያደረገና አሳታፊ የመማርማስተማር ዘዴስለመጠቀማችሁ እርግጠኛ መሆን አለባችሁ፡፡በተጨማሪምለሁለቱም ጾታዎች እኩል የመሳተፍ ዕድል የሚሰጥ የመማር ማስተማር ዘዴመጠቀም አስፈላጊ ነው፡፡

## ልዩ ተሰጥዖ ያላቸዉን ተማሪዎች መደገፍ

ልዩ ተሰጥዖና ከፍተኛ ግንዛቤ ያላቸዉን ተማሪዎች በመደገፍ የፈጠራ ችሎታቸዉን እንዲያዳብሩ ማበረታታት አስፈላጊ ነዉ።ለምሳሌ ካርታ ማንሳትና ስዕል የመሳል ሞያ መለማመድ የሚፈልጉ ተማሪዎች ካሉ አበረታታቸዉ/ቿያዉ። በቡድናቸዉ ዉስጥ የተሰጣቸዉን ስራ ቀድመዉ የጨረሱ ተማሪዎችም ካሉ በተጨማሪ ሊሰሩ የሚችሉትን ጥያቄ መስጠት ተገቢ ነዉ።እነኝህም ጥያቄዎች እየተማሩት ካለዉ ርዕስ ዉስጥ ሳይወጣ በተቀራራቢ ይዜት በማዘጋጀት ሊሰጣቸዉ ይገባል።

## ተከታታይ ምዘና

የተማሪዎችን ተሳትፎና ግንዛቤ በመገምገም የብቃታቸውን ደረጃ መለካት አስፈላጊ ነው፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች ቢያንስ ሊኖራቸው የሚገባ የትምህርት ብቃት ማወቅ ተገቢ ስለሆነ ነው፡፡ተማሪዎች በቡድንና በግል ስራ የሚያደርጉትን እንቅቃሴዎችበዕለታዊ መዝብብ ላይ በተከታታይ መያዝ አስፈላጊ ነው፡፡ ገንቢ ግብረ መልስ በመስጠት የተማሪዎች ግንዛቤ ማሳደግአስፈላጊ ነው፡፡ እያንዳንዱን የተማሪዎች ባህሪይ ለውጥ በተከታታይ መመዘገብና መያዝ ያስፈልጋል፡፡

ተማሪዎች የጥንታዊ ግብፅ ስላጣኔዎች መገለጫ የሆኑትን አስመስሎ እንዲሰሩ በማድረግ ግንዛቤያቸውን እንዲያሳድጉ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡በመጨረሻም ተማሪዎች በዚህ የትምህርት ይዜት ውስጥ ያሉትን የተግባር ስራና መልመጃዎችን እንዲሰሩ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ በመጨረሻም ትክክለኛ ግብረ መልስ መስጠት በጣም አስፈላጊ ነዉ፡፡

## 5.2. የጥንታዊ ኑቢያ /ኩሽ/ስልጣኔ

**የክፍለ ጊዜ ብዛት------------ 3**

**ተማሪዎች ቢያንስሊኖራቸው የሚገባ የትምህርትብቃት:**

- የጥንታዊ ኑቢያ ስልጣኔ የት እንደተጀመረ ይገልፃሉ
- የጥንታዊ ኑቢያና ሌሎች የአፍሪካ ሀገሮች ስልጣኔዎች ያላቸውን ግንኙነትን ያብራራሉ
- የጥንታዊ ኑቢያ ስልጣኔ ለዓለም ያበረከታቸውን ይገልጻሉ

### ዋና ዋና ነጥቦች

በዚህ ትምህርት ይዜት ውስጥ ትኩረት የሚሰጠው የጥንታዊ ኑቢያ ስልጣኔ መገኛና ለዓለም ያበረከታቸው ስልጣኔዎች ነው።ጥንታዊየኑቢያ ስልጣኔ በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ አከባቢ በአሁኑ ሱዳን አከባቢ የተመሰረተ ነው። ይሁን እንጂ የጥንታዊ ኑቢያ ስልጣኔ አመሰራረት በተመለከተ ተጨባጭ መረጃ አልተገኘም።ነገር ግን የጥንታዊ ኑቢያ ስልጣኔ የኩሽ ስልጣኔ በመባል ይታወቃል።የተለያዩ የታሪክ መረጃዎች እንደሚያመልክቱት የኩሽ ሕዝቦች በቆላማ ኑቢያ አከባቢ ሲኖሩ እንደነበሩ ነው።

የጥንታዊኑቢያ ምጣኔ ሀብት መሰረት ግብርናና ንግድ መሆኑን እንደ ሁለተኛ የትኩረት ነጥብ መያዝ ያስፈልጋል።የግብርና ስራውም በይበልጥ በእንስሳት እርባታ ላይ ያተኮረ ሲሆንየንግዱ ስራ ደግሞ የተለያዩ ጥሬ ዕቃዎች ዝውውር ላይ ያተኩራል።የጥሬ ዕቃዎች ዓይነት የዝሆን ጥርስ፣ የተለያዩ እንስሳቶች እና ወርቅ ናቸው።

ተማሪዎች በቀላሉ የትምህርቱን ይዜት መረዳት በሚችሉበት መንገድዋና ዋና ነጥቦችን ማደራጀት አስፈላጊ ነው። በተለይ የጥንታዊግብፅና ኑቢያ ትስስርና የተወራረሱትንስልጣኔዎች ለይተው ማውቅ አስፈላጊ ነው። በተመሳሳይ መልኩ የሁለቱ ስልጣኔዎች ትስስርና ለአለም ያበረከቱትን አስተዋጽዎለመለየት የተለያዩ ዋቢ መጽሐፍቶችንበማንበብ ዋናዋና ነጥቦችን ማደራጀት አስፈላጊ ነው።

# ቅደመ ዝግጅት

መምህራን ይህንን የትምህርት ይዜት ማስተማር ከመጀመራችሁ በፊት የኑቢያ ስልጣኔዎች ከተለያዩ የማጣቀሻ መጽሐፍት በማጠናከር ቅድመ ዝገጅት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡የኑቢያ ህዝቦች ስልጣኔዎች ለዓለም ያበረከቱትን አስተዋጽኦ ከተለያዩ መረጃዎች በማቀናጀት ትክክለኛ ግንዛቤ መያዝ ያስፈልጋል።ምክንያቱም የዓለምና የአፍሪካ ስልጣኔዎችኑቢያን ጨምሮበቂ ግንዛቤ ማግኘት ከቅደመ ዝገጅቶች ውስጥአንዱ ነው፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ የጥንታዊ ኑቢያስልጣኔ መስፋፋት ሂደት የሚያሳይ ካርታ ማዘጋጀትከቅደመ ዝግጅቶች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ የጥንታዊ ግብፅስልጣኔን ለማስተማር ያዘጋጃችሁ ካርታ ለጥንታዊ ኑቢያስልጣኔማስተማሪያመጠቀምትችላላችሁ፡፡ ይሁን እንጂ የኑቢያ ስልጣኔዎች መገኛ ቦታዎች የሚያሳይ ካርታ አስቀድመው በማዘጋጀት ለማስተማሪያነት መጠቀም አሰፈላጊነው፡፡ በተመሣሣይ የተለያዩ ስዕሎች፣ፎቶግራፎች እና ፖስተሮችን በመጠቀም የጥንታዊኑቢያ ስልጣኔዎችን ማሳየት ይቻላል፡፡ እነዚህ ስዕሎች፣ፎቶግራፎች እና ፖስተሮች በትምህት ቤቱ ተሰርተው ካሉ ፈልገው በማግኘት ለማስተማሪያነት መጠቀም ያስፈልጋል፡፡ በትምህርት ቤቱ ያሉ መርጃ መሣሪዎች ለማስተማሪያነት የማያገለግሉ ከሆኑ በማሳደስ መጠቀም ያስፈልጋል፡፡ ከተለያዩ መረጃዎች የአፍሪካ አህጉር፣በተለይ የኑቢያ ስልጣኔ የሚያመለክቱ ፅሁፎች እና የማጣቀሻ መጽሐፍት በመምህሩ መጽሐፍ መጨረሻ ገጽ የተዘረዘሩትንዋቢመጽሐፍት ፈልገው በማንበብመረጃዎችን ማጠናከር ያስፈልጋል ፡፡

መምህራን ከተለያዩ መርጃ መሳሪዎችና ከተለያዩ የማጣቀሻ መጽሐፍት ስለ ኑቢያ ስልጣኔ መረጃዎችን ካጠናከሩ በኃላ ግልጽ የሆነ ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ ማዘጋጀትተማሪዎች ቢያንስ ሊኖራቸው የሚገባ ብቃቶችንበግልጽ ለማስጨበጥ ይረዳል፡፡ በአከባቢ በሚገኙ የተለያዩ ቅርጻቅርጾችን በማዘጋጀት ለማስተማሪያነት በመጠቀም ትምህርቱን ተጨባጭ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ይህንን የትምህርት ይዜት ለማስተማር የተሰጠው የክፍለ ጊዜ ብዘት ሦስት (3) ስለሆነ ዕለታዊ ዕቅዳቸችሁን ከተሰጠው ጊዜ ጋር ማጣጣም ያስፈላጋል፡፡

## የመማር ማስተማር ዘዴ

ይህንን የትምህርት ይዜት ማስተማር ከመጀመራችሁበፊት ተማሪዎችንስለ ጥንታዊግብፅ ስልጣኔ ማስታወስ ያስፈልጋል።ተማሪዎች በዚህ ርዕስ እንዲማሩ የታቀደው ይዜት ና በፊት የተማሩትን በማስተያየት የተማሪዎችን ግንዛቤ ማጠናከር ከመማር ማስተማር ዘዴ አንዱ ነው፡ ፡

የአፍሪካ አህጉር በጥንታዊና መካከለኛ ክፍለ ዘመን ምን ዓይነት ታሪክ እንደነበረው ተማሪዎችን ማስገንዘብ ያስፈልጋል። ከተማሪዎች ውስጥ ግንዛቤ ያላቸው ካሉበፍላጎታቸው እንዲያብራሩ ማድረግ ይቻላል። የግንዛቤያቸውን ደረጃ ከተረዳችሁ በኃላ ተማሪዎች ቢያንስ ሊኖራቸው የሚገባ ብቃት እንዲጎናጸፉማድረግ። ተማሪዎች በመጻፋቸው (5.2) ላይ የተሰጡትን የሙከራ ጥያቄዎች በቡድንና በግል ሆነው እንዲሰሩ ማበረታታ ያስፈልጋል።

የዚህን ትምህርት ይዜት ለማሰተማርምቹየሆነውን የመማር ማስተማር ዘዴዎች ውስጥ መርጠው መጠቀም ይኖርባችኋል። ለምሳሌ የኑቢያ ምጣኔ ሀብት መሰረት የሆነውንና ከጥንታዊ ግብፅ ጋር ያላቸውን ትስስር በቡድን እንዲወያዩበት ማድረግ። ተማሪዎች በቡድን ሆነው የጥንታዊ ኑቢያ ስልጣኔ የሚያሳዩ የተለያዩ ቅርጻ ቅርጾችን ከተለያዩ በአከባቢያቸው ከሚገኙ ቁሳቁሶች እንዲያዘጋጁ ማበረታታት አስፈላጊ ነው።

በተጨማሪም ተማሪዎችንበክፍል ውስጥ በሶስት ወይም በአራት ቡድን በማደራጀት ስለጥንታዊ የአፍሪካ ስልጣኔዎች በማመዛዘን ግንዛቤ እንዲያገኙ ማበረታታት ያስፈልጋል።ተማሪዎች በውይይታቸው ያገኙትን ግንዛቤካቀረቡ በኃላ ገንቢ የማጠቃለያ ሐሳብ መስጠት የተመረጠ ነው፡ ፡ ከተለያዩ የመማር ማስተማር ዘዴዎች ለምሳሌ ከውይይት፣ከሰርቶ ማሳየት፣ከሪፓርት እና ከማመዛዘን ዘዴዎች ውስጥ ለትምህርት ይዘቱምቹ የሆኑትን መርጠው መጠቀም ያስፈልጋል።ከመማር ማስተማር ዘዴዎች ውስጥ በውይይት፣የፕሮጀክት ስራማሰራት እና ሪፖርት ማካሄድ የተሻሉ ናቸው። በተመሣሣይ ከመማር ማስተማር ዘዴዎች ውስጥ ሁለቱን ጾታ ያማከለንመጠቀም ትኩረት ከሚፈልጉ ጉዳዮች አንዱ መሆኑን ማወቅ ያስፈልጋል።

**ልዩ ተሰጥዖ ያላቸዉን ተማሪዎች መደገፍ**

ልዩ ተሰጥዖና ከፍተኛ ግንዛቤ ያላቸዉን ተማሪዎች በመደገፍ የፈጠራ ችሎታቸዉን እንዲያዳብሩ ማበረታታት አስፈላጊ ነዉ። ለምሳሌ ካርታ ማንሳትና ስዕል የመሳል ሞያ መለማመድ/መሞከር የሚፈልጉ ተማሪዎች ካሉ አበረታታቸዉ/ቿያዉ። በቡድናቸዉ ዉስጥ የተሰጣቸዉን ስራ ቀድመዉ የጨረሱ ተማሪዎችም ካሉ በተጨማሪ ሊሰሩ የሚችሉትን ጥያቄ መስጠት ተገቢ ነዉ።እነኝህም ጥያቄዎች እየተማሩት ካለዉ ርዕስ ዉስጥ ሳይወጣ በተቀራራቢ ይዜት በማዘጋጀት ሊሰጣቸዉ ይገባል።

## ተከታታይ ምዘና

ተማሪዎች በቡድንና በግላቸው የሚያደርጉት ተሳትፎ በመገምገም የብቃታቸውን ደረጃ መለካት አስፈላጊ ነው፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች ቢያንስ ሊኖራቸውየሚገባየትምህርት ብቃት ለማስጨበጥ የሚረዱ ዘዴዎችን ማወቅ ተገቢ ስለሆነ ነው፡፡ተማሪዎች በካርታ ላይ የኑቢያ ስልጣኔ የት እንደተጀመረ እንዲያሳዩ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡የኑቢያ ስልጣኔ ለዓለም ስልጣኔ ያበረከታቸው አስተዋጽዖዎችንተማሪዎች እዲናገሩ ዕድል መስጠት ያስፈልጋል፡፡እገዛ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ካሉማበረታታና ገንቢ ግብረ መልስ መስጠት ተገቢ ይሆናል፡፡ በመጨረሻ ላይ ተማሪዎች የሙከራ ስራና መልመጃዎችን በትክክል መስራታቸውን መከታተልና ብቃታቸውን መገምገም ያስፈልጋል፡፡

## 5.3. ጥንታዊ የሜሮኤ ስልጣኔ

**የክፍለ ጊዜ ብዛት------------3**

**ተማሪዎች ቢያንስ ሊኖራቸው የሚገባ የትምህርትብቃት:**

- ከቅኝ ግዛት በፊት የአፍሪካ አህጉር ነገስታት ሁኔታ ያመዛዝናሉ
- ጥንታዊ የሜሮኤ ስልጣኔ ለዓለም ያበረከታቸውን አስተዋጽዖ ይገልጻሉ
- የጥንታዊ ሜሮኤ ዋነዋና ስልጣኔዎችን ያመዛዝናሉ

## ዋናዋና ነጥቦች

ከአፍሪካ አህጉር የጥንታዊ ሜሮኤ ስልጣኔ በብረታ ብረት ወይም ብረታ ብረትን በማቅለጥ ስራ ይታወቃሉ፡፡ሜሮኤ በ5ኛው እና በ4ኛው ዓ.ዓብረታ ብረት የማቅለጥ ሙያ ሲያስፋፉ ነበር፡፡

በዚህ መሰረት የሜሮኤ ብረታ ብረት ስራ ለሰው ልጆች ምርትና ምርታማነት መሻሻል ምክንያት መሆኑን አስቀድመው ማወቅ ያስፈልጋል።የጥንታዊ ሜሮኤ ስልጣኔ የኩሽ ስልጣኔ በመባልም ይታወቃል።የጥንታዊ ሜሮኤ ስልጣኔ የምስራቅ አፍሪካ የብረታ ብረት ማቅለጫ ማዕከል በመባል ይታወቃል።

እንደ ጥንታዊ ግብፅና ኑቢያ የሜሮኤምጣኔ ሀብት መሰረት ግብርናና የንግድ ስራዎችናቸው። የጥንታዊ ግብፅ፣ኑቢያ እናሜሮኤ ስልጣኔዎችን ትስስራቸውና ልዩነቶቻቸውን ማመዛዘን አስፈላጊ ነው፡፡መምህራን የጥንታዊ ግብፅ፣ኑቢያ እና ሜሮኤ ስልጣኔዎችን የአፍሪካን ካርታ በመጠቀም መገኛቸውን አስቀድመው ማቀናጀት ያስፈልጋል።

መምህር!የጥንታዊ ሜሮኤ ስልጣኔ የተቋቋመው በአሁኑ ሱዳን አከባቢ መሆኑን የተለያዩመረጃዎችን በመጠቀም ግንዛቤያችሁን ማጠናከር አስፈላጊ ነው፡፡በተጨማሪም ጥንታዊ ሜሮኤ ለ400 ዓመታት በጥንታዊ ግብፅበመውረር በግብፅ አስተዳደር ስር ቆይቷል። መምህራን አስቀድመው የጥንታዊ ግብፅና ሜሮኤ ስልጣኔዎች የተወራረሱ መሆናቸውን በመለየት ተገቢውን ዝግዝት ማድረግ ይኖርባችኋል።ነገር ግን ከ730-670ዓ.ዓ አከባቢ የሜሮኤና ኑቢያ ህዝቦች በጋራ በመሆን የፖሊቲካና ምጣኔ ሀብት የበላይነትን በመቆጣጠር ለ60 አመታት ጥንታዊ ግብፆችን አስተዳድረዋል፡፡ይህ የሚያመለክተው በጥንታዊ ዘመን አንዱ አንዱን በጉልበት በግዛቱ ስር በማስገባት የተነሳ ስልጣኔዎቻቸው ሲወራረሱ መቆየታቸውን አስቀድማችሁ መረጃ በማጠናከር ቅድመ ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል።

በመጨረሻም ለጥንታዊ ሜሮኤ ስልጣኔ መውደቅ ምክንያት የሆኑትን ማጠናከር ያስፈልጋል፡፡ ለጥንታዊ ሜሮኤ መዳከም የጥንታዊ አክሱም መንግስት የተጫወተውን ሚና ለተማሪዎች ማብራራት አስፈላጊ ነው፡፡ በመጨረሻም በአክሱም መንገግስት ወረራም ክንያትበ350 ዓ.ም ሜርኤ ልትፈርስ መቻሏ ከዋና ዋና ነጥቦች ውስጥ አንዱ ነው፡፡

## ቅደመ ዝግጅት

መምህር!ይህንን የትምህርት ይዜት ማስተማር ከመጀመርዎ በፊት ከተለያዩ መረጃዎች ስለ ሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ስልጣኔ ዋና ዋናነጥቦችን ማዘጋጀት ያስፈልጋል። በመምህሩ መመሪያ መጽሐፍ በመጨረሻ ገጽ ላይ የተዘረዘሩትን የማጣቀሻ መጽሐፍት መጠቀም ያስፈልጋል።

የጥንታዊ ግብፅና ኑቢያ ስልጣኔዎችን ለማስተማር የተጠቀሙትን ካርታ ለሜሮኤ ስላጣኔ ማስተማሪነትብትጠቀሙ የተሻለ ነው፡፡ የዓለም ዋና ዋና ስልጣኔዎቸን የሚያሳይ ካርታ ከሜሮኤ ስላጣኔ መገኛ እና መስፋፋት ጋር ያለውን ትስስር ማመዛዘን ያስፈልጋል፡፡በዕለታዊ የትምህርት ዕቅዳችሁ ውስጥ የትምህርቱን ዋና ዓላማ፣ የትምህርት መርጃመሳሪያ እና የመምህራንና የተማሪዎችን ተግባራትን ለይቶ ማስቀመጥ ያስፈልጋል፡፡ በመጨረሻም የትምህርቱን ይዜት ና ዕቅድበተሰጠው ክፍለ ጊዜ ማጠናቀቅ አስፈላጊ ነው፡፡

## የመማር ማስተማር ዘዴ

በመማሪያ ክፍል ውስጥ የሚንጸባረቁትን የተማሪዎች ስነ ምግባር መከታተል ያስፈልጋል፡፡ ተማሪዎች ያለፈውን የትምህርት ጭብጠ ሀሳብ እንዲገልጹ በማድረግ ከዕለቱ ርዕስ ጋር ማስተሳሰር አስፈላጊ ነው፡፡ ይህን የማስተማር ዘዴ በመጠቀም ከአፍሪካ ስልጣኔዎች ውስጥ የጥንታዊ ግብፅናኑቢያን እና ሜሮኤ በማነጻጸር እንዲገነዘቡማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በመጨረሻም ተማሪዎች ቢያንስ ሊኖራቸው የሚገባ የትምህርት ብቃት እዲያጎለብቱ ማድረግ፡፡ተማሪዎች ሁሉንም የሙከራና የመልመጃ ጥያቄዎችን በቡድን በመወያየት በትክክል እንዲመልሱ ማድረግ ፡፡

በመቀጠል የጥንታዊ ሜሮኤ ስልጣኔ የተስፋፋበትን ቦታ ለማሳየት የሚረዳ ካርታን ለማስተማሪያነትበማዘጋጀት ተማሪዎች እንዲያሳዩ ማድረግ፡፡ በክፍል ውስጥ የሚገኙ የተማሪዎችን ብዛት መሰረት በማድረግ በአምስት ወይም ስድስት ቡድን በማደራጀት በጥንታዊ ሜሮኤስልጣኔ ላይ ውይይት እንዲያደርጉ መምራት ያስፈልጋል፡፡በቀጣዩ የትምህርትክፍለ ጊዜ ተማሪዎች በአከባቢው ከሚኙ ነገሮች ለምሳሌ ከአፈር፣ካርቶን፣ እና ከእጨትየጥታዊ ሜሮኤ ስላጣኔ የሚያሣዩ ቅርጻቅርጾችን ሰርተው እንዲያቀርቡ ማድረግ፡፡እንዲሁም ጥንታዊ የሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ስላጣኔዎችን እንዲያመዛዝኑ ማድረግ ያስልጋል፡፡ያታን ያማከል የመማር ማስተማር ዘዴ መጠቀምም ትኩረት ከሚሰጡባቸው ጉዳዩች ውስጥ አንዱ ነው፡፡

## ልዩ ተሰጥዖ ያላቸዉን ተማሪዎች መደገፍ

ልዩ ተሰጥዖና ከፍተኛና ቶሎ የመገንዘብ ችሎታያላቸዉን ተማሪዎች በመደገፍ የፈጠራ ችሎታቸዉን እንዲያዳብሩ ማበረታታት አስፈላጊ ነዉ፡፡ለምሳሌ የጀልባ ስዕል ማንሳት፣ ካርታ ማንሳትና ስዕል የመሳል ሞያ መለማመድ የሚፈልጉ ተማሪዎች ካሉ

አበረታታቸዉ/ቿያዉ። በቡድናቸዉ ዉስጥ የተሰጣቸዉን ስራ ቀድመዉ የጨረሱ ተማሪዎችም ካሉ በተጨማሪ ሊሰሩ የሚችሉትን ጥያቄ መስጠት ተገቢ ነዉ።እነኝህም ጥያቄዎች እየተማሩት ካለዉ ርዕስ ዉስጥ ሳይወጣ በተቀራራቢ ይዜት በማዘጋጀት ሊሰጣቸዉ ይገባል።

## ተከታታይ ምዘና

ተማሪዎች በቡድን ውስጥ የሚያሳዩትን ተሳትፎ በመለየትና በመገምገም ምን ያህል ያህል እንዳገናዘቡ ማመዛዘን ያስፈልጋል፡፡ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ካሉ እገዛ በማድርግ የትምህርቱ ዋና ዓላማ ማስጨበጥ ያስፈልጋል፡፡የሜሮኤ ስልጣኔ የሚያሣይ ካርታ በማዘጋጀት ተማሪዎች እንዲለዩ መጠየቅ፡፡ተማሪዎች የጥታዊ ሜሮኤ ስላጣኔ የሚያሣዩ ቅርጻቅርጾችን እንደተረዱ ማመዛዘን አስፈላጊ ነው፡፡

በመጨረሻም ተማሪዎች የሙከራና መልመጃ ጥያቄዎችን በትክክል መስራታቸውን መከታተል፡፡ መምህራን ተማሪዎች ቢያንስ ሊኖራቸው የሚገባ የትምህርትብቃት እንዲያገኙ ትኩረት በመስጠት በተከታታይ መገምገም፡፡በመጨረሻም ተማሪዎች የሙከራ ስራና መልመጃዎችን በትክክል መስራታቸውን መከታተልና ብቃታቸውን መገምገም እና ለሙከራና መልመጃ ጥያቄዎች ግብረ መልስ መስጠት ያስፈልጋል፡፡

**የመልመጃ 5.1ጥያቄዎች መልስ**

**I.የእውነት /ሐሰት ጥያቄዎች መልስ**

1. ሐሰት 2. እውነት 3. እውነት 4. እውነት

**II. የአጫጭር ጽሑፍ ጥያቄዎች መልስ**

1. ሄሮግሎፊክስ
2. ፓፒረስ በሚባለው ላይ ሲጽፉ ነበር
3. ናይል
4. ከ3100 ዓ.ዓ.በፊት
5. ስነ-ጽሁፍ፣የአኗኗር ዜይቤ፣ የሃይማኖት ፅንሰ-ሀሳቦች እና የህንጻ ግንባታ ሙያዎች ናቸው

**የመልመጃ 5.2 ጥያቄዎች መልስ**

**I. የአጫጭር ጽሑፍጥያቄዎች መልስ**

1. የአሲሪያን ወረራ
2. ግብርናና ንግድ
3. ከኩሽ ዘር ግንድ የመነጩ በመሆናቸው
4. አዎ ልክ እንደ ዛጉዌና አክሱምስልጣኔዎች ናቸው

**የመልመጃ 5.3 ጥያቄዎች መልስ**

1. የአጫጭር ጽሑፍ ጥያቄዎች መልስ
2. ሁለቱም ነገስታት ከራሳቸው የግዛት ማዕከል ሲያስተዳድሩ ወይም ሲገዙ ነበር። ህዝቡም አንድ ባህል፣ተመሳሳይ ፓለቲካ እና አንድ ማንነት ነበራቸው
3. በብረታ ብረት ስራ ወይም ሙያ በጣም ይታወቁ ነበረ
4. ለጥንታዊ ስልጣኔዎች መሰረት የሆኑት ንግድና የግብርና ስራዎች ነበሩ
5. ጥንታዊ የግብፅ፣ኑቢያ እና ሜሮኤ ስልጣኔዎች ጠንካራ ትስስር ነበራቸው።ሶስቱ ስልጣኔዎች ተመሳሳይ ባህልና ከፍተኛ የሆነ የስልጣኔ ትስስር ነበራቸው።

**የምዕራፉ 5 ማጠቃለያ ጥያቄዎች መልስ**

**I. የምርጫ ጥያቄዎች መልስ**

1.ሐ 2. መ 3. መ 4. ለ5. መ

**II.የአዛምድ ጥያቄዎች መልስ**

1. ሐ 2.ለ 3.ሀ 4. ሠ 5. .መ

**III. የአጫጭር ጽሑፍ ጥያቄዎች መልስ**

1. የስልጣኔ ውጤቶች ሁሉ ይመሳሰላሉ፣በብዙ መንገድ የተሳሰሩ ናቸው፡፡
2. በሁለት ክፍል ይመደባሉ፣እነሱም ጥንታዊ እና ዘመናዊ መንግስታት ሲሆኑ መምህራን ተማሪዎች የሰሩትን ካርታ በማየት ማረጋገጥ ያስፈላጋል፡፡

# ምዕራፍ 6፡ጥንታዊውና የመካከለኛ ዘመን የኢትዮጵያ መንግሥታትና የህዝቦች ታሪክ

**የክፍል ጊዜ ብዛት-------------------12**

**ከዚህ ምዕራፍ የሚጠበቁውጤቶች፤**

- የኢትዮጵያን የጥንት ሥልጣኔ መገለጫዎችን ይዘረዝራሉ
- የአክሱምና የዛጉዌ ቀደመት ሥልጣኔዎችን ታሪክ ይገነዘባሉ
- የኢትዮጵያ የሙስሊም ሱልጣኖች አነሳስና መስፋፋትን ያብራራሉ
- የጐንደር ታሪካዊ ሁኔታዎችን በማድነቅ ይዘረዝራሉ
- የኢትዮጵያ የጥንትና የመካከለኛ ዘመን ምጣኔ ሀብት እንቅስቃሴ ይገነዘባሉ

**መግቢያ**

የኢትዮጵያ ታሪክ ከተከናወኑበት ጊዜ ጋር ሲታይ በሶስት ደረጃ ይከፈላሉ፡፡እነዚህም ጥንታዊ፣ መካከለኛ እና ዘመናዊው የኢትዮጵያ ታሪክ በመባልይታወቃሉ፡፡በዚህ ምዕራፍ ውስጥም የጥንታዊ እና መካከለኛው ዘመን ታሪክ በአጭሩ ይማራሉ፡፡ጥንታዊዉ የኢትዮጵያ ታሪክ የሚባለው መንግሥታት ከተመሠረቱበት እስከ 1270 ዓ.ም ያለው ጊዜ ማለት ነው፡፡ የአክሱምና የዛጉዌ መንግሥታት አመሠራረት በዚሁ በጥንታዊ ታሪክ ዘመን ውስጥ ይካተታል፡፡ የመካከለኛው ክፍለ ዘመን ታሪክ ደግሞ ከ1270 ዓ.ምእስከ 1855 ዓ.ምድረስ ያለውን ያካተተ ነው፡፡በመካከለኛው ዘመን ታሪክ ደግሞ የተለያዩ መንግስታትና ህዝቦች የበላይነትን ለመያዝ ሲፎካከሩ የነበረበት ክፍለ ዘመን መሆኑን በስፋት ተገልጿል፡፡

## 6.1. ጥንታዊ የኢትዮጵያ መንግሥታት

### 6.1.1. የአክሱምመንግሥት

**የክፍለ ጊዜ ብዛት-----------------3**

**ተማሪዎች ቢያንስ ሊኖራቸው የሚገባ የትምህርት ብቃት፤**

- የግብርና፣ንግድእና የቀረጥ ገቢዎች በሀገር ምጣኔ ሀብት ውስጥ ያላቸውንድርሻ ይገልጻሉ
- የአክሱምና የዛጉዌ የጥንት ሥልጣኔ ታሪክ ይገልጻሉ
- የአክሱምና ዛግዌ ሥልጣኔ ለዘመናዊ ኢትዮጵያ ያደረጉትንአስተዋጽኦ ያደንቃሉ
- የአክሱም እና ዛግዌ ሥልጣኔ አስተዋጽኦ በማነፃፀር ያገናዘባሉ

## ዋና ዋና ነጥቦች

በሰሜን ኢትዮጵያ ከተመሠረቱት የጥንት ስልጣኔዎች ውስጥ የአክሱምና ዛጉዌ መንግስታት ስልጣኔዎች ታዋቂዎቹ ናቸው። የአክሱም መንግሥት ስልጣኔ ከ1ኛውዓ.ዓ.እስከ 1150 ዓ.ም ቆይቷል። ከጥንታዊ አክሱምስልጣኔ መገለጫዎች ታዋቂዎቹ የመገበያያ ሳንቲሞች መቅረፅ፣ የቅርፃቅርፆች ስራ፣የሀውልት ግንባታ፣ስነፅሑፍ (ግዕዝ) እና የክርስትና ሃይማኖት መስፋፋት ናቸው።። በተጨማሪም ጠንካራ አስተዳደራዊ መዋቅርመኖር፣ጠንካራየጦር ኃይል በመገንባትና የኢኮኖሚ መሰረት የሆነውን ግብርናንና የንግድ ስራን በማጠናከር ይታወቃል።ከውጭውየአለም ሀገሮች ማለትምእንደ ግበፅ፣ግሪክ፣ሶሪያ፣እና ከምስራቅሮማ ሀገሮች ጋርጠንካራምጣኔ ሀብታዊ፣ ፖሊቲካዊ እና የሀይማኖት ግንኙነት ነበራቸው።በመጨረሻም የአክሱም መንግሥት አስተዳደር በሀገር በውስጥእና በውጭችግሮችተፅዕኖ በ1150 ሊወድቅ ችሏል።

በ1150 ዓምአክሱምበዛጉዌ በመሸነፉ የተነሳ የዛጉዌ ሥረወ መንግሥትተቋቁሟል። የዛጉዌ ነገሥታት ውቅር አብያተ ክርስቲያንን በማነጽ ይታወቃሉ።የዛጉዌ መንግስታት ምጣኔ ሀበት በግብርና እናከዘይላ የንግድ መስመር በሚገኝ ገቢላይየተመሰረተነበር። ይሁን እንጂ የዛጉዌ መንግሥት አስተዳደር በውስጥና በውጭ ችግሮችተፅዕኖ በ1270 ሊወድቅ ችሏል።

በአጠቃላይ በእነዚህ ሁለት ንዑስ ርእሶች ውስጥ የመንግስት አመሰራረትናምጣኔ ሀብት መሰረቶችና እድገት የእነዚህ ርእሶች ዋናዋና ነጥቦች ናቸው። በተጨማሪም የአስተዳደር ወሰን፣

የውጭ ግንኙነትና የውድቀታቸው ምክንያቶችንም ማወቅ ዋናዋና ፍሬ ሃሳቦች ናቸው፡፡ በተለይ የአክሱም መንግስት ከአረብ ሀገሮች ጋር ያለውን ግንኙነትእንደ ዋና ነጥብ የሚቀመጥ ነው፡፡.

## ቅድመ ዝግጅት

ይህን ርእስ ከማስተማራችሁ በፊት በቂ ዝግጅት ማድረግ አስፈላጊ ነው። በዚህ መሰረት በመጀመሪያ እነዚህን ሁለትን ንዑስ ርዕሶች በደንብ መረዳታችሁን ማረገገጥ አስፈላጊ ነው፡፡ የተለያዩ ታሪካዊ መረጃዎች ስለ ኢትዮጵያ ጥንታዊ ስልጣኔ የሚገልጹትን መፅሐፍት በስፋት ማንበቡ ይጠቅማል። በድጋሜ በምዕራፍ አራትና አምስት ስለ ቀደምት የአለምና የአፍሪካ ስልጣኔዎች መገንዘብ አስፈላጊ ነው። የአክሱምና የዛግዌ መንግስታትን የሚያሳይ ካርታ አዘጋጁ። የአክሱምና የዛግዌስልጣኔዎችን የሚያሳዩ ፎቶዎችን ፖስተሮችን፣ በጥንት ዘመን የነበሩ የሀውልቶችና የአብያተክርስቲያናትን ፎቶዎች እንዲሁምየተለያዩ የታሪካዊ ቅርሶች ፎቶ እና ሳንቲሞች ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው፡፡

በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ የትምህርት ዕቅድ ማውጣት ዋናው ተግባር ነው። እለታዊ የትምህርት ዕቅድ በምታወጡ ጊዜ የትምህርት መርጃ መሳሪያ ማዘጋጀት እና የተለያዩ የማስተማር ዘዴዎችን መጠቀም አስፈላጊ ነው፡፡.በዚህ ሁኔታ የአክሱም መንግሥትስልጣኔ ለማስተማር **ሁለት ክፍለ ጊዜ** ተጠቀሙ፡፡ እንዲሁም የዛግዌ ሥርወ መንግስትን ለማስተማር **አንድ ክፍለ ጊዜ** ተጠቀሙ፡፡ በአጠቃላይ እነዚህን ርዕሶች ለማስተማር**ሦስት ክፍለ ጊዜ**ተሰጥተዋል።

## የመማር ማስተመማር ዘዴ

ይህን ርእስ ለማስተማር በቂ ዝግጅት ካደረጋችሁ በኋላ የተለያዩ የመማር ማስተማር ዘዴዎችን መጠቀም አለባችሁ፡፡ከእነዚህ የመማር ማስተማር ዘዴዎችወስጥ ለትምህርቱ ምቹ የሆነውን መምረጥ አለባችሁ፡፡ይህንን ርዕስ ለማስተማር ሊያገለግሉ የሚችሉ የመማር ማስተማር ዘዴዎች ውስጥ ለመሳሌጥያቄና መልስ፣ በገለፃ፣ ድራማ ሰርቶ ማሳየት፣ በቡድን ስራ፣ በሁለትዮሽና በክፍል ሙሉ ውይይት፣ምልከታና ክርክር ማድረግ እና የመሳሰሉት ናቸው። በካርታ ላይ የአክሱም መንግሥትእና የዛግዌ መንግስት ግዛቶችን እንዲያሳዩ ማድረግ፡፡ ለተማሪዎች የተለያዩ መልመጃዎችን በድርጊት መልክ ሊያሳዩ እንዲችሉበመፅሐፉ ዉስጥ

ከተሰጡትስራዎች የተወሰኑትንእንደ ቤት ሥራ መስጠት፡፡ የአክሱም መንግሥትና የዛግዌ መንግስታትን የሚገልፅ ታሪካዊ ቅርሶችን በአካባበያቹ ከሚገኙ ነገሮችን እንዲሰሩ ማድረግ፡፡

ተማሪዎችየቀደምት ኢትዮጵያን ስልጣኔ የሚያሳዩ ቅርፃቅረፆችን በፕሮጄክት ሠርተዉ እንዲያቀርቡ አድርጉ፡፡ አሳታፊ የሆነየትምህርት ዘዴስራ ላይ ለማዋል የሚረዳ የትምህርት ዕቅድ ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው፡፡

## ልዩ ተሰጥዖ ያላቸዉን ተማሪዎች መደገፍ

ልዩ ተሰጥዖ ያላቸዉን ተማሪዎች በማበረታታት ለበለጠ ዉጤትና ስራ እንዲነሳሱ በመደገፍ የፈጠራ ችሎታቸዉን እንዲያዳብሩ ማበረታታት አስፈላጊ ነዉ። ለምሳሌ ካርታ ማንሳትና ስዕል የመሳል ሞያ መለማመድ የሚፈልጉ ተማሪዎች ካሉ አበረታቷቸዉ። በቡድናቸዉ ዉስጥ የተሰጣቸዉን ስራ ቀድመዉ የጨረሱ ተማሪዎችም ካሉ በተጨማሪ ሊሰሩ የሚችሉትን ጥያቄዎች መስጠት ተገቢ ነዉ።እነኝህም ጥያቄዎች እየተማሩት ካለዉ ርዕስ ዉስጥ ሳይወጣ በተቀራራቢ ይዜት በማዘጋጀት ሊሰጣቸዉ ይገባል።

## ተከታታይ ምዘና

የተማሪዎችንግንዛቤ የሚያጠናክር የተለያዩ ጥያቄዎችንና ክንውኖችኝ በተለያዩ ርዕሶችሥር በግል ወይም በቡድን እንዲሠሩ ማድረግና ማየት፡፡ ተማሪዎች በካርታ ላይ ወይንም በቻርት ላይ የጥንት አክሱምና የዛግዌመንግስት የስልጣኔ ማዕከላት የነበሩትን ቦታዎችእንዲያሳዩ መጠየ፡፡ ተማሪዎች በግልም ሆነ በቡድን የሚከናወኑትን ሥራ በቅርበት በመከታተል ግብረ መልስ እና የማስተካከያሃሳብ መስጠት፡፡

የቀደምት ኢትዮጵያን ስልጣኔዎች የሚያሳዩ ታሪካዊ ቅርፃ ቅረፆችን በጥራትሠርተዉ ማቅረባቸውን መመዘን፡፡አሳታፊ የሆነ ትምህርት ለመስጠት ማቀድ አለባችሁ፡፡የተለያዩ መልመጃዎችን በመስጠት እንዲሰሩ ማድረግ፣ የሰሩትንም በማረም ተማሪዎችን ማበረታታትና በቅርበት በመከታተልና ግብረ መልስ መስጠት፡፡

## 6.2.የኢትዮጵያ ሙስሊም ሱልጣኔቶች እና የጎንደር ምስረታ

**የክፍለ ጊዜ ብዛት--------------3**

**ተማሪዎችቢያንስሊኖራቸው የሚገባ የትምህርትብቃት፤**

- የጥንት እና የመካከለኛውንክፍለ ዘመን የኢትዮጵያሙስሊም ሱልጣኔቶች ፖሊቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ እንቅስቃሴዎችንይገልፃሉ
- የጎንደርን ከተማን የመንግስት አመሰራረትና ዕድገት ይገልፃሉ፡፡
- የጎንደርን ስልጣኔ አወዳደቅ ያብራራሉ፡፡

## ዋና ዋና ነጥቦች

የሙስሊም ሱልጣኔቶችና የጎንደር መንግስት አመሰራረትና ዕድገት በጥልቀት ማየት አስፈላጊ ነው፡፡ ሁለቱም ርዕሶችበይበልጥ የመካከለኛውን የኢትዮጵያ ዘመን ክንውኖችናቸው፡፡ ስለዚህ ሁለቱንም በማያያዝ ማስተማር አሰፈላጊ ነው፡፡በሙስሊም ሱልጣኔቶችና በመካከለኛው ዘመን መካከል ያለውን ቁርኝት መገንዘብ አስፈላጊ ነው፡፡

ሌላው ዋና ነጥብ ደግሞየአመሰራረታቸው ሁኔታና ዕድገታቸው ነው፡፡ የሙስሊም ሱልጣኔቶች ከአስረኛው ክፍለ ዘመን አንስቶ እስከ ዘመናዊ ኢትዮጵያ ሲስፋፉ ቆይተዋል፡፡

እነሱም ሸዋ፤ ኢፋት፤አዳል፤ፈጠጋር፤ሀዲያ፤ደራ፤አረባቢኒ፤ሻርካ እና ባሊየመሳሰሉት ናቸው፡፡ እነዚህ ሱልጣኔቶች በአብዛኛው በስደት ከአረብ ሀገር ወደ ኢትዮጵያ የመጡ ሰዎች ወይም የሙሰሊም ቤተሰቦች የተመሰረቱ ናቸው፡፡ አስተዳደራቸውንም ከአጠናከሩ በኃላ ፖለቲካዊ፤ ምጣኔ ሀብታዊና ሀይማኖታዊ ሁኔታዎችጋር በተያያዘ በደጋማው አካባቢ ከሚኖረው የክርስቲያን መንግስትና ማህበረሰብ ጋር በመጋጨት ግንኙነታቸው ወደ አለመግባባት ተቀይሮ ነበር፡፡

በሌላ በኩል በሰላም ያለውን ቁርኝት ስንመለከት ለመንግስት ግብር በመክፈል ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር የመግባባት ባህላቸውንና በማጠንከርናየሙስሊም ሀይማኖትን ማስፋፋታቸው ግንዛቤ የሚፈለግ ነጥብ ነው፡፡የኦሮሞ ሕዝብ መስፋፋት የክርስቲያን መንግስትና የሙስሊም ሱለጣኔቶች እንቅስቃሴ ኃይል ለማዳከም የእርስበርስ ጦርነቱንም ቀላል አድርጎታል፡፡

ቀጣዩ ወሳኝ ነጥብ የጎንደርን ከተማ ምስረታና የአስተዳደር መስፋፋትን ይመለከታል። የጎንደር መንግስት ምስረታ ከጎንደር ከተማ ምስረታ ቢቀድምም ቋሚ ማእከልና ሀገርን ማስተዳደር የጀመረው ግን የጎንደር ከተማ ከተመሰርተ በኃላ ነው።የጎንደር ክተማ የተመሰረተው በ1636 በንጉስ ፋስሊደስ ነው።ከዚህ አመት እስከ የመሬት ባለሃብቶችዘመነ መሳፍንት ድረስ የነበረው የመንግስተየእርስ በርስጦርነት ከባድ ቢሆንም በዘመነ መሳፍንትበመሬት ባለሃብቶች ዘመን በጣም ስለቀዘቀዘ ይህ መንግስትለስም ብቻ ያለ ይመስል ነበር። ምክንያቱ ደግሞ ጠንካራና እውነተኛው ስልጣን በየጁ/ ወረሼህ ወሎ እጅ ስለነበረ ነው።

በአጠቃላይ የሙስሊም ሱለጣኔቶችና የጎንደር መንግስት አስተዳደር በማያያዝ ማየት ዋነኛና ትልቁ ነጥብ ነው።እንደዚሁም በጎንደር ከተማ የታዩ የተለያዩ ስልጣኔዎችና የማህበረሰቡ እድገት መተንተን እንደ ዋና ሃሳብ የሚታይ ነው።

በጎንደር ከተማየተለያየ ሙያና አመለካከት ያላቸው የውጭ ሃገር ዜጎች በአንድ ላይ ሲኖሩ እንደነበርመገንዘብ ያለባችሁ ትልቅ ቁምንገር ነው።

## ቅድመ ዝግጅት

የመጀመሪያው ዝግጅት የመካከለኛው ዘመን የኢትዮጵያን ካርታ ማዘጋጀት የመጀመሪያው ስራ ነው።የተለያዩ የሙስሊም ሱልጣኔቶች ወደ ኢትዮጵያ የገቡባቸው መንገዶችና አቅጣጫዎችን የሚያሳይ ካርታ ያስፈልጋል። የሙስሊም ሱልጣኔቶችና የኢትዮጵያን የመካከለኛው ዘመን የመንግስት ግንኙነትን በጥሩ ሁኔታ ለመተንተን ጥልቅ ግንዛቤ እንዲኖር ያግዛል። በዚህ መሰረት የማጣቀሻ መፅሃፍትን በዚህየመምህሩ መምሪያ የማስተማሪያ ያሉትንና ሌሎችንም መመርመር/ማየት ወሳኝ ነው።እንደ ፖለቲካዊ፣ ምጣኔ ሀብታዊ፣ ማህበራዊና እና የጦር ኃይል ጉዳዮችን በደንብ ማገናዘብ አለባችሁ። የእርስበርስ ግጭትና ውጊያ ጥቅምና ጉዳቱን ምን ምን ሲሆን እንደሆነ በተደራጀ መልኩ ግልፅ መሆን አለባቸው።

የቀኑን የትምህርት እቅድ ከአመታዊውእቅድ ላይ በትክክል ማውጣት ቀጣዩ ትልቁ ስራ ነው። የትምህርት መርጃ መሳሪያ በአካባቢው ከሚገኙት ግብዓቶች ማዘጋጀት።ከዚሁ ጋር የተያያዘ ነው።ይህንን የመማር ማስተማር ሂደትን ለማከናወን **ሶስት ክፍለ** ጊዜ በቂ ነው። በመሆኑምየሙስሊም ሱለጣኔቶች የሚለውን ንዑስ ርዕስ ለማስተማር ደግሞ **ሁለት**ክፍለ ጊዜ በቂ ነው። የጎንደር መንግስትን ለማስተማር 1 ክፍለ ጊዜ በቂ ነው።

**የመማር ማስተማር ዘዴ**

የመማር ማስተማር ዘዴዎች ብዙ ስለሆኑ ውጤታማ የሆነና ተማሪዎችን በቂ ክህሎት እንዲያዳብሩ የሚያደርጉ ዘዴዎችን መምረጥ ይገባል፡፡መምህራን የተለያዩ የመማር ዘዴዎችን የመጠቀማቸው ዋናው አላማ የትምህርቱን ይዜት ለታለመለት ግብ ለማድረስ ነው፡፡ይህ ትልቅ ግብ ደግሞ ተማሪዎችን ማብቃት ነው፡፡ይህ ስለሆነም መምህራን የሚሻለውንና ውጤታማ የሚያደርጉትን የመማር ማስተማር ዘዴዎች መጠቀም ግዴታ ነው፡፡

በዚህ መሰረት ተማሪዎችን በሰባትቡድን ወይንም በክፍሉ ተጨባጭ ሁኔታ ላይ በመመስረት በቡድን በመክፈል ለእያንዳንዱ ቡድን የንዑስ ረዕሱን ፕሮጀክት ስራ በመስጠት ሰርተው እንዲያቀርቡ ማድረግ ጥሩ ነው፡፡ ለምሳሌ የሙስሊም ሱልጣኔቶች ወደ ኢትዮጵያ የገቡበትን መንገድ የሚየሳይ ካርታ እንዲያዘጋጁ ማድረግ አንዱ ሊሆን ይችላል፡፡ በተጨማሪም መማር ማሰተማር ዘዴ እንደ ሪፖርት ማድረግ፤ ማነጻጸር፤ገለጻ፤ማሳየትና ከመሳሰሉትን ዘዴዎች መርጦ መጠቀም ይቻላል፡፡ የተሸለዉ ዘዴ ሚበልጠው ግን ተማሪዎቹ ራሳቸውን የሚያስተምሩበትና የትምህርቱን ይዜት እንዲገነዘቡ የማድረግ ዘዴ በጣም ተመራጭ ነው፡፡ በይበልጥ መምህራኑ መረዳትና ማቀድ ያለባቸውን ነገር ሁሉን አካታችና አሳታፊ የሆነውን የመማር ማስተማር ዘዴ ስራ ላይ ማዋል ነው፡፡ እንዲሁም ወንድና ሴት ተማሪዎችን በእኩልነት ማሳተፍማድረግ መረሳት የለበትም፡፡

## ልዩ ተሰጥዖ ያላቸዉን ተማሪዎች መደገፍ

ልዩ ተሰጥዖና ከፍተኛ ግንዛቤ ያላቸዉን ተማሪዎች በመደገፍ የፈጠራ ችሎታቸዉን እንዲያዳብሩ ማበረታታት አስፈላጊ ነዉ።ለምሳሌ ካርታ ማንሳትና ስዕል የመሳል ሞያ መለማመድ የሚፈልጉ ተማሪዎች ካሉ አበረታታቸዉ/ቿያዉ። በቡድናቸዉ ዉስጥ የተሰጣቸዉን ስራ ቀድመዉ የጨረሱ ተማሪዎችም ካሉ በተጨማሪ ሊሰሩ የሚችሉትን ጥያቄ መስጠት ተገቢ ነዉ።እነኝህም ጥያቄዎች እየተማሩት ካለዉ ርዕስ ዉስጥ ሳይወጣ በተቀራራቢ ይዜት በማዘጋጀት ሊሰጣቸዉ ይገባል።

## ተከታታይ ምዘና

ተከታታይ ምዘና ተማሪዎች የሙስሊም ሱልጣኔቶችን ምስረታና ማዕከል ከተለያዩ ካርታ ወይም ስዕል ላይ እንዲያሳዩ ማድረግ።የእያንዳንዱ ተማሪ ጠንካራና ደካማ ጎን ከተሰጠው የፕሮጀክቱ ስራ ወይም ክርክር ላይ በቡድናቸው ውስጥ ያላቸውን የተሳትፎ መጠን በመገምገም መለየትና የሙከራ ፈተና እና የቤት ስራ በመስጠት ሪፖረት እንዲያቀርቡና ብቃታቸውን እንዲያሳድጉ ለማድረግ ምዘናና ግብረ መልስ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡

የጎንደር ከተማ ማህበረሰብ ያላቸውን የእርስበረስ ትስስር እንዲናገሩ መጠየቅ ጥሩ ነው፡፡ እያንዳንዱ ተማሪ በግሉ በንዑስ ርእስ ስር ያሉትን መልመጃዎች እንዲሰሩ ማድረግ ግዴታ ነው፡፡

## 6.3 የህዝቦች ግንኙነት፣ትስስር እና እንቅስቃሴ

**የተሰጠው የክፍለ ጊዜ ብዛት-------------4**

**ተማሪዎች ቢያንስ ሊኖራቸው የሚገባቸው የትምህርት ብቃት፤**

- ከጥንት ዘመን ጀምሮ ያለው የኢትዮጲያ ህዝቦች እንቅስቃሴ፣ግንኙነት እና ትስስር ይገናዘባሉ
- የህዝቦች እንቅስቃሴ፣ግንኙነት እና ትስስር ጥቅም እና ጉዳት በማነፃፀር ያመዛዝናሉ
- የህዝቦች እንቅስቃሴ ምክንያቶችን በማነፃፀር ያገናዘባሉ.

## ዋና ዋና ነጥቦች

በአፍሪካ ቀንድ ውስጥ የህዝቦች እንቅስቃሴ በ15ኛዉ እና 16ኛው ክፍለ ዘመን ውስጥ መካሄዱን መገንዘብ ዋና ነጥብ ይሆናል፡፡ የህዝቦችን እንቅስቃሴ በፖሊቲካዊ፣ በምጣኔ ሀብታዊ እና ማህበራዊ ለውጦች መገምገም እና ማመዛዘን አስፈላጊ ነው፡፡በነዚህ አርእስቶች ውስጥ የተካተቱትን ዋና ዋነ ነጥቦች በትክክል መገንዘብ አስፈላጊ ነው ፡፡ በዚህ መሰረት በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ የተከሰቱት የህዝቦች እንቅስቃሴ ብዙ ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ የሶማሌ፣ የአፋር፣ የአርጎባ ፣የሐረሪ እና የኦሮሞ ህዝቦች እንቅስቃሴ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

የኦሮሞ ህዝብና የገዳ ሥርዓት፣ የህዝብ እንቅስቃሴ ካሉት ነጥቦች ውስጥ ዋነኞቹ ናቸው። በዚህ መሰረት የኦሮሞ ህዝብ በኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እንዲሁም በተፈጥሮ ችግር ምክንያት ከ16ኛ እስከ 17ኛ ክፍለ ዘመን ድረስ በአሁኑ መዳ ወላቡ ከሚባለው አካባቢ በሁለት አቅጣጫ ተንቀሳቅሷል። የቦረና ፌደሬሽን በደቡብና በመካከለኛው ኢትዮጵያ ወደ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሲንቀሳቀሱ የባሬንቱ ፌደሬሽን ደግሞ በምስራቅና በሰሜን ምስራቅ አቅጣጫ ተንቀሳቅሷል። በይበልጥ ይህ እንቅስቃሴ ሊሳካ የቻለው የገዳ ሥርዓት የፈጠራቸው ቅንጅትና አደረጃጀቶችጠንካራ መሆን ነው።

በአጠቃለይ የኦሮሞ ገዳ ሥርዓት ፖሊቲካዊ፣ምጣኔ ሀብታዊና ማህበራዊ ሥርዓትን ያካተተ መሆኑን መገንዘብ አስፈላጊ ነው። በተጨማሪም የክርስቲያንና የሱልጣኔቶች መንግስታት ለረጅም ጊዜ ሲዋጉ መቆያታቸው አቅማቸው እየተዳከመ መምጣቱ ለኦሮሞ ህዝብ እንቅስቃሴ ስኬት ትልቅ አስተዋፅኦ አድርጓል።የተደራጀ የገዳ ሥርዓትና የኦሮሞ ባህላዊ ስርዓቶች በሁሉም አኳያ ለኦሮሞ ህዝብ ያደረገው እንቅስቃሴ እንዲሳካ ትልቅ አስተዋፅኦ አበርክቷል።

ከገዳ ሥርዓት አደረጃጀት ውስጥ ታዋቂዎቹ የሲንቄ ሥርዓት፣ የኢሬቻ ሥርዓት፣ የሙዳ ሥርአት፣ ዋቄፈና፣ ጉዲፈቻ እና ሞጋሳ ሥርዓቶችናቸው። የሲንቄ ሥርዓት የኦሮሞ ሴቶችን መብት የሚያስከብር ተቋም ነው። ኢሬቻ የምስጋና በዓል ሲሆን በአመት ሁለቴ ይካሄዳል። እንዲሁም የገዳ ሥርዓትውስጥ የጋብቻ ሥርዓት፣የሀዘንና የደስታ ሥርዓቶችን ያካትታል። እነዚህንስርዓቶች ሁሉንም መግለጽ ስለማይቻል አስፈላጊ የሆኑትን ብቻማስተማር ከመምህሩ ይጠበቃል።

በተማሪዎች መጽሐፍ ውሰጥ ከተጠቀሱት በተጨማሪ የማጣቀሻ መጽሐፍቶችን በመጠቀም ማስተማር አለባችሁ። ሌላው ዋና ነጥብ ለኦሮሞ ገዳ ሥርዓት መዳከም ምክንያት የሆኑትን ዘርዝሮ መለየት ወሳኝ ነው። በተማሪ መጽሐፍ ውሰጥ በጥሩ ሁኔታ የተገለፀ ስለሆነ መገንዘብ አስፈላጊ ነው። የገዳ ሥርዓት በ2016 ዓ.ም በአለም የቅርስ መዝገብ(UNESCO) ላይ ተመዝግቧል። በአጠቃላይ የገዳ ሥርዓት የሰውልጅ ለኑሮው የሚያስፈልጉትን ነገሮችሁሉ በውስጡ ያካተተ መሆኑን ተማሪዎችን መገንዘብ አስፈላጊ ነው።

**ቅድመ ዝግጅት**

ይህን ርዕስ ለማስተማር በቅድሚያ ቅድመ ዝግጅት ማድረግ አስፈላጊ ነው። በአካባቢያችሁ ከሚገኙ አዛውንቶች፣ ሀደ-ሲንቄዎች እና አባገዳዎች በመጠየቅ በገዳ ሥርዓት ውስጥ የሚገኙ ማህበራዊ፣ምጣኔ ሀብታዊ እና ፖለቲካዊ አደረጃጀቶችን መረዳት የመጀመሪያ ተግባር ይሆናል። በተጨማሪ የማጣቀሻ መጽሐፍቶችን በመጠቀም ያላችሁን ግንዛቤ ማሳድግ የስፈልገል።

በመቀጠልም በአፍሪካ ቀንድ የህዝቦች እንቅስቃሴ የሚያሳይ የመካከለኛው ክፍለ ዘመን ካርታ ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው። በተጨማሪም የኦሮሞ የዘር ሀረግ ግንድ የሚያሳይ ቻርት ወይንም ፖስተር፣ ፎቶዎች፣ የሲንቄ ሥርዓትን የሚያሳይና ፎቶ፣ ባሊ(ስልጣን) ማስተላለፍ የሚያሳዩ ቪዲዮዎችን መጠቀም። አባ ገዳ፣ ከለቻ እና የተለያዩ የኦሮሞ ባህልን የሚያሳዩ የክብር ቁሳቁሶችን (ጌጣጌዖችን) የሚያሳዩ ነገሮችን ማሰባሰብ ወሳኝነት አለው፡፡ በአካባቢያችሁ የሚገኙ አባ ገዳዎችን ወይም ከባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ባህላዊ እሴቶችንና የተለያዩ የገዳ ሥርዓትን የሚያሳዩ ፎቶዎችን ወይንም ቪዲዮወችንበዉስትም ቢሆን አዘጋጁ።

ጥራት ያለው ትምህርት ለመስጠት የትምህርት ዕቅድና በቂ ዝግጅት ማድረግ አስፈላጊ ነው። በዕቅድዎ ውስጥ ዓላማ፣ግልፅ የሆነ የመማር ማስተማር ዘዴ እና የትምህርት መርጃ ማሳሪያዎችን መዘርዘር መጠቀም አስፈላጊ ነው። ይህንን ርዕስ ለማስተማር **አራት ክፍለ ጊዜ** ተጠቀሙ። በዚህ መሰረት የህዝቦችን እንቅስቃሴን ለማለስተማር **አንድ ክፍለ ጊዜ**፣የኦሮሞ ህዝብ እንቅስቃሴን ለማለስተማር **አንድ ክፍለ ጊዜ**፣ የኦሮሞ ገዳ ሥርዓትን ለማስተማር **አንድ ክፍለ ጊዜ** እንዲሁም የማህበረሰብ ባህላዊ ተቋማት ለማስተማር **አንድ ክፍለ ጊዜ** በቂ ነው።

## የመማር ማስተመማር ዘዴ

ይህን ርእስ ለማስተማር ተማሪዎች በአካባቢያችሁ የሚገኙ አባ ገዳዎችን ፣አዛውንቶች እና ሀደ-ሲንቄዎች ስለ ገዳ ሥርዓት እንዲጠይቁ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ ሰለ ኦሮሞ ህዝቦች እንቅስቃሴ በመጀመሪያ ክፍለ ጊዜ ካሰተማሩ በኋላ ወደሚቀጥለው ርዕስ ከመሽጋገራችሁ በፊት ተማሪዎች አባ ገዳዎችንና አዛውንቶችን ጥያቄ ጠይቀው እንዲመጡ ማድረግ አስፈላጊ ነው። በመቀጠል የገዳ ሥርዓት ክፍለ ጊዜከመጀመሩ በፊት ተማሪዎች ከማህበረሰቡ የተረዱትንና እራሳቸው የሚያውቁትን በነጻነት እንዲያስረዱ ማድረግ ነው። በክፍል ውስጥ በስድስት/ሰባት ቡድን ከተከፈሉበኂላ የቡድን ዉይይት አከሂደው ያላቸውን ዕውቀትና ልምድ እንዲለዋወጡ ማድረግ። ከዚህም በመቀጠል ሀሳባቸውን ለሌሎች ተማሪዎች እንዲያካፍሉ ማድረግ።

በሚቀጥለው ክፍለ ጊዜ የክፍሉ ተማሪዎች በአራት/አምስት ቡድን ከከፋፈላችሁ በኂላ በፕሮጀክት የሲንቄ ሥርዓት የሚያሳይ ፎቶ፣ ባሊ(ስልጣን) ማስተላለፍ፣ ከለቻ እና የተለያዩ የኦሮሞ ባህልን የሚያሳዩ ጌጣጌያችንና ዕቃዎችን የሚያሳዩ ነገሮችንሰርተው እንዲያቀርቡ ማድረግ፡፡

በአካባቢያችሁ የሚገኙ አባ ገዳዎችን፣ ሀደሲንቄች፣ እና ከባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት በመጋበዝ ከኦሮሞ ባህል እና ታሪካዊ ቅርሶች ጋር ተያያዥ ያላቸውን ጉዳዮች ለተማሪዎች እንዲያስረዱ ማድረግማስረዳት አስፈላጊ ነው፡፡

የገዳ ስርዓት አስተዳደርና ዘመናዊ የአስተዳደር ሥርዓትን በማነፃፀር እንዲከራከሩ በማድረግ ግንዛቤያቸውን እንዲያሳድጉ ማድረግ፡፡ በዚህ መሰረት ተማሪዎች በአምስት/አራት ቡድን በመከፋፈል የሕብረተሰቡን ተቋማት፣ ባህላዊ ተቋማት እና ዘመናዊ ተቋማትን ተማሪዎች አነፃፅረው እንዲከራከሩ በማድርግ ዕውቀት ማስጨበጥ ይቻላል፡፡ በተጨማሪም የገዳ ሥርዓት በዩኔስኮ እንደ ቅርስነት መመዝገቡ ላይ ተማሪዎቹ ሪፖርት እንዲያቀርቡ ማድረግ ተጨማሪ አማረጭ ነው፡፡

## ልዩ ተሰጥዖ ያላቸዉን ተማሪዎች መደገፍ

ልዩ ተሰጥዖና ከፍተኛ ግንዛቤ ያላቸዉን ተማሪዎች በመደገፍ የፈጠራ ችሎታቸዉን እንዲያዳብሩ ማበረታታት አስፈላጊ ነዉ።ለምሳሌ ካርታ ማንሳትና ስዕል የመሳል ሞያ መለማመድ የሚፈልጉ ተማሪዎች ካሉ አበረታታቸዉ/ቿያዉ። በቡድናቸዉ ዉስጥ የተሰጣቸዉን ስራ ቀድመዉ የጨረሱ ተማሪዎችም ካሉ በተጨማሪ ሊሰሩ የሚችሉትን ጥያቄ መስጠት ተገቢ ነዉ።እነኘህም ጥያቄዎች እየተማሩት ካለዉ ርዕስ ዉስጥ ሳይወጣ በተቀራራቢ ይዜት በማዘጋጀት ሊሰጣቸዉ ይገባል። ከዚህ የተለየ ፈጠራ መስራት ለሚፈልጉት ከትምህርት ቤታችሁ ጋር በመተባባር መርዳት አለባችሁ

## ተከታታይ ምዘና

የተማሪዎችን የክፍል ተሳትፎ በመመልከት የተማሪዎችን ጠንካራ ጎን እና ደካማ ጎን መመዘን እና ለይቶ ማወቅ ወሳኝ ነው፡፡ በካርታ ላይ የኢትዮጵያን እና የምስራቅ አፍሪካ ቀንድ ህዝቦች እንቅስቃሴ አቅጣጫዎችን እንዲያመለክቱ በማድረግ ምዘና ማካሄድ አስፈላጊ ነው፡፡ በተሰጣቸው የፕሮጀክት ስራ ውስጥ የየግላቸውን ድርሻ መመዘን አስፈላጊ ነው፡፡ የተደረገው ክርክር

በተፈለገው መንገድ መሄዱንና አለመሄዱን በመመዘን ወሳኝ ነው፡፡ የገዳ ሥርአት በአለም የታሪካዊ ቅርስ መዝገብ ላይ መመዝገብ ለምን እንዳስፈለገ እና መመዝገቡ ምን አይነት ጥቅም እንዳለው መጠየቅ አስፈላጊ ነው፡፡በአጠቃላይ በሁሉም የምዘና አይነቶች ውስጥ ያለውን ደካማ ጎን እና ጠንካራ ጎን በመረዳት አጥጋቢ ግብረ መልስ መስጠት ግዴታ ነው፡፡

## 6.4. የኢትዮጵያ መሰረታዊ የምጣኔ ሀብት እንቅስቃሴ
## (ግብርና ፣ንግድ፣ የንግድ መስመር እና ግብር)

**የክፍለ ጊዜ ብዛት---------------- 2**

**ተማሪዎች ቢያንስ ሊኖራቸው የሚገባቸው የትምህርት ብቃት፤**

- ግብርና፣ የንግድ ስራ እና ግብር ለሀገር ምጣኔ ሀብት ዕድገት የሚያስገኙትን ጥቅም ይገልፃሉ
- የዜጎች ተሳትፎ ለሀገር ምጣኔ ሀብት እድገት ያለውን አስተዋፅኦ ይለያሉ

### ዋና ዋና ነጥቦች

ግብርና፣ የንግድ ስራ እና ግብር እንዲሁም ቀረጥለሀገር ምጣኔ ሀብት ዕድገት ያላቸውን አስተዋፅኦ ማወቅ አሰፈላጊ ነው፡፡ ግብርና፣ የንግድ ስራ እና ግብር ለሀገር ምጣኔ ሀብት ዕድገት ያላቸውን አስተዋፅኦ ከጥንት ዘመን ጀምሮ እስከ መካከለኛ ዘመን ምን እንደሚመስል አንድ ላይ በማጠቃለል መረዳት ተገቢ ነው፡፡

ግብርና ለኢትዮጵያ ምጣኔ ሀብት ዕድገት የጀርባ አጥንት ነው፡፡ ከጥንታዊ ኢትዮጵያ ጀምር እስከ ዘመናዊ ኢትዮጵያ ድረስ ያሉ የኢትዮጵያ ነገስታት በብዛት ልማት ሲያካሄዱ የነበረው ከግብርና ከሚገኘው ገቢ ነበር፡፡ ግብርና መሬትን ማረስና እንስሳትን ማርባት ያካትታል፡፡ በዚህ መሰረት የአክሱምና የዛግዌ መንግስታት የገቢ ምንጭ ግብርና ነበር፡፡ንግድና ግብር ተጨማሪ የገቢ ምንጭ ነበሩ፡፡ የግብርና ምርቶች እንደ ገብስ፣ጤፍ፣ ዳጉሳ እና የቅባት እህሎች በባህላዊ ዘዴ በብዛት ይመረታሉ፡፡

የተለያዩ የታሪክመረጃዎች እንደሚያመለክቱትንግድ የገቢ ምንጭ ብቻ ሳይሆን ለከተሞችመቆርቆርና ለመንግስታት መመስረትም ዋነኛው ምክንያት ሆኗል፡፡ ከዚህ የምጣኔ ሀብት እንቅስቃሴ መንግስታት በግብርና በቀረጥ መልክ ገቢ ያገኛሉ፡፡ ከነጋዴዎች ላይ በንግድ

መተላለፊያ መንገዶች ላይ ኬላን እያቋቋሙ ቀረጥ ሲሰበስቡ ቆይቷል። ይሁን እንጂ የግብር እና የቀረጥ አሰባሰብ ዘዴዎች በዘመናዊና በመደበኛ መልክ ስላልነበረ በቂ ግብር መስብሰብ አልተቻሉም ነበር።

## ቅድመ ዝግጅት

የጥንታዊና የመካከለኛው ዘመን የኢትዮጵያ የንግድ መስመር የሚያሳይ ካርታናየንግድ መሳሪዎችን የሚያሳዩ ፖስተሮችን/ፎቶዎች ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው፡፡ የግብርና ምርቶችን የሚያሳዩ ስዕሎች እንዲሁም የተለያዩ ሀገራትን የመገበያያ ገንዘቦች ማግኘ ቢቻል የተመረጠ ነው።ግብርና ቀረጥን በመሰብሰብ መንግስት የሰራውን የተለያዩ መሰረተ ልማቶች ፎቶዎችን ለምሳሌት/ቤት፣ ጤና ጣብያ፣ ሆስፒታል እና የመሳሰሉትን ማዘጋጀት ያስፈልጋል።

የሀገር ውስጥ ገቢ በተመለከተ ተማሪዎች በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው የተለያዩ መረጃዎችን በማሰባሰብ ማጠቃለያ አዘጋጁ፣ ቢቻል የሀገር ውስጥ ገቢን የሚሰበስቡትንና የሚያደራጁትን ቢሮዎች በመጋበዝ ለተማሪዎች በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው አድርጉ።

ይህንን ርዕስ ከማስተማርዎ በፊት ግልፅ የሆነ የትምህርት ዕቅድና በቂ ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል። በዚህ የትምህርት ዕቅድ ውስት የመማር ውጤት፣ የመምህርና የተማሪ ተግባር በጥራት መካተት አለበት፡፡ የትምህርት መርጃ መሳሪዎችና የምዘና ስልቶችም በዕቅዱ ውስጥ መካተት አለባቸው። በአጠቃላይ እነዚህን ዋና ዋና ነጥቦች ለማስተማር**ሁለት ክፍለ ጊዜ** ተመድቦላቸዋል። እነዚህን አርዕስቶች ከተሰጣችሁ ክፍለ ጊዜጋር በማስማማት ማከናወን አስፈላጊ ነው።

## የመማር ማስተማር ዘዴዎች

በመጀመሪያ ተማሪዎች ከዚህ በፊት የነበራቸውን ግንዛቤ በነፃነት በክፍል ውስጥ እንዲገልጹ ማድረግ አስፈላጊ ነው። በመቀጠልም በንዑስ ርዕሱ ስር የሚገኙትን የሙከራ ጥያቄዎች ላይ ተማሪዎችን ማወያየት ያስፈልጋል። የውይይታችውን ውጤት በሪፖርት መልክ እንዲያቀርቡ ማድረግ። ተማሪዎች ስለ ግብርናና ንግድ ምንነት ቤተሰቦቻቸውንና በአከባቢያቸው የሚገኙትን ነጋዴዎችን በመጠየቅ ለክፍል ተማሪዎች እንዲቀርቡ ማድረግ በጣም ወሳኝ ነው። ተማሪዎች

በምልከታ ያገኙትን ውጤት በሪፖርት መልክ እንዲያቀርቡ ማድረግ፡፡ ከንግድ ዘርፍ ጋር ተያይዞ ስለ ግዢና ሽያጭ በድራማ መልክ በክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡

የግብርንናና የቀረጥ ጥቅም በክፍል ውስጥ በሪፖርት መልክ እንዲያቀርቡ ማድረግ የተመረጠ የመማር መስተማር ዘዴ ነው፡፡ የግብርናና የንግድ ስራ እንዴት እንደሚከናወኑ በማነፃፀር እንዲከራከሩ ማድረግ የክርክራቸውን ውጤት ሪፖርት እንዲያደርጉ ማድረግ፡፡

## ልዩ ተሰጥዖ ያላቸዉን ተማሪዎች መደገፍ

ልዩ ተሰጥዖና ከፍተኛና ቶሎ የመገንዘብ ችሎታ ያላቸዉን ተማሪዎች በመደገፍ የፈጠራ ችሎታቸዉን እንዲያዳብሩ ማበረታታት አስፈላጊ ነዉ።ለምሳሌ ስለገቢ ማዳበርና ንግድ የተሸለ ማብራራት የሚችሉትን ተማሪዎች ማነሳሳት፡፡ በቡድናቸዉ ዉስጥ የተሰጣቸዉን ስራ ቀድመዉ የጨረሱ ተማሪዎችም ካሉ በተጨማሪ ሊሰሩ የሚችሉትን ጥያቄ መስጠት ተገቢ ነዉ።እነኝህም ጥያቄዎች እየተማሩት ካለዉ ርዕስ ዉስጥ ሳይወጣ በተቀራራቢ ይዜት በማዘጋጀት ሊሰጣቸዉ ይገባል።

## ተከታታይ ምዘና

የተማሪዎችን የክፍል ተሳትፎ በመመልከት የተማሪዎችን ጠንካራና ደካማ ጎን መመዘንና ለይቶ ማወቅ ወሳኝ ነው፡፡የግብርናና የንግድ ስራ እንዴት እንደሚከናወን ቤተሰቦቻቸውን ወይም አርሶአሮደችን በመጠየቅ ያቀረቡትን ሪፖርት በመመልከት መመዘን ይቻላል፡፡ የመካከለኛ ዘመን የኢትዮጵያ የንግድ መስመር የሚያሳይ ካርታና የንግድ ማዕከላትን እንዲገልጹ ማድረግ ወሳኝ ነው፡፡ እንዲሁም የሽያጭ ምርት አይነቶችን በሥዕል እንዲያሳዩ በማድረግ መመዘን ይቻላል፡፡ የቡድን ስራ በመስጠት ያስመዘገቡትን ውጤት በማየትመመዘን ይቻላል፡፡በአጠቃላይ በሁሉም የምዘናዓይነቶች ውስጥ ያለውን ደካማና ጠንካራ ጎን በመረዳት አጥጋቢ ግብረ መልስ መስጠትምግዴታ ነው፡፡

## የምዕራፍ 6 የመልመጃ ጥያቄዎች መልስ

### የመልመጃ 6.1 ጥያቄዎች መልስ

1. ሳንቲሞችን በመጠቀም፣ የግንባታ ስራ፣ጠንካራ የፖሊቲካ ስርዓት መኖር
2. ከንግድና ግብርና የሚገኝ ገቢ
3. አዱሊስና ዘይላ
4. ተመሳሳይ የፖሊቲካ ስርዓት መከተልና ሀይማኖትን ከመንግስት አስተዳደር ጋር የተሳሰረየአስተዳደርስርዓት መኖሩ

### 6.2.የሙከራ ጥያቄዎች

ተማሪዎች የሰሩትን የተግባር ስራ በመገምገም አጠናክሩት

1. በእርስ በርስ ግጭቶች ምክንያት የምጣኔ ሀብትና የፖሊቲካ የበላይነትን ለመቆጣጠር የሚደረገው ፉክክር መሆኑን ተማሪዎች እንዲገነዘቡ አድርጉ

### የመልመጃ 6.3.ጥያቄዎች መልስ

**I. እዉነት/ሐሰት**

1. **እዉነት** 2. **ሐሰት** 3. **እዉነት** 4. **እዉነት** 5. **እዉነት**

**II. ምርጫ**

1. ሐ 2. መ 3. ሐ 4. ሐ

## የምዕራፍ 6 የመልመጃ መልስ

I. የእዉነት/ሐሰትጥያቄዎች መልስ

1. እዉነት 2.እዉነት 3. እዉነት 4.ሐሰት

5. እዉነት6. እዉነት 7.ሐሰት

**II. የምርጫጥያቄዎች መልስ**

1. መ. 2. ለ 3. ለ 4. መ 5. መ 6. ለ

**III. የአጭር መልስ ስጥ/ጪጥያቄዎች መልስ**

1. ሚችሌ፣ሜልባ፣ሙደና፣ ኪሎሌ፣ እና ሮበሌ እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

2. በመንግስታዊ መዋቅር፣ በሀይማኖት እና በምጣኔ ሀብት እንቅስቃሴ ተያያዥነትአላቸው፡፡

3. እባክዎመምህር! የተማሪዎችን ሪፖርት በማዳመጥ ያቀረቡትን ሪፖርት ያጠናክሩ፡፡

# ምዕራፍ 7 ፡ልዩ ትኩረት የሚሹ የዓለም ጉዳዮች

**ከምዕራፉ የሚጠበቁ የመማር ውጤት**

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኃላ ተማሪዎች፡

- የአከባቢን ፅንሰ ሀሳብ ይገልፃሉ፤
- የሰዉ ልጅ በአከባቢ ላይ የሚያደርሰዉ ተፅዕኖን ይገልፃሉ፤
- በሀገርና በዓለም ደረጃ በአከባቢ ላይ የሚደርሱ ጉዳቶችን ይለያሉ፤
- በአከባቢ ጥበቃና እንክብካቤ ውስጥ ተሳትፎ ያደርጋሉ፤
- የህዝብ ቁጥር መጨመር በአከባቢ ላይ የሚያመጣዉን ጉዳት ያመዛዝናሉ፤
- የአሸባርነት ምንነትና በሰዉ፣ በኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ላይ የሚያመጣዉን ጉዳት ይገልፃሉ፤
- የህገ ወጥ የሰዎች ዝውውርና የስደት ምክንያት፤ በኢኮኖሚ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ላይ የሚያመጣዉን ጫና ይገልፃሉ።

**መግቢያ**

በዚህ ትምህርት ውስጥ ልዩ ትኩረት የሚሹ የዓለም ጉዳዮች ጋር የተያያዙትን ጉዳዮች ለምሳሌ የሚንኖርበት አከባቢ፤ የተፈጥሮአዊ አከባቢ ችግሮች(የአከባቢ ብክለት፣ የዓለም ሙቀት መጨመር፣ የኦዞን መሳሳት፣ አከባቢን የሚበክሉ የተለያዩ ቆሻሻዎች፣ የብዘ ህይወት ቁጥር መቀነስ ይማራሉ። እነዝህን ችግሮች ለመፍታት ልተኮርባቸዉ የሚገቡ ጉዳዮች አከባቢን መንከባከብ፣ በባዶ ቦታዎች ላይ እፅዋትን መትከል፣ ደን የጠፋባቸዉን ቦታዎችን መልሰዉ መትከል፣ ህብረተሰብን ማስተማር፣ የተፈጥሮ ሀብትን በቁጠባና መልሰዉ መጠቀም የህዝብ ቁጥር መጨመር፣ ሽብርተኝነትና ህገወጥ የሰዎች ዝውውር ናቸዉ።

## 7.1 የምንኖርበት አከባቢ

**የክፍለ ግዜ ብዛት --------------7**

### 7.1.1. **የምንኖርበት አከባቢ ማወቅ ------------------የክፍለ ግዜ ብዛት 1**

### 7.1.2. የተፈጥሮአዊ አከባቢ ትላልቅ ችግሮች---------የክፍለ ግዜ ብዛት 4

**ተማሪዎች ብያንስ ልደርሱበት የሚገባቸዉ የመማር ብቃት፣**

ከዚህ ርዕስ ትምህርት በኃላ ተማሪዎች፤

- የምንኖርበት አከባቢ ምንነት ይገልፃሉ፤
- በአከባቢያችን የሚገኙ ነገሮችን ይዘረዝራሉ፤
- የተፈጥሮኣዊ አከባቢ መሰረታዊ ችግሮችን ያመዛዝናሉ፤
- የአከባቢ ብክለት፣ የሙቀት መጨመርና የኦዞን ማሳሳት ምንነት ይገልፃሉ፤
- ብክለት፣ የሙቀት መጨመርና የኦዞን ማሳሳት የሚያደርሱትን ጉዳት ይገልፃሉ፤
- ለተፈጥሮ ሀብት የሚደረገዉ እንክብካቤ ምን እንደሆነ ይዘረዝራሉ፡፡

## ዋና ዋና ነጥቦች

በዚህ ትምህርት ርዕስ ሥር ተማሪዎች የሚማሩት ዋና ዋና ነጥቦች የምንኖርበት አከባቢ፤ የተፈጥሮዊ አከባቢ ችግሮች እንደ ብክለት፣ የሙቀት መጨመርና የኦዞን ማሳሳት፣ አከባብን የሚያቆሽሹ ነገሮችና የብዘ-ህይወት ቁጥር ማነስ ናቸዉ፡፡ ይህንን ርዕስ ተማሪዎች በደንብ እንድረዱና ሳይረሳ ለረጅም ግዜ እንድቆይ ለማድረግ በትምህርት ማበልፀግያ ማዕከል ያሉ ስዕሎችና ከእንተርኔት የተለያዩ ፎቶዎችን በማዉረድ ከዚህ ረዕስ ጋር የሚያያዙ በሌሎች መፃህፍት ላይ ያሉ ስዕሎችን መጠቀም ይቻላል፡፡

## ቅድመ ዝግጅት

ትምህርቱን ለማስተማር ከመጀመሮህ በፊት ከርዕሱ ጋር የሚያያዙ የመማር ማስተማር ዘዴዎች፤ ከብክለት፣ የዓለም ሙቀት መጨመርና የኦዞን ማሳሳት ጋር የሚያያዙ የተለያዩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡

## የመማር ማስተማር ዘዴዎች

የዚህን ርዕስ ትምህርት ማስተማር ከመጀመራችዉ በፍት የተማሪዎችን መፅሓፍና ሌሎች ካዝህ ርዕስ ጋር የሚያያዙ መፅሓፎችን በማንበብ መረጃዎችን መሰብሰብ ያስፈልጋል፡፡ ተማርዎች ከዚህ በፍት ያላቸዉ እዉቀት እንድናገሩ ለማድረግ ትምህርቱን በጥያቄ መጀመር ያስፈልጋል፡፡ በተቻለ መጠን ሁሉም ተማሪዎች እንድናገሩ ማበረታታት አስፈላግ ነዉ፡፡ የተማሪዎችን መልስ በጥቁር ሳሌዳ ላይ ፃፉ፡፡ ተማሪዎችን በቡድን በማደራጀት እንድወያዩ ማድረግ፡፡ በውይይቱ ወቅት ሁሉም ተማሪዎች አኩል እድሳተፉ ማድረግ፡፡ የተወያዩትን ተራ

በተራ ለክፍል ተማሪዎች እንድያቀርቡ ማድረግ። በመጨረሻም በትምህርቱ ላይ ግብረ መልስ በመስጠት በተማሪዎች መካከል ያለዉን ልዩነት ማጥበብ ያስፈልጋል።

## ልዩ ተሠጥዖና ከፍተኛ የሆነ ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎች

የተለየ ችሎታና ከፍ ያለ ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎችን በማገዝ የፈጠራ ችሎታቸውን እንዲያሳድጉ ማድረግ ያስፈልጋል። በውይይት ግዜ በፍጥነት መጨረስ ስለሚችሉ ርእሱን የበለጠ ለመረዳት የሚያስችል ተጨማሪ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት መስጠት ያስፈልጋል። ነገር ግን እነዚህን የተለየ ችሎታ ያላቸውን ተማሪዎች ለማገዝ ሲዘጋጁ በዝግታ የሚመሩና ሴት ተማሪዎች ተጨማሪ ሥራ በመስጠትና የሚፈለገው የመማር ብቃት ላይ እንዲደርሱ መርዳት ልረሳ የማይገባ ጉዳይ ነው።

## ተከታታይ ምዘና

ተማሪዎች ትምህርቱን ምን ያህል እንደተማሩና እንደተገነዘቡ ለማወቅ የማያቋርጥ ክትትል ያስፈልጋል። የተማሪዎቻችሁን ችሎታ ለመለየት የተለያዩ የምዘና ጥያቄዎችን ማዘጋጀት ያስፈልጋል። ተማሪዎች የሚያቀረቡት መልሶችን በመሰብሰብ በትምህርቱ ላይ ምን ያህል እዉቀትና ግንዛቤ እንዳገኙና የሚጠበቀዉ የመማር ብቃት ማግኘታቸዉን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። የተማሪዎችን ተሳትፎ በየቀኑ በማስታወሻ ደብተር ላይ መመዝገብ። ሁሉም ተማሪዎች ልደርሱበት የሚገባቸዉ እዉቀትና ግንዛቤ ማግኘት አለባቸዉ። የሚጠበቀዉ የመማር ብቃት ላይ መድረስ ያለቻሉ ተማሪዎች ልዩ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ የመማር ችሎታቸዉን ማሻሻል ያስፈልጋል።

## የመልመጃ 7.1 መልስ

1. የተፈጥሮ ሀብት(እንደ አፈር፣ ደን) ብክነት፤ የአየር ብክለት፣ የውሃ ብክለት፤ የዓለም ሙቀት መጨመርና የኦዞን መሳሳት።
2. ከመኪናዎች የሚወጣ ጪስ፤ የአረም መድሃንት፣ ፀረ ተባይ፣ ሰደድ እሳትና ከመኖሪያ ቤት የሚወጣ ጪስ።
3. እፅዋትን መትከልና ማንከባከብ፤ ተዳሽ የሆኑ የተፈጥሮ ሀብቶችን መጠቀም፤ አከባቢን የሚበክሉ ፈሳሽ ነገሮችን ወደ አከባቢ አለመልቀቅና የአከባቢን ንፅህና መጠበቅ ናቸዉ።

4. ካርቦንዳይኦክሳይድ(የመኪና ጪስ፣ ከፋብርካ የሚወጣ ጪስ የእሳተ ጋሞራ ጪስ) በተፈጥሮ ከሚገኙ በላይ ወደ ከባቢ አየር ስቀላቀሉ ነዉ፡፡ በከባቢ አየር ውስጥ የካርቦንዳይኦክሳይድ መጠን መብዛት ከባቢ አየር ስለሚታመቅ የዓለም ሙቀት እንድጨምር ያደርጋል፡፡
5. የተፈጥሮ ሀብትን ማንከባከብ፣ በቁጠባ መጠቀም፣ ህብረተሰብን ማስተማርና የመሳሰሉት ናቸዉ፡፡

## 7.2. የህዝብ ቁጥር መጨመር

የተሰጠ የክፍለ ግዜ ብዛት -------------1

**ተማሪዎች ብያንስ ማግኘት የሚገባቸዉ የመማር ብቃት፣**

ከዚህ ርዕስ ትምህርት በኃላ ተማሪዎች፤

- የአከባቢ እንክብካቤ ምንነት ይገልፃሉ፤
- ለተለያዩ የተፈጥሮ ሀብቶች የሚደረገዉ እንክብካቤ ይዘረዝራሉ፤
- ለተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤ የሚደረግላቸዉን መንገዶች ይገልፃሉ፤
- የህዝብ ቁጥር መጨመር በተፈጥሮ ሀብት ላይ የሚደርሰዉን ጉዳት ይገልፃሉ፡፡

### ዋና ዋና ነጥቦች

ባለፉት ትምህርት ውስጥ የተለያዩ ትላልቅ የተፈጥሮ ሀብት ችግሮች እንደ ብክለት፣ የዓለም ሙቀት መጨመር፣ የኦዞን ማሳሳት፣ የብዘ-ህይወት ቁጥር ማነስ ተምራቹዋል፡፡ በዚህ ትምህርት ውስጥ ደግሞ አከባቢን ማንከባከብ፣ እፅዋቶችን መትከል፣ ደን የጠፋባቸዉን አከባቢዎች መልሰዉ መትከል፣ ማህበረሰብን ማስተማር፣ በተፈጥሮ ሀብት በጥንቃቄ መጠቀምና የህዝብ ቁጥር መጨመርን ይማራሉ፡፡ ይህንን ትምህርት በደንብ እንድረዱና ለረጅም ግዜ ሳይረሳ እንድቆይ ለማድረግ ከአከባቢ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በመያያዝ ማስተማር ያስፈልጋል፡፡

## ቅድመ ዝግጅት

ይህንን ርዕስ ማስተማር ከመጀመራችዉ በፍት ከዚህ ትምህርት ጋር ልሔዱ የሚችሉ የተለያዩ መርጃ መሳሪያዎችን ማዘጋጀት ያስፈልጋል።

## የመማር ማስተማር ዘዴዎች

ተማሪዎች ትምህርቱን ከሚያዉቁት እንድነሱ በማድረግ ትምህርቱን በጥያቄ መልክ መጀመር ያስፈልጋል። ለምሳሌ የአከባቢ እንክብካቤ ማለት ምን ማለት ነዉ? የሚትኖሩበት መህብረሰብ አከባቢያቸዉን የሚያንከባክቡት እንዴት ነዉ?

የህዝብ ቁጥር መጨመር ማለት ምን ማለት ነዉ? በህዝብ ቁጥር መጨመር ምክንያት የሚመጡ ችግሮች ምን ምን ናቸዉ? የሚሉ ጥያቄዎችን መጠየቅ ያስፈልጋል፡፡ እነዝህን ጥያቄዎች ተማሪዎች የሚያዉቁትን እንድናገሩ ማበረታታት ያሰፈልጋል። በተቻለ መጠን ሁሉም ተማሪዎች እድል እንድያገኙ ማድረግ አስፈላጊ ነዉ። የተማሪዎችን መልስ በጥቁር ሳሌዳ ላይ ፃፉ። ተማሪዎችን እንደ ክፍላቸዉ ተጨባጭ ሁነታ በቡድን ማደራጀትና እንድወያዩ ማድረግ፡፡ በውይይቱ ወቅት ሁሉም ተማሪዎች አኩል እድሳተፉ ማድረግ። የተወያዩትን ተራ በተራ ለክፍል ተማሪዎች እንድያቀርቡ ማድረግ፡፡ በመጨረሻም በትምህርቱ ላይ ግብረ መልስ በመስጠት በተማሪዎች መካከል ያለዉን ልዩነት ማጥበብ ያስፈልጋል።

## ልዩ ተሠጥዖና ከፍተኛ የሆነ ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎች

የተለየ ችሎታና ከፍ ያለ ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎችን በማገዝ የፈጠራ ችሎታቸውን እንዲያሳድጉ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በውይይት ግዜ በፍጥነት መጨረስ ስለሚችሉ ርእሱን የበለጠ ለመረዳት የሚያስችል ተጨማሪ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት መስጠት ያስፈልጋል። ነገር ግን እነዚህን የተለየ ችሎታ ያላቸውን ተማሪዎች ለማገዝ ሲዘጋጁ በዝግታ የሚመሩና ሴት ተማሪዎች ተጨማሪ ሥራ በመስጠትና የሚፈለገው የመማር ብቃት ላይ እንዲደርሱ መርዳት ልረሳ የማይገባ ጉዳይ ነው።

## ተከታታይ ምዘና

ተማሪዎች ትምህርቱን ምን ያህል እንደተማሩና እንደተገነዘቡ ለማወቅ የማያቋርጥ ክትትል ያስፈልጋል፡፡ የተማሪዎቻችሁን ችሎታ ለመለየት የተለያዩ የምዘና ጥያቄዎችን ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ ተማሪዎች የሚያቀርቡትን መልሶች በመሰብሰብ በትምህርቱ ላይ ምን ያህል እዉቀትና ግንዛቤ እንዳገኙና የሚጠበቀዉ የመማር ብቃት ማግኘታቸዉን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ የተማሪዎችን ተሳትፎ በየቀኑ በማስታወሻ ደብተር ላይ መመዝገብ፡፡ ሁሉም ተማሪዎች ልደርሱበት የሚገባቸዉ እዉቀትና ግንዛቤ ማግኘት አለባቸዉ፡፡ የመማር ብቃት ላይ መድረስ ያልቻሉ ተማሪዎች ልዩ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ የመማር ችሎታቸዉን ማሻሻል ያስፈልጋል፡፡

# 7.3. ሽብርተኝነት

**ተማሪዎች ብያንስ ማግኘት የሚገባቸዉ የመማር ብቃት**

ከዚህ ርዕስ ትምህርት በኃላ ተማሪዎች፤

- የሽብርተኝነት ምንነት ይገለፃሉ፤
- ሽብርተኝንት በሰዉ ህይወት፣ በንብረት፣ በማህበራዊና ኢኮኖሚ ላይ የሚያመጣዉን ጉዳት ይገልፃሉ፡፡

## ዋና ዋና ነጥብ

ባለፉት ትምህርት ውስጥ ተማሪዎች ስለ ህዝብ ቁጥር መጨመር ተምሩዋል፡፡ በዚህ ትምህርት ውስጥ ደግሞ ስለ ሽብርተኝነትና የሚያመጠዉን ችግር ይማራሉ፡፡

## ቅድመ ዝግጅት

የዚህን ርዕስ ትምህርት ለማስተማር ወደ መማሪያ ክፍል ከመግባታችሁ በፍት ስለ ሽብርተኝነት ምንነትና በሽብርተኝነት ልመጡ የሚችሉ ጉዳቶች ላይ በቂ ትምህርት መስጠት የሚችሉ የተለያዩ መርጃ መሣሪያዎችን እንደ ስዕል፣ ፎቶና ቻርት ያሉትን ከተለያዩ የታሪክ መፅሃፍ፣ ከተለያዩ መፅሐፎችና ከእንተርኔት በመፈለግ መዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡

## የመማር ማስተማር ዘዴዎች

የዚህን ርዕስ ትምህርት ለማስተማር መጀመሪያ ተማሪዎች ከሚያዉቁት ነገር እንድጀምሩ በማድረግ በተለያዩ ጥያቄዎች ለምሣሌ ሽብርተኝነት ምንድነዉ? በሚሉ መጀመር ያስፈልጋል፡፡ ተማሪዎች መጀመሪያ ለብቻቸዉ እንድያስቡ ማድረግ፤ በመቀጠል ሁለት ሁለት ሆነዉ፤ በቡድን በማደራጀት እንድወያዩ ማድረግ ይቻላል፡፡ ውይይታቸዉን ከጨረሱ በኃላ ከዚህ በፍት ዕድል ላላገኙ ተማሪዎች ቅድሚያ በመስጠት በተቻለ መጠን ሁሉም ተማሪዎች እንድናገሩ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በመጨረሻም ተማሪዎች ከመወያየታቸዉ በፍትና ከተወያዩ በኃላ ያላቸዉን የግንዛቤ ልዩነት ምን እንደሆነ በመገምገም ግብረ መልስ መስጠት አስፈላግ ነዉ፡፡

## ልዩ ተሠጥዖ እና ከፍተኛ የሆነ ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎች

የተለየ ችሎታና ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎችን በማገዝ የፈጠራ ችሎታቸውን እንዲያሳድጉ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በውይይት ግዜ በፍጥነት መጨረስ ስለሚችሉ ርእሱን የበለጠ ለመረዳት የሚያስችል ተጨማሪ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት መስጠት ያስፈልጋል፡፡ ነገር ግን እነዚህን የተለየ ችሎታ ያላቸውን ተማሪዎች ለማገዝ ሲዘጋጁ በዝግታ የሚመሩና ሴት ተማሪዎች ተጨማሪ ሥራ በመስጠትና የሚፈለገው የመማር ብቃት ላይ እንዲደርሱ መርዳት ልረሳ የማይገባ ጉዳይ ነው፡፡

## ተከታታይ ምዘና

ተማሪዎች ትምህርቱን ምን ያህል እንደተማሩና እንደተገነዘቡ ለማወቅ የማያቋርጥ ክትትል ያስፈልጋል፡፡ የተማሪዎቻችሁን ችሎታ ለመለየት የተለያዩ የምዘና ጥያቄዎችን ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ ተማሪዎች የሚያቀረቡትን መልሶች በመሰብሰብ በትምህርቱ ላይ ምን ያህል እዉቀትና ግንዛቤ እንዳገኙና የሚጠበቀዉ የመማር ብቃት ማግኘታቸዉን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ የተማሪዎችን ተሳትፎ በየቀኑ በማስታወሻ ደብተር ላይ መመዝገብ፡፡ ሁሉም ተማሪዎች ልደርሱበት የሚገባቸዉ እዉቀትና ግንዛቤ ማግኘት አለባቸዉ፡፡ የሚጠበቀዉ የመማር ብቃት ላይ መድረስ ያልቻሉ ተማሪዎች ልዩ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ የመማር ችሎታቸዉን ማሻሻል ያስፈልጋል፡፡

## የመልመጃ 7.2. መልስ

1. መከባበር፣ የጋራ መብቶችን መክበር፣ የአከባቢ ፀጥታን መጠበቅና የመሳሰሉት ናቸዉ፡፡
2. ሽብርተኝነትን ለመከላከል ሀገራት በጋራ መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡ በሰላም ጉዳይ ላይ ወቅታዊ መረጃን መያዝ ያስፈልጋል፡፡

## 7.4. በህገ ወጥ መንገድ የሰዎች ዝውውር

**ተማሪዎች ብያንስ ማግኘት የሚገባቸዉ የመማር ብቃት**

ከዚህ ርዕስ ትምህርት በኃላ ተማሪዎች፤

- ህገ ወጥ የሰዎች ዝውውር ምክንያቶችና በማህበራዊ፣ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ የሚያደርሰዉ ጉዳቶች ምን እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡

የክፍለ ግዜ ብዛት ------------------------------2

### ዋና ዋና ነጥብ

ተማሪዎች ባለፉት ትምህርት ላይ ስለ ሽብርተኝነትና የሚያደርሰዉ ጉዳት ተምሩዋል፡፡ በዚህ ትምህርት ላይ ደግሞ ህገ ወጥ የሰዎች ዝውውርና በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ የሚያደርሰዉ ጉዳቶች ምን ምን እንደሆነ ይማራሉ፡፡

### ቅድመ ዝግጅት

የዚህን ርእስ ለማስተማር የተለያዩ መርጃ መሣሪያዎችን እንደ ህገ ወጥ ስደትን የምያሳዩ ሥዕል፣ ፎቶ ከተቻለ የተቀረፀ ቪድዮ መጠቀም ያስፈልጋል፡፡ ህገ ወጥ የሰዎች ዝውውር በማህበረሰብ ላይ በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለትካዊ ጉዳዮች የሚያመጣዉ ችግር ምን እንደሆነ ተማሪዎችን በደንብ እንድረዱ ለማድረገና እንዴት ማስተማር እንዳለብን ቀድመን ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡

### የመማር ማስተማር ዘዴ

የዚህን ርዕስ ትምህርት ለማስተማር ህገ ወጥ የሰዎች ዝውውር ምን እንደሆነ የተማሪዎችን መፅሓፍና ሌሎች ፅሑፎችን በማንበብ በቂ የሆነ እዉቀትና ግንዛቤ መያዝ ይኖርባቸዋል፡፡ ትምህርቱን ከመጀመራችሁ በፍት በጥያቄዎች መጀመር ያስፈልጋል፡፡ ለምሳሌ ህገ ወጥ

የሰዎች ዝውውር ማለት ምን ማለት ነዉ? ህገ ወጥ የሰዎች መዘዋወር የሚያደርሰዉ ጉዳት ምንድነዉ? በእነዝህ ጥያቄዎች ላይ ተማሪዎች መጀመሪያ የሚያዉቁትን እንድናገሩ ማድረግ። በተቻለ መጠን ሁሉም ተማሪዎች የሚያዉቁትን እንድናገሩ ዕድል መስጠት። ከዚህ በኃላ እንደ የክፍሉ ተጨባጭ ሁኔታ ተማሪዎችን በቡድን በመከፋፈል እንድወያዩ ማድረግ ያስፈልጋል። በውይይት ወቅት ሁሉም ተማሪዎች መሳተፋቸዉን መከታተል አስፈላግ ነዉ። የተወያዩትን ተራ በተራ እንድናገሩ ማድረግ ያስፈልጋል። በመጨረሻም በተማሪዎች መካከል ያለዉን ልዩነት ለማጥበብ መሞከርና ግብረ መልስ መስጠት አስፈላግ ነዉ።

## ልዩ ተሠጥዖና ከፍተኛ የሆነ ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎች

የተለየ ችሎታና ከፍ ያለ ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎችን በማገዝ የፈጠራ ችሎታቸውን እንዲያሳድጉ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በውይይት ግዜ በፍጥነት መጨረስ ስለሚችሉ ርእሱን የበለጠ ለመረዳት የሚያስችል ተጨማሪ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት መስጠት ያስፈልጋል። ነገር ግን እነዚህን የተለየ ችሎታ ያላቸውን ተማሪዎች ለማገዝ ሲዘጋጁ በዝግታ የሚመሩ እና ሴት ተማሪዎች ተጨማሪ ሥራ በመስጠትና የሚፈለገው የመማር ብቃት ላይ እንዲደርሱ ለማድረግ መርዳት ልረሳ የማይገባ ጉዳይ ነው።

## ተከታታይ ምዘና

ተማሪዎች ትምህርቱን ምን ያህል እንደተማሩና እንደተገነዘቡ ለማወቅ የማያቋርጥ ክትትል ያስፈልጋል። የተማሪዎቻችሁን ችሎታ ለመለየት የተለያዩ የምዘና ጥያቄዎችን ማዘጋጀት ያስፈልጋል። ተማሪዎች የሚያቀረቡትን መልሶችን በመሰብሰብ በትምህርቱ ላይ ምን ያህል እዉቀትና ግንዛቤ እንዳገኙና የሚጠበቀዉ የመማር ብቃት ማግኘታቸዉን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። የተማሪዎችን ተሳትፎ በየቀኑ በማስታወሻ ደብተር ላይ መመዝገብ። ሁሉም ተማሪዎች ልደርሱበት የሚገባቸዉ እዉቀትና ግንዛቤ ማግኘት አለባቸዉ። የሚጠበቀዉ የመማር ብቃት ላይ መድረስ ያለቻሉ ተማሪዎች ልዩ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ የመማር ችሎታቸዉን ማሻሻል ያስፈልጋል።

## የመልመጃ 7.3 መልስ

1. ከአቅም በላይ የሆነ ሥራ ማሰራት፤ የአካል ጉዳት፤ በተለያዩ ወንጀሎች ላይ በግድ እንድሳተፉ ማድረግ፤አስገድዶ መድፈር፤ ልጆች ከቤተሰብ በመለየትና ለተለያዩ ችግሮች መጋለጥ
2. ወጣቶችና ህፃናት
3. ሰዎችን በገንዘብና በጥቅማ ጥቅም በማታለልና ለህገ ወጥ የሰዎች ዝውውር እንድጋለጡ ማድረግ፤
4. ሰራተኛና አሠሪ አገናኝ በሚል ስም ፤ ሰዎችን የተሻለ ሥራና ክፍያ ታገኛላችዉ በማለት ሰዎችን በማታለል ገንዘብ በመቀበል ለሌሎች ደላላዎች ማስተላለፍ ከሀገር እንድወጡ በማድረግ።

## የምዕራፍ 7 የማጠቃለያ ጥያቄዎች መልስ

ክፍል 1.

1. እዉነት 2. ሀሰት 3. እዉነት 4. ሀሰት

ክፍል 2. ምርጫ

1. ለ 2. ሐ 3. ሀ

ክፍል 3. አዛምድ

1. ሐ 2. ሀ 3. ለ 4. መ 5. ሠ

## ዋቢ መጽሐፍት


Asmarom Legesse. *Gada: Three approaches to the study of African society*. 2nd ed, New York: Free Press.1973.

________. Oromo Democracy: An indigenous African political system, New York: Red Sea printing INC,.2006

Badasa Gebisa Ago. "Freedom of *Waqeffannaa* Religion in Ethiopia Post 1991," *IJRSI* published, 2(9), 2015.

Bartels, Lambert. *Oromo Religion: Myths and Rites of the Western Oromo of Ethiopia-an Attempt to Understand*. Berlin: Reimer press. 1983.

Bichaka Fayisa."Some Aspects of the Vision and Effectiveness of Oromo Organizations."*In the journal of Oromo Studies,* 1(2), 1994.

Curtin, Philip etal .*African History:From Earlier time to Independence.*London and New York: Longman, 1995

Davidson, B. *(1967).The Growth of African Civilization: East and Central Africa to the later Nineteenth Century*

De Salviac,Martial**.***Ancient People Great African Nation: the Oromo*. (2nd ed.).Translated by Ayalew Kenno. Addis Ababa: Oromia Culture and Tourism Bureau. 2008.

Dirribi Damise. *Ilaalcha Oromoo: Barroo Adaa, Seenaa fi Amanta Oromo*. Finfinnee: Finfinne Printing and publishing S. C. 2012.

Honorary, Marcell,D.and John. *Ancient and Medieval history*; LarousseEncyclopedia.4th ed. Newyork,1972.

Mohaammad Hassan. *The Oromo of Ethiopia: A History 1570-1860*.Trent one: Red sea Press, 1994 a.

Pankhurst, Richard. *A Social History of Ethiopia: The Northern and Central Highlands from Early Medieval Times to the Rise of Emperor Tewodros II.* Addis Ababa: Addis Ababa University press, 1990.

Tasama Ta'a. "*The Place of the Oromo in Ethiopian History:"* In 2003 OSA Conference Keynote in *the Journal of Oromo Studies. Edited by* Bichaka Feyisa11 (1&2), 2004.

Shillington, Kevin. *History of Africa*, 3rd ed. PalgraveMacymilian 2012.***Also available, www.palagrave.com.***

Smart, Ninian.*The World's Religions.*2nd ed. Cambridge: Cambridge University Press, 1998.

Summer, Claude. *Oromo Wisdom Literature*: Songs, vol-2. Addis Ababa: Gudina Tumsa Foundation press, 1997.

S. Lewis, Herbert. *The Development of Oromo Political Consciousness from 1958to1994*, in the international research work, Being and becoming Oromo: Historical and Anthropological Enquiries .Asmara: The Red Sea Press, Inc.Eri.1996.

# የሕብረተሰብ ትምህርት
# መርሐ ትምህርት 7ኛ ክፍል

## ምዕራፍ 1: የመሬት አፈጣጠር ባህሪያት

**የክፍለ ጊዜ ብዛት --------------------------- 20**

**ከምዕራፉ ትምህርት የሚጠበቁ የመማር ውጤቶች:**

**ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ትምህርት ተምረዉ ከጨረሱ በኃላ፤**

- የመሬትና የሥርዓተ ፀሓይ አፈጣጠር እንዴት እንደሆነ ይገልፃሉ፤
- አራቱ የመሬት ይዘቶችና እርስ በርስ ያላቸዉ ግንኙነት ምን እንደሆነ ይገልፃሉ፤
- የመሬት ንብርብሮችና ያላቸዉ ባህሪያት ምን እንደሆነ ይገልፃሉ፤
- ስለ የመሬት ውስጣዊ ክፍሎች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚገኙ የመረጃ ምንጮችን ይለያሉ፤
- ውጫዊ የመሬት ክፍል የተሰራባቸዉ ማዕድናት፣ ዓለቶችና ንጥረ ነገሮችን ይለያሉ፤
- በኢትዮጵያ ውስጥ የዓለቶች ሥርጭትና በኢኮኖሚ ላይ ያላቸዉ ጠቀሜታ ምን እንደሆነ ያመዛዝናሉ፡፡

| የመማር ብቃቶች | ይዘቶች | የመማር ማስተማር ዘዴዎች | ግምገማ |
|---|---|---|---|
| • የመሬትና የሥርዓተ ፀሓይ አፈጣጠርና ቅርፃቸዉን እንዴት እንደያዙ ለመረዳት ውይይት ያደርጋሉ፤<br>• አራቱ የመሬት ይዘቶችን (ሊቶስፌር፣ ባዮስፌር፣ ሃይድሮስፌርና አትሞስፌር) ይገልፃሉ፤<br>• በተለያዩ የመሬት ንብርብሮች ውስጥ የሚገኙ ነገሮች ለምን እንደ ተለያዩ ይገመግማሉ፤<br>• የመሬት ውጫዊ ክፍል የተሰራባቸዉን ማዕድናት፣ ዓለቶችና ንጥረ ነገሮችን ይለያሉ። | **1. የመሬት አፈጣጠር ባህሪያት**<br>1.1.የመሬት አፈጣጠርና ሥርዓተ ፀሀይ<br>1.2. ውጫዊ የመሬት ይዘትና በውስጣዊ የመሬት ክፍል የሚገኙ መዋቅሮች<br>1.2.1. በመሬት ገፅታ ላይ የሚገኙ ይዘቶች (ሊቶስፌር፣ ባዮስፌር፣ ሃይድሮስፌርና አትሞስፌር)<br>1.2.2. የመሬት ውስጣዊ ክፍልና የመረጃ ምንጮች | ▪ ተማሪዎች የመሬትና የሥርዓተ ፀሓይ አፈጣጠር ሁኔታ ላይ ሀሳብ እንድሰጡ የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ማነቃቃት፣ በተማሪዎች መካከል ያለዉን ልዩነት ለማጥብብ በቂ መብራሪያ ማስጠትና ተመሳሳይ የሆነ ግንዛቤ እንድያገኙ ማድረግ።<br>▪ በክፍል ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎችን በቡድን በመክፈል ስለውስጣዊና ውጫዊ መሬት ክፍሎች ላይ ውይይት እንድያደርጉ በማድረግና የተስማሙበትን ነጥብ በተወካያቸዉ አማካይነት እንድያቀርቡ ማድረግ። | መምህራን በክፍል ውስጥ በመዘዋወር ተማሪዎችን በቡድን ውስጥ የሚያደርጉትን ተሳትፎ መከታተል። በመቀጠል ሀሳባቸዉን በማቀናጀት በተወካያቸዉ አማካይነት እንድያቀርቡ ማድረግ፤ በመጨረሻም በቂ የሆነ መብራሪያና ግብረ መልስ መስጠት። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| • ስለመሬት ውስጣዊ ክፍሎች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚገኙ መረጃዎች ልዩነት ይለያሉ፤<br>• በኢትዮጵያ ውስጥ የተለያዩ ዓለቶች ስርጭትና በኢኮኖሚ ውስጥ ያላቸዉ ጠቀሜታ ምን እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡ | 1.2.2.1. ስለመሬት ውስጣዊ ክፍሎች የመረጃ ምንጮች<br>1.2.2.2. የመሬት ንብርብሮች (ቅርፍተ መሬት መካከለኛና እምብርተ መሬት)<br>1.3. ቅርፍተ መሬት የተሰራባቸዉ ነገሮች<br>1.3.1. ትላልቅ ንጥረ ነገሮች<br>1.3.2. ትላልቅ ማዕድናት<br>1.3.3. ቅርፍተ መሬት የተሰራባቸዉ ትላልቅ ዓለቶች<br>1.4. በኢትዮጵያ ውስጥ የዓለቶች ስርጭትና በኢኮኖሚ ውስጥ ያለዉ | ▪ ተማሪዎችን በሶስት ቡድን በመክፈል አንዱ ቡድን ስለ ማዕድናት፣ ሁለተኛዉ ቡድን ስለዓለቶችና ሶስተኛዉ ቡድን ስለንጥረ ነገሮች የተፃፉትን እንድያነቡና እንድወያዩበት ማድረግ፡፡ በመቀጠልም በተወካያቸዉ አማካይነት ለክፍል እንድያቀርቡ ማድረግና በመጨረሻም መምህራን የማጠቃለያ ሀሳብ መስጠት ያስፈልጋል፡፡<br>▪ተማሪዎች የተለያዩ ዓለቶች ናሙና ወደ ክፍል በማምጣትና በአከባቢያቸዉ ለምን ዓይነት አገልግሎት እንደሚዉሉ እንድገልፁ ማድረግ ያስፈልጋል፡ | • መምህራን ተማሪዎች በቡድናቸዉ ውስጥ ለሚያደርጉት የነቃ ተሳትፎ ዋጋ መስጠትና ማበረታታት፡፡ መምህራን<br>• የተማሪዎች ውይይት ውጤታማ እንድሆን ለማድረግ ተማሪዎች በጥያቄና መልስ እንድሳተፉ ማድረግ፡፡<br>• ተማሪዎች ባቀረቡት ሀሳብ ላይ ገንቢ የሆነ ግብረ መልስ መስጠትና ማጠቃለል፡፡ ,<br>• የተማሪዎችን የቡድን ውይይት ውጤታማ ለማድረግ መምህራን የየራሳቸዉን ዘዴ በመጠቀም ተማሪዎችን መርዳት፡፡ |

# ምዕራፍ 2፡ የሰዉ ልጅ ዘገምተናዊ ለውጥና የዓለም ህዝብ

**የክፈለ ጊዜ ብዛት ---------------------------- 27**

**ከምእራፉ ትምህርት የሚጠበቁ የመማር ውጤቶች:**

**ተማሪዎች ይህንን የምዕራፉን ትምህርት ተምረዉ ከጨረሱ በኃላ፤**

- ስለ የሰዉ ልጅ አፈጣጠር ምንነት ይገልፃሉ፤
- ስለ የሰዉ ልጅ መገኛ የሚያሳዩ የአርኪዮሎጂ የምርምር ቦታዎችን ያሳያሉ፤
- ስለ የሰዉ ልጅ ስርጭትና በቁጥር እየጨመረ መሄድ ይገልፃሉ፤
- በሰዉ ልጅ ቁጥር መለያየት ተፅዕኖ የሚያደርጉ ነገሮች(ውልደት፣ ስደትና ሞት) ሂሳባዊ ስሌት ይሰራሉ፤
- የመጓጓዧ ዓይነቶችና ያላቸዉ ድርሻ ምን እንደሆነ ይገመግማሉ፤
- መሰረታዊ የመንገድ ላይ ምልክቶችን በመለየት በካርታ ላይ ያሳያሉ፡፡

| የመማር ብቃቶች | ይዘቶች | የመማር ማስተማር ዘዴዎች | ግምገማ |
|---|---|---|---|
| • የሰዉ ልጅ የአርኪዮሎጂ መገኛ የሆኑ ቦታዎችን ያሳያሉ፡፡<br>• የሰዉ ዘር መገኛና ያለፈባቸዉ ታሪካዊ ክስተቶች ምን እንደሆኑ ይገመግማሉ፡፡<br>• አሁን ያለዉና በፊት የነበረዉን መነሻ በማድረግ ወደፍት የሚኖረዉን የዓለም የህዝብ ቁጥርን ይገምታሉ፡፡ | **2.** የሰዉ ልጅ ዘገምተናዊ ለውጥና ዓለም የህዝብ<br><br>2.1. የሰዉ ዘር ዘገምተናዊ ለውጥ<br><br>2.1.1.አርኪዮሎጂና የአርኪዮሎጂ የምርምር ሥራዎች<br><br>2.1.2. የመጀመሪያ ሰዉ መገኛ<br><br>2.1.3. የሰዉ ልጅ ያለፈባቸዉ ታሪካዊ ክስተቶች | • የሰዉ ልጅ አፈጣጠር ላይ ተማሪዎችን የግንዛቤ ጥያቄዎችን መጠየቅ፤<br>• በተማሪዎች መካከል ያለዉ ልዩነት ለማጥበብ መምህራን በሰዉ ልጅ አፈጣጠር ላይ ትክክለኛና በቂ የሆነ መብራሪያ መስጠት፤<br>• መምህራን የዓለም ህዝብ ቁጥርን የሚያሳይ ግራፍ በማዘጋጀትና ወደ ክፍል በማምጣት ተማሪዎች የዓለም ህዝብ ቁጥር እያደገ መሄዱን እንድረዱ ማድረግ፤<br>• ተማሪዎችን በቡድን በመክፈል የህዝብ ቁጥር እየጨመረ መሄድና ሥርጭት ማወቅ ምን ጥቅም እንደለዉ ከተወያዩ በኋላ ያለዉ ጠቀሜታ ምን እንደሆነ እንድገልፁ ማድረግ፡፡ | • መምህራን ተማሪዎች ምን ያህል እንደተሳተፉ ለማወቅ በየግዜዉ ማስታወሻ እየያዙ መሄድ፤<br>• ተማሪዎችን የሚያበረታታ ግብረ መልስ መስጠት፤<br>• የዓለም ህዝብ ቁጥር መጨመር የሚያሳይ ግራፍ እንዴት እንደሚለዩ ለተማሪዎች ግንዛቤ መስጠት፤<br>• ለምን የህዝብ ቁጥር መለያየት እንደሚከሰት ተማሪዎችን መጠየቅ፡፡ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| • ተማሪዎች ውልደት፣ ሞትና ስደት እንዴት የህዝብ ቁጥር መጨመርና መቀነስ ላይ ተፅዕኖ እንደሚያመጡ ሂሳባዊ ስሌት ይሰራሉ፤<br>• የህዝባዊ እንቅስቃሴዎች ዓይነትና ምክንያቶችን ይለያሉ፤<br>• በካርት ላይ ህዝብ ተጠጋግተዉና ተበታትነዉ የሚኖሩባቸዉን አከባቢዎችን ያሳያሉ፤<br>• የዓለም ህዝብ ቁጥር መነሻ በማድረግ የኢትዮጵያ የህዝብ ቁጥርን ይገመግማሉ፤<br>• ከመጓጓዥ ጋር በተያያዘ የቃላትና የፅንሰ-ሀሳብ ፍቺዎችን ይሰጣሉ<br>• የመጓጓዣ ታሪካዊ የእድገት ደረጃን ይገልፃሉ፤<br>• የተለያዩ የመጓጓዣ ዓይነቶችን ጥቅማቸዉንና ድርሻቸዉን ይገመግማሉ፤<br>• ጥቅሞቻቸዉን መሰረት በማድረግ የመጓጓዣ ዓይነቶችን ያወዳድራሉ፡፡<br>• በመንገድ ላይ የሚገኙ የትራፍክ ምልክቶች ጥቅም ይለያሉ፤<br>• መሰረታዊ የሆኑ የትራፍክ | 2.2.2. የህዝብ ቁጥር መቀያየርና ባህሪያት<br>2.2.3. የህዝብ ሥርጭት<br>• በህዝብ ሥርጭት ላይ ተፅዕኖ የሚያመጡ ነገሮች<br>• የዓለም የህዝብ ሥርጭት<br>2.2.4. የህዝብ እንቅስቃሴ (በሀገር ውስጥና ውጪ)<br>2.2.5. የህዝብ ጥግግት በከተማና በገጠር<br>2.3. ህዝብና የመጓጓዣ እድገት<br>2.3.1. የመጓጓዣ ፅንሰ ሀሳብና የእድገት ደረጃ<br>2.3.2. መጓጓዣ በማህበራዊና ኢኮኖሚ እድገት ውስጥ ያለዉ ድርሻ<br>2.3.3. የመጓጓዣ ዓይነቶች<br>➢ የየብስ መጓጓዣ<br>➢ የአየር መጓጓዣ<br>➢ የውሃ ላይ መጓጓዣ<br>2.3.4. የመንገድ ላይ ደንነት፣ የትራፍክ አደጋዎች፣ በማህበራዊና ኢኮኖሚ ላይ የሚያደርሰዉ ጉዳት | • በክፍል ውስጥ የህዝብ ቁጥር መቀያየር (ውልደት፣ ሞትና ስደት) በሂሳባዊ ስሌት ማስራት እንድችሉ በቂ የሆነ መብራሪያ መስጠት፤<br>• መምህራን የህዝብ ፒራምድ በመጠቀም የፆታ፣ የእድሜ፣ የጥገኞችና የአምራቾች እምርታ በመለየት ማሳየት<br>• ተማሪዎች በቡድን ሆነዉ ስለስደት፣ ውልደትና ሞት ሂሳባዊ ቀመሩን እንድሰሩ ማድረግ፤<br>• ተማሪዎችን በአምስት ቡድን በመክፈል የኢትዮጵያ የህዝብ ስርጭትና በቁጥር መጨመር ላይ እንድወያዩ ማድረግ፤<br>• የህዝብ ስርጭትን ለማስተማር ተማሪዎች የቀበሌያቸዉን የህዝብ ስርጭትን እንድገልፁ ማድረግ፤ ህዝብ ለምን አንዳንድ ቦታ ላይ ተጠጋግተዉና በሌላ ቦታ ተበታትነዉ እንደሚኖሩ መጠየቅ፤ በመቀጠል የህዝብ ሁኔታ በዓለም ላይ እንዴት ተፅዕኖ እንደሚያመጣ መጠየቅ፤ በኢትዮጵያ ህዝብ አጨማመር ላይ ተማሪዎች ሃሳብ እንድሰጡ ማድረግ፤<br>• ሁለት ተማሪዎች በቡድን ውይይት ላይ ማጠቃለያ እንድሰጡ ማድረግ፤<br>• ተማሪዎች ከመማሪያ መፅሐፋቸዉ የሰዉ ልጅ ስርጭትና የእድገት ደረጃ፤ የመጓጓዣ ዓይነቶችና ጥቅማቸዉን፤የትራፍክ አደጋዎችና ህጎች እንድገነዘቡ ማድረግ፤<br>• ተማሪዎች በአከባቢያቸዉ የመስክ ጉብኝት በማድረግ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ የእድገት ደረጃቸዉ ምን እንደሚመስል እንድገልፁ ማድረግ፡፡ | • ተማሪዎች በቡድናቸዉ ውስጥ የሚያደርጉትን ተሳትፎ መመልከትና መገምገም፡፡ |

# ምዕራፍ 3፡ ሰዉና የተፈጥሮ ሀብት

**የክፍለ ጊዜ ብዛት --------------------------- 11**

**ከምእራፉ ትምህርት የሚጠበቁ የመማር ውጤቶች:**

**ተማሪዎች ይህንን የምዕራፉን ትምህርት ተምረዉ ከጨረሱ በኃላ፤**

- ❖ በሰዉ ልጅና በተፈጥሮ ሀብት መካከል ያለዉ ግንኙነት ምን እንደሆነ ይገልፃሉ፤
- ❖ የተፈጥሮ ሃብትን በመገኛቸዉና በሚሰጡት ጥቅም መሰረት ይመድባሉ፤
- ❖ በተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም ላይ ተፅዕና ማድረስ የሚችሉ ነገሮችን ይዘረዝራሉ፤
- ❖ የሰዉ ልጅና በተፈጥሮ ሀብት ግንኙነት (ከአቅም በላይ፣ ተመጣጣኝና ከአቅም በታች የሆነ የህዝብ አሰፋፈር) ምን እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡

| የመማር ብቃቶች | ይዘቶች | የመማር ማስተማር ዘዴዎች | ግምገማ |
|---|---|---|---|
| ምዕራፍ ሶስት፤ ሰዉና የተፈጥሮ ሀብት<br>• የሰዉና የተፈጥሮ ሀብት ግንኙነት ምን እንደሆነ ይተነትናሉ፤<br>❖ የሰዉና የተፈጥሮ ሀብት ስርጭትን (ከአቅም በላይ፣ ተመጣጣኝና ከአቅም በታች) በማለት ይገልፃሉ፤<br>• የሚታደሱና የማይታደሱ የተፈጥሮ ሀብት ዓይነቶች ልዩነትን ይለያሉ፤<br>• በኢትዮጵያ ውስጥ በሰዉ ልጅ ተግባር በተፈጥሮ ሀብት ላይ የሚደርሱ ጉዳትን | 3. ሰዉና የተፈጥሮ ሀብት<br>3.1. የሰዉና ተፈጥሮአዊ አከባቢ ግንኙነት<br>3.2. የሰዉ ልጅና የተፈጥሮ ሀብት (ከአቅም በላይ፣ ተመጣጣኝና ከአቅም በታች)<br>3.3. የተፈጥሮ ሀብት ዓይነቶች<br>3.3.1. የሚታደሱ የተፈጥሮ ሀብቶች<br>3.3.2. የማይታደሱ የተፈጥሮ ሀብቶች<br>3.4. በኢትዮጵያ በተፈጥሮ ሀብት ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ነገሮች | • ተማሪዎች የሰዉ የተፈጥሮ ሀብት ግንኙነት ላይ እንድወያዩ በማድረግ አንዱ በሌላዉ ላይ ያለዉ ጉዳት በመረዳት እንድገልፁ ማድረግ፤<br>ተማሪዎች በአከባቢያቸዉ የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብቶችን እንድዘረዝሩ ካደረጋችዉ በኂላ የተፈጥሮ ሀብት ዓይነቶችን የሚታደሱና የማይታደሱ በማለት ለይተዉ እንድመድቡ ማድረግ፤<br>• ተማሪዎች በአከባቢያቸዉ የሚገኙ ደኖችንና የአፈር ዓይነቶችን ከጎበኙ | • ተማሪዎችን ጥያቄ መጠየቅ ተሳትፎአቸዉን መከታተልና በመጨረሻም ግብረ መልስ መስጠት፤<br>• ተማሪዎች በየግለቸዉ በመስክ ጉብኝታቸዉ ላይ ሪፖርት እንድያቀርቡ ማበረታታትና ግብር መልስ መስጠት |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ይዘረዝራሉ፤<br>• በአከባቢያቸዉ የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብቶችን የሚያሳይ ካርታን በማዘጋጀት ያሳያሉ፡፡ | ➢ የህዝብ ተፅዕኖ፣<br>➢ የእርሻ መሬት መስፋፋት፣<br>➢ የከተሞች መስፋፋት<br>➢ የህዝብ ጥግግት<br>የፕሮጀክት ሥራ፡ ተማሪዎች በአከባቢያቸዉ የሚገኙ ደኖችንና የአፈር ዓይነቶችን እንድጎበኙና ሪፖርት እንድያቀርቡ ማድረግ | በኋላ በተረዱት ላይ ሪፖርት እንድፅፉ ማድረግ፤ በመቀጠል የተረዱትን ነገር በካርታ እንድያሳዩ ማድረግ፡፡ | ያስፈልጋል፡፡ |

# ምዕራፍ 4:ቀደምት የአለም ስልጣኔ ከጥንት እስከ መካከለኛው ክፍለ ዘመን

**የክፍለ ጊዜ ብዛት ---------- 24**

**ከዚህ ምዕራፍየሚጠበቁ የትምህርቱ ውጤቶች**

- ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኃላ፡
- በካርታ ላይ በወንዞች ዳርቻ የተመሰረቱትን ስልጣኔዎች ታሳያለህ/ሽ
- የክርስትና የእስልምናሀይማኖትአመጣጥናመስፋፋትን በማነፃፀር ትገመግማለህ/ሽ
- የመካከለኛክፍለዘመንየአለም ዋናዋነ የታሪክ ክስተቶችን ታገናዝባለህ/ሽ

| የትምህርትብቃት | ይዘት | የማር ማስተማር ዘዴ | ተከታታይ ምዘና |
|---|---|---|---|
| • በወንዞች ዳርቻ የተመሰረቱትን ስልጣኔዎች ትዘረዝራለህ/ሽ<br>• የክርስትናየእስልምናሀይማኖትአ መጣጥናመስፋፋትን በማነፃፀር መመልከት ትችላለህ/ሽ<br>• ስለ ባዛንታየን ኢምፓየር ምንነትታገናዝባለህ/ሽ | 4.ቀደምትየአለምስልጣኔከጥን ትእስከመካከለኛውክፍለዘመን<br>4.1.ጥንታዊየአለምስልጣኔ<br>4.1.1.የሜሶፖታሚያስልጣኔ<br>4.1.2. ቀደምት የህንድና ቻይና ስልጣኔ,<br>4.1.3. ጥንታዊ የግሪኮ-ሮማን ስልጣኔ<br>4.1.4.የክርስትናሀይማኖትአመ ጣጥናመስፋፋት<br>4.2.የመካከለኛክፍለዘመንየአለ ምታሪክ<br>4.2.1. የባዛንታየን ኢምፓየር<br>4.2.2. የክርስትና የእስልምናሀይማኖትአመጣጥና መስፋፋት | • የአለምን ካርታ በመጠቀም ተማሪዎች የሜሶፖታሚያ፣የህንድ፣ ቻይና እና የግሪኮ-ሮማን ስልጣኔ መገኛን እንዲያሳዩ ማድረግ<br>• ተማሪዎችን ስለ ባዛንታየን ኢምፓየር እንዲረዱ የንባብ ምዛና መስጠት<br>• ተማሪዎችን በአምስት ቡድን በማደራጀት እያንዳንዱ ቡድንበጥንታዊ የአለም ስልጣኔ ላይ ተወያይተው እንዲያቀርቡ ማድረግ<br>• ተማሪዎች የህዝብ ብዛትን የሚያመለክት ፒራሚድ በመጠቀም የክርስትና የእስልምናሀይማኖትአመጣጥናመ ስፋፋት ላይእንዲወያዩ ማድረግ፡፡ | • ተማሪዎች በካርታ ለይ ቀደምት የአለም ስልጣኔዎች መገኛን እንዲያሳዩ እደል መስጠት<br>• ተማሪዎች በቡድን በሚወያዩበት ወቅት ክትትል/ምልከታ በማድረግ መመዘን<br>• የተማሪዎችን ገለፃውና ትግበራ መመዝገብ<br>• ለተማሪዎችን ትግበራ ገንቢ የሆነ ግብረ መልስ መስጠት |

# ምዕራፍ 5 :ጥንታዊ የአፍሪካ ታሪክ

**የክፍለ ጊዜ ብዛት**------ 9

**ከዚህ ምዕራፍየሚጠበቁ የትምህርቱ ውጤቶች**

ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኃላ፡

- ጥንታዊየግብፅሥልጣኔ ለአለም ስልጣኔ ያበረከተውን ትገልፃለህ/ሽ
- የጥንት ኑቢያና ሜሮኤ ስልጣኔዎች ከሌሎች ስልጣኔዎች በምን እንደሚለዩ ትዘረዝረለህ/ሽ
- ለሜሮኤ መንግስት መመስረት ምክንያት የሆነው በመለየት ታገናዝባለህ/ሽ

| የትምህርትብቃት | ይዘት | የማር ማስተማር ዘዴ | ተከታታይ ምዘና |
|---|---|---|---|
| • ጥንታዊየግብፅሥልጣኔ ለአለም ስልጣኔ ያበረከተውን ትገልፃለህ/ሽ<br>• የጥንት ኑቢያና ሜሮኤ ስልጣኔዎች ከሌሎችስልጣኔዎች በምን እንደሚለዩትዘረዝረለህ/ሽ<br>• የአፍሪካ ሀገራትን ከቅኝ ግዛት በፊት ያሉትን ሁኔታዎችን በማሰተ.ያየት ታመዛዝናላችሁ | 5. ጥንታዊየአፍሪካታሪክ<br>5.1.የግብፅስልጣኔ<br>5.2. ጥንታዊትየኑቢ.ያስልጣኔ<br>5.3. ጥንታዊትየሜሮኤ ስልጣኔ | • ከመምህርሩ ስለ ጥንታዊየአለምሥልጣኔ ስልጣኔ በቂ የሆነ ገለፃ መስጠት ይጠበቃል<br>▪ በክፍል ውሰጥ ተማሪዎችንበሶስት ቡድኖች እንዲከፈሉ በማድረግየጥንታዊ ግብፅ፣ ኑቢ.ያ እና ሜሮኤ ስልጣኔዎችላይ ተወወያይተው ለክፍል ተማሪዎች እንዲ.ያቀርቡ ማድረግ፤ | • ተማሪዎች የተሰጣቸው ስራ ተሳትፎ፣ ገለፃው እና ትግበራ መመዝገብ<br>▪ ለተማሪዎችን ትግበራ ገንቢ የሆነ ግብረ መልስ በመስጠት ተማሪዎችን ማበረታታት |

# ምዕራፍ 6፡ጥንታዊናየመካከለኛው ዘመን የኢትዮጵያ መንግሥታትና ህዝቦች ታሪክ

**የክፍለ ጊዜ ብዛት** ---------- 12

**ከዚህ ምዕራፍየሚጠበቁ የትምህርቱ ውጤቶች**

ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኃላ፡

- ጥንታዊ የአክሱምሥልጣኔ ምንነት ትገልፃለህ/ሽ
- የዛጉዌ ስር መንግስት ታሪካዊ ክሰተቶችን ትለያለህ/ሽ
- ስለ የኢትዮጵያ ሙስሊም ሱልጣኔቶች ምንነት ታገናዝባለህ/ሽ
- የኢትዮጵያ የጥንትና መካከለኛው ዘመን ምጣኔ ሀብት እንቅስቃሴ ( ግብርና፣ ንግድ ግብር)መሰብሰብ ያሉትን ትገልፃለህ/ሽ

| የትምህርትብቃት | ይዘት | የማር ማስተማር ዘዴ | ተከታታይ ምዘና |
| --- | --- | --- | --- |
| • ጥንታዊ የኢትዮጵያ ታሪክና ሥልጣኔ መገለጫዎችን ትገልፃለህ/ሽ<br>• የጥንትና መካከለኛው ዘመን የኢትዮጵያ ሙስሊም ሱልጣኔቶች ፖሊቲካዊ፣ ምጣኔ ሀብታዊ እና ማህበራዊ መዋቅሮችን ትገልፃለህ/ሽ<br>• የጥንት ኢትዮጵያህዝቦች መካከል የነበረውን ግንኙነትና ትስስርትገነዘባለህ/ሽ<br>• ግብርና፣ ንግድእናግብርበኢትዮጵያምጣኔሀብት ዕድገት ውስጥያላቸውድርሻትገልፃለህ/ሽ | 6.ጥንታዊናየመካከለኛውዘመንየ ኢትዮጵያመንግሥታትናህዝቦ ችታሪክ<br>6.1. አክሱም፣ ላሊበላ እና ጎንደር<br>6.2. የኢትዮጵያ ሙስሊም ሱልጣኔቶች<br>6.3.የህዝቦች እንቅስቃሴ፣ ግንኙነት እና ትስስር(የገዳ ስርአት እና ታዋቂ የሆኑ ማህበራዊ ተቋሟት)<br>6.4. የኢትዮጵያ መስረታዊ ምጣኔ ሀብት እንቅስቃሴ (ግብርና፣ ንግድ እና ግብር መሰብሰብ) | • ከመምህሩ ስለ ጥንታዊናየመካከለኛውዘመንየኢ ትዮጵያመንግሥታትናህዝቦችታሪ ክ ማስተማር በፊት በቂ የሆነ ገለፃ መስጠት ይጠበቃል<br>• በክፍል ውሰጥ ተማሪዎችን በሶስት ቡድኖች እንዲከፈሉ በማድረግ በጥንታዊ ጥንታዊ የኢትዮጵያ ሥልጣኔ (አክሱም፣ ላሊበላ እና ጎንደር) ላይ እንዲከራከሩ ማድረግ.<br>• የክፍሉ ተማሪዎችን በሰባት ቡድኖች በመክፈል ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ርዕሶች መሰረት በማድረግ የፕሮጀክት ስራ ስርተው እንዲያቀርቡ ማድረግ፤ እነሱም.የኢትዮጵያ ሙስሊም ሱልጣኔቶች፣ የህዝቦች እንቅስቃሴ፣የገዳ ስርአት፣ ግብርና፣ ንግድ እና ግብር መሰብሰብ ናቸው | • ተማሪዎች በቡድን በሚከረከሩበት ወቅት ክትትል/ምልከታ በማድረግ መመዘን<br>• የእያንዳንዱን ቡድን ጠንካራና ደካማ ጎን በመለየት መመዝገብ<br>• ለተማሪዎችን ትግበራ ገንቢ የሆነ ግብረ መልስ በመስጠት ተማሪዎችን ማበረታታት |

# ምዕራፍ 7፡ትኩረት የሚሹ ወቅታዊ የዓለም ጉዳዮች

**የክፍለ ጊዜ ብዛት** ---------- 12

**ከምዕራፉ ትምህርት የሚጠበቁ የመማር ውጤቶች:**

**ተማሪዎች ይህንን የምዕራፉን ትምህርት ተምረዉ ከጨረሱ በኃላ፤**

- የተፈጥሮኣዊ አከባቢ ፅንሰ-ሀሳብ ምን እንደሆነ ይገልፃሉ፤
- የሰዉ ልጅ በተፈጥሮኣዊ አከባቢ ላይ የሚያደርሰዉ ጉዳት ይገልፃሉ፤
- በዓለምና በሀገር ደረጃ በተፈጥሮኣዊ አከባቢ ላይ የሚደርሰዉ ጉዳት ምን እንደሆነ ይለያሉ፤
- የአከባቢዉ ህብረተሰብ በተፈጥሮኣዊ አከባቢ እንክብካቤ ላይ በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ዉስጥ የድርሻቸዉን ይወጣሉ

| የመማር ብቃቶች | ይዘቶች | የመማር ማስተማር ዘዴዎች | ግምገማ |
|---|---|---|---|
| • የሰዉ ልጅ በአከባቢ ላይ የሚያደርሰዉ ጉዳት ምን እንደሆነ ይተነትናሉ፤<br>• በተፈጥሮአዊ አከባቢ ላይ የሚደርሰዉን ጉዳት ለመቃነስ የህብረተሰቡ ተሳትፎ ያለዉ ጠቀሜታ ምን እንደሆነ ይገልፃሉ፤<br>• በሚኖሩበት አከባቢ ህብረተሰቡ አከባቢያቸዉን ለማንከባከብ የሚያደርጉት ተሳትፎ ምን እንደሆነ ይገልፃሉ፤<br>• የህዝብ ቁጥር መጨመር በተፈጥሮ ሀብት ላይ የሚያደርሰዉ ምን እንደሆነ ለማወቅ ውይይት ያካሄዳሉ፤ | **7. በአሁኑ ጊዜ ትኩረት የሚሹ የዓለም ጉዳዮች**<br>7.1. የሚንኖርበት አከባቢ<br>7.1.1. የሚንኖርበትን አከባቢ ማወቅ<br>7.1.2. የተፈጥሮአዊ አከባቢ ትላልቅ ችግሮች<br>➢ ብክለት<br>➢ የዓለም ሙቀት መጨመር የኦዞን ንብርብር መሳሳት<br>➢ የተለያዩ ቆሻሻዎች<br>➢ ህይወት ያላቸዉ ነገሮች ቁጥር ማነስ<br>7.1.3. አከባቢን መከባከብ<br>• ባዶ መሬትን በደን መሸፈን<br>• ደን የጠፋባቸዉን ቦታዎችን | • በአከባቢ ላይ የሚከሰቱ ችግሮችና እንዴት መከላከል እንደሚችሉ በክፍል ውስጥ ያሉ ተማሪዎች በሙሉ እንድናገሩ ማድረግ፤<br>• የመስክ ጉብኙት በማዘጋጀት ለተፈጥሮአዊ አከባቢ ብክለት መንስኤ የሆኑ ነገሮችን እንዴት መቀነስ እንደሚቻል በክፍል ውስጥ በቃል ሪፖርት እንድያቀርቡ ማድረግ፤<br>• ተማሪዎች የህዝብ ቁጥር በፍጥነት መጨመር በቀበሌያቸዉ ወይም በወረዳቸዉ ምን ዓይነት ጉዳት እንዳለዉ ጥናታዊ ፅሑፍ እንድያቀርቡ ማድረግ፡፡ | • የተማሪዎችን ውይይትና ክርክር መከታተል፤<br>• ተማሪዎች ሪፖርታቸዉን በፅሑፍ ወይም በቃል ሲያቀርቡ መከታተል<br>• የተማሪዎች የሪፖርት አቀራረብ መመልከት፤<br>• የተማሪዎችን ብቃት መመዝገብ<br>• ተማሪዎችን የሚያበረታታ ግብረ መልስ መስጠት፡፡ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| • የሽብርተኝነት ምንነትና በሰዉ ልጅ፤ ኢኮኖሚና በማህበራዊ ላይ የሚያደርሰዉ ጉዳት ምን እንደሆነ በመወያየት ይገልፃሉ፤<br>• ህገ ወጥ የሰዎች ዝውውር ምክንያትና በማህበራዊ፣ ፖለትካዊና ኢኮኖሚ ላይ የሚያመጣዉ ጉዳት ምን እንደሆነ ይገልፃሉ። | • የተፈጥሮ ሀብትን በሶስት መንገዶች መጠቀም (በቁጠባ፣ መልሶ አገልግሎት ላይ ማዋልና ተራ በተራ በመጠቀም)<br>7.2. ከፍተኛ የሆነ የህዝብ ጥግግት<br>7.3. ሽብርተኝነት<br>7.4. ህገ ወጥ የሰዎች ዝውውር | | |